Amerigroup
District of Columbia

# የተመዝጋቢ አነስተኛ መጽሐፍ

## Amerigroup District of Columbia, Inc.

## DC Healthy Families

1-800-600-4441

**www.myamerigroup.com/DC**

DHCF The Department of Health Care Finance
INVESTING IN YOUR HEALTH

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

DC-MHB-0007-19 AM

## Amerigroup District of Columbia, Inc.

---

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት ሊደውሉልን ወይም ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ 8 a.m. እስከ 5:30 p.m. ድረስ ወደ የእኛ ቢሮ መምጣት ይችላሉ። እንዴት ወደ እኛ ጋር መምጣት እንደሚችሉ አቅጣጫ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 202-548-6700 ይደውሉልን።

**Washington, DC office**
609 H Street NE, Ste. 600
Washington, DC 20002

8 a.m. to 5:30 p.m.
1-800-600-4441

# የተመዝጋቢ አነስተኛ መጽሐፍ

**Amerigroup District of Columbia, Inc.**

DC Healthy Families

**1-800-600-4441**

www.myamerigroup.com/DC

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

DC-MHB-0007-19

Amerigroup District of Columbia

Amerigroup District of Columbia, Inc. የፌደራል የሲቪል መብት ሕጎችን ያከብራል። ሰዎችን በሚከተሉት ምክንያቶች መድልዎ አናደርግባቸውም፡-

- ዘር
- ቀለም
- ብሔራዊ ማንነት
- ዕድሜ
- የአካል ጉዳት
- ጾታ ወይም የጾታ ማንነት

ይህ ማለት በእነዚህ ነገሮች ምክንያት እኛ እርስዎን አናገልዎትም ወይም በተለየ መልኩ መስተንግዶ አንሰጥዎትም ማለት ነው።

**ከእርስዎ ጋር መልእክት መለዋወጥ መቻል አስፈላጊ ነው**
የአካል ጉዳቶች ላሉባቸው ወይም ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የተለየ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች በእርስዎ ላይ ምንም ዓይነት ወጪ ሳያስከትል እነዚህን አገልግሎቶች እናቀርባለን፡-

- የሙያብቃትማረጋገጫያላቸውየምልክትቋንቋአስተርጓሚዎች
- በትላልቅጽሑፍ፣ኦዲዮ፣ኤሌክትሮኒክእናሌሎችቅርጾችየተዘጋጁጽሑፎች
- እርስዎበሚናገሩትቋንቋየሙያብቃትማረጋገጫባላቸውአስተርጓሚዎችየሚሰጥእገዛ
- እርስዎበሚናገሩትቋንቋየተዘጋጁጽሑፎች

እነዚህንአገልግሎቶችለማግኘትበእርስዎ መታወቂያ ካርድ ላይ ወዳለው የአባል አገልግሎቶች ቍጥር ይደውሉ።

**የእርስዎመብቶች**
እነዚህንአገልግሎቶችእያገኙአይደለምብለውያስባሉወይምከላይበተጠቀሱትምክንያቶችእርስዎላይመድልዎየፈጸምንብዎትሆኖይሰማዎታል? እንዲህከሆነ፣የቅሬታማመልከቻ (አቤቱታ) ፋይልማስገባትይችላሉ።በፖስታቤት፣በኢሜይል፣ወይምበስልክፋይልአቤቱታፋይልያስገቡ፡-

Grievance Coordinator
609 H Street NE
Washington, DC 20002

ስልክቍጥር፡-1-800-600-4441 (TTY 711)
ኢሜይል፡- dc-g&a@anthem.com

**ፋይልማስገባትላይእገዛይፈልጋሉ?**ወደየእኛ የቅሬታ አስተባባሪከላይበተጠቀሰውስልክቍጥርይደውሉ።
በተጨማሪየሲቪልመብቶችአቤቱታንወደዩኤስአሜሪካየጤናእናየሰብአዊአገልግሎቶችሚኒስቴር፣የሰብአዊመብቶችቢሮፋይልማስገባትይችላሉ፡-

- **ድርላይ፡-** https://ocrportal.hhs.gov/ocr/portal/lobby.jsf
- **በፖስታቤት፡-** U.S. Department of Health and Human Services
  200 Independence Avenue SW
  Room 509F, HHH Building
  Washington, DC 20201
- **በስልክቍጥር፡-** 1-800-368-1019 (TTY/TDD 1-800-537-7697)

የአቤቱታቅጽንለማግኘት**www.hhs.gov/ocr/office/file/index.html**ንይጎብኙ።

**www.myamerigroup.com/DC**

DHCE The Department of Health Care Finance — INVESTING IN YOUR HEALTH

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

DC-MEM-0997-19

This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

**ENGLISH**
'If you do not speak and/or read English, please call 1-800-600-4441 between 8 a.m. - 6 p.m. A representative will assist you.'

**SPANISH**
Si no habla ni lee inglés, llame al 1-800-600-4441 entre las 8 a.m. - 6 p.m. Un representante lo asistirá.

**AMHARIC**
"እንግሊዘኛመናገር/ወይምማንበብካልቻሉ፣እባክዎበዚህስልክቁጥር 1-800-600-4441 ከ ከጥዋቱ8 .-ከሰዐት6 ይደውሉ። ተወካይይረዳዎታል።"

**VIETNAMESE**
'Nếu quý vị không nói và/hoặc đọc Tiếng Anh, vui lòng gọi 1-800-600-4441 từ 8 a.m. - 6 p.m. Một người đại diện sẽ hỗ trợ quý vị.'

**KOREAN**
'영어를구사하지못하시거나읽지못하시는경우, 1-800-600-4441 번으로 8 a.m. – 6 p.m.중에연락해주십시오. 상담원이도움을드릴것입니다.'

**FRENCH**
Si vous ne parlez pas et / ou ne lisez pas l'anglais, appelez le 1-800-600-4441 entre 8 a.m. - 6 p.m. Un représentant vous aidera.

**ARABIC**

إذا كنت لا تتحدث و/أو تقرأ الإنجليزية، فيرجى الاتصال برقم 1-800-600-4441 بين 8 a.m. - 6 p.m. وسيساعدك أحد الممثلين.

**MANDARIN**
如果您不会说和/或读英语，请致电1-800-600-4441，服务时间： 8 a.m. - 6 p.m.。我们的服务代表将为您提供协助。

**RUSSIAN**
Есливынеговоритеи/иличитаетепо-английски, позвонитепотелефону 1-800-600-4441c
8 a.m. - 6 p.m. Нашпредставительпоможетвам.

**BURMESE**
သင့္အေနျဖင့္အဂၤလိပ္စကားကိုေျပာဆိုႏိုင္ျခင္းႏွင့္/
သို႔မဟုတ္ဖတ္ႏိုင္ျခင္းမရွိပါကေက်းဇူးျပဳ၍ 8 a.m. - 6 p.m. ၾကားတြင္ 1-800-600-4441
သို႔ဖုန္းေခၚဆိုပါ။ ကိုယ္စားလွယ္တစ္ဦးမွသင့္အားကူညီေပးမည္ျဖစ္ပါသည္။

**CANTONESE**
「如果您不會說和/或讀英語，請致電1-800-600-4441，服務時間：8 a.m. - 6 p.m.。我們的服務代表將為您提供協助。」

**FARSI**

اگر انگلیسی صحبت نمی کنید/نمی خوانید، لطفا بین ساعات 8 a.m. - 6 p.m. با شماره 1-800-600-4441تماس بگیرید. یکی از نمایندگان ما به شما کمک خواهد کرد.

**POLISH**
Osoby, które nie potrafią mówić lub czytać po angielsku, mogą zadzwonić na numer 1-800-600-4441 w godzinach od 8 a.m. - 6 p.m., aby skorzystać z pomocy konsultanta.

**PORTUGUESE**
Caso você não fale/leia em inglês, ligue para 1-800-600-4441 entre 8 a.m. - 6 p.m. Um representante o ajudará.

**PUNJABI**
ਜੇਕਰ ਤੁਸੀਂ ਅੰਗਰੇਜ਼ੀ ਬੋਲਦੇ ਅਤੇ/ਜਾਂ ਪੜ੍ਹਦੇ ਨਹੀਂ, ਕਿਰਪਾ ਕਰਕੇ 8 a.m. - 6 p.m. ਦੇ ਵਿਚਕਾਰ 1-800-600-4441ਉੱਤੇ ਕਾਲ ਕਰੋ। ਇੱਕ ਪ੍ਰਤੀਨਿਧ ਤੁਹਾਡੀ ਸਹਾਇਤਾ ਕਰੇਗਾ।

**HAITIAN CREOLE**
Si ou pa pale ak/oswa li Angle, tanpri rele 1-800-600-4441 ant 8 a.m. - 6 p.m. Yon reprezantan ap ede w.

**HINDI**
यदि आप अंग्रेज़ी बोलते और/या पढ़ते नहीं, कृपया 8 a.m. - 6 p.m. के बीच 1-800-600-4441पर कॉल करें। एक प्रतिनिध आपकी सहायता करेगा।

**SOMALI**
Haddii aadan ku hadlin iyo/ama qorin luuqada Ingiriiska, fadlan wac lambarkan 1-800-600-4441 inta u dhaxaysa
8 a.m. - 6 p.m. wakiil ayaa ku caawin doona.

**HMONG**
Yog tias koj tsis hais thiab/lossis nyeem tau Lus As Kiv, thov hu rau 1-800-600-4441 thaum 8 a.m. -6 p.m. Ib tug neeg sawv cev yuav pab tau koj.

**ITALIAN**
Se ha difficoltà a parlare e/o leggere la lingua inglese, chiami il numero 1-800-600-4441 dalle 8 a.m. - 6 p.m. Un rappresentante le presterà assistenza.

**TAGALOG**
Kung hindi ka nakakapagsalita at/o nakakapagbasa ng Ingles, pakitawagan ang 1-800-600-4441 sa pagitan ng 8 a.m. -6 p.m. May kinatawan na tutulong sa iyo.

**JAPANESE**
英語がわからない場合は、8 a.m. - 6 p.m. の間に1-800-600-4441までお電話ください。担当者がサポートいたします。

# አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮች

## (ይህን ገጽ ቆርጠው ያውጡት እና ከስልክዎ አጠገብ ያስቀምጡት)

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ወይም ስለ የእርስዎ MCO ጥያቄ ካልዎት፦** | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 1-800-600-4441 (ነጻ የስልክ መሥመር) | ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት |
| | TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 711 (ነጻ የስልክ መሥመር) | ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት |
| **የእርስዎ ዶክተር ቢሮ ከተዘጋ በኋላ ክብካቤ ማግኘት ካስፈለግዎት፦** | Nurse HelpLine | 1-800-600-4441 (ነጻ የስልክ መሥመር) | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| | TTY/TDD Nurse HelpLine | 711 (ነጻ የስልክ መሥመር) | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **በ24 ሰዓታት ውስጥ በዶክተር መታየት ካስፈልግዎት ("አስቸኳይ ሕክምና")፦** | የእርስዎ PCP ቢሮ | (የእርስዎን PCP መረጃ እዚህ ላይ ይሙሉት) | |
| | Nurse Helpline | 1-800-600-4441 (ነጻ የስልክ መሥመር) | በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **ወደ ሐኪም ቀጠሮ ለመሄድ ትራንስፖርት ካስፈለግዎት፦** | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | [ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት]<br>1-800-600-4441 (ነጻ የስልክ መሥመር)<br>ወይም<br>Medical Transportation Management<br>1-888-828-1081 (ነጻ የስልክ መሥመር) | |
| **የአእምሮ ጤና ክብካቤ ካስፈለግዎት ወይም የአእምሮ ጤና ነክ ጥያቄ ካልዎት፦** | የእርስዎ PCP ቢሮ | (የእርስዎን PCP መረጃ እዚህ ላይ ይሙሉት) | |
| | Nurse HelpLine | 1-800-600-4441 (ነጻ የስልክ መሥመር) | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| | DC Department of Behavioral Health Access Hotline | 1-888-793-4357 | በቀን 24 ሰዓታት፣ በሳምንት 7 ቀናት |
| **የእርስዎን ቋንቋ የሚናገር ሰው ማግኘት ካስፈለግዎት ወይም መስማት የተሳንዎት ከሆኑ፦** | የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 1-800-600-4441 (ነጻ የስልክ መሥመር) | ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት |
| | TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች | 711 (ነጻ የስልክ መሥመር) | ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት |
| **የጥርስ ሕክምና ነክ ጥያቄዎች፦** | DentaQuest | 1-844-876-7918 | ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 5 ፡ 30 ከሰዐት |
| **የዓይን ዕይታ ነክ ጥያቄዎች፦** | Avesis | 1-833-554-1012 | ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 5 ፡ 30 ከሰዐት |
| **በድንገተኛ አደጋ ጊዜ፣ ወደ 911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል የድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል ይሂዱ** | | | |

# የግል መረጃ

የእኔ Medicaid መታወቂያ ቁጥር፡- ______________________________________________________

ለእኔ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP)፡-______________________________________________________

የእኔ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP) አድራሻ፡- ______________________________________________________

የእኔ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP) ስልክ ቁጥር፡- ______________________________________________________

የልጅ Medicaid መታወቂያ ቁጥር፡-

__________________

__________________

__________________

ለልጅ/ልጆች ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP)፡- ______________________________________________________

ለልጅ/ልጆች ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP) አድራሻ፡-

______________________________________________________

ለልጅ/ልጆች ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ PCP) ስልክ ቁጥር፡-

______________________________________________________

የእኔ ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP)፡-

______________________________________________________

የእኔ ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP) አድራሻ፡-

______________________________________________________

የእኔ ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP) ስልክ ቁጥር፡-

______________________________________________________

ለልጅ/ልጆች ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP)፡-

______________________________________________________

ለልጅ/ልጆች ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP) አድራሻ፡-

______________________________________________________

ለልጅ/ልጆች ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP) ስልክ ቁጥር፡-

______________________________________________________

# ማውጫ


**አስፈላጊ የስልክ ቁጥሮች** ..... 3

**ወደ Amerigroup District of Columbia, Inc. እንኳን በደህና መጡ** ..... 9

ይህ አነስተኛ መጽሐፍ እንዴት እንደሚያገለግል ..... 9

ይህ የተመዝጋቢ አነስተኛ መጽሐፍ እንዴት ሊያግዝዎት እንደሚችል ..... 9

**የእርስዎ ሙብቶች** ..... 10

**የእርስዎ ግዴታዎች** ..... 11

**የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ** ..... 12

**የእርስዎ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP)** ..... 13

የእርስዎን PCP መምረጥ ..... 13

እንዴት የእርስዎን PCP መቀየር እንደሚችሉ ..... 13

**የእርስዎ ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP)** ..... 14

የእርስዎን PDP መምረጥ ..... 14

እንዴት የእርስዎን PDP መቀየር እንደሚችሉ ..... 14

**መደበኛ ሕክምና፣ አስቸኳይ ሕክምና እና ድንገተኛ ሕክምና** ..... 15

መደበኛ ሕክምና ..... 15

አስቸኳይ ሕክምና ..... 15

ድንገተኛ ሕክምና ..... 15

**ከከተማ ውጪ ሲሆኑ የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት** ..... 15

**በአውታረ-መረብ ውስጥ ያሉ እና ከአውታረ-መረብ ውጭ ያሉ አገልግሎት አቅራቢዎች** ..... 17

**ቀጠሮ ማስያዝ** ..... 18

ከእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ ..... 18

ቀጠሮን መቀየር ወይም መሰረዝ ..... 18

የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ሲዘጋ እንክብካቤ ማግኘት ..... 18

የእርስዎን ዶክተር ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል? ..... 18

**ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች** ..... 19

የትራንስፖርት አገልግሎቶች ..... 20

የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች/መስማት እና ማየት ለተሳናቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች ..... 20

የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ..... 20

የትርጉም አገልግሎቶች ..... 20

መስማት እና ማየት ለተሳናቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች ..... 20

**የአጠቃቀም አስተዳደር ማስታወቂያ** ..... 20

**ወደ አጠቃቀም አስተዳደር ሠራተኞች መዳረሻ** ..... 21

ልዩክብካቤእናሪፌራሎች ..... 21

ራስን በራስ ሪፌር ማድረጊያ አገልግሎቶች ..... 22

የሥነ አእምሮ ጤና አገልግሎቶች ........ 23
ለአልኮል ወይም ሌላ የአደገኛ መድኃኒቶች ችግሮች አገልግሎቶች ........ 23
የወሊድ ቁጥጥር እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች........ 23
የመድኃኒት መደብር አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች ........ 24
የበሽታ ቁጥጥር አስተዳደር የተማከለ የእንክብካቤ አሃድ ........ 25
የሕክምና ማስተባበር እና የጉዳይ ክትትል ፕሮግራሞች ........ 26
**ጎልማሶች እንዳይታመሙ ለመከላከል የሚሰጡ አገልግሎቶች ........ 27**
በሐኪም ለመታየቶች (“ምርመራዎች”) የሚሰጡ ምክሮች........ 27
የመከላከያ የምክር አገልግሎት........ 27
**እርግዝና........ 28**
My Advocate™ ን ማወቅ ........ 28
ነፍሰጡር ሲሆኑ ........ 29
አዲስ ልጅ ሲወልዱ ........ 30
ልጅ ከወለዱ በኋላ........ 30
**የእርስዎ ልጅ ጤና........ 31**
Health Check Program for Children (EPSDT)........ 31
ስደተኛ ልጆች........ 31
ለእርስዎ ልጅ ጥርስ ክብካቤ........ 31
ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያሉዋቸው ልጆች ........ 31
የ IDEA Program ........ 32
ለሕፃናት እና ታዳጊ ወጣቶች ክትባቶች (ሾትስ) ........ 32
**የእርስዎ ጤና የመድን ሽፋኖች........ 33**
በ Amerigroup የመድን ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች ........ 33
እኛ የማንከፍልባቸው አገልግሎቶች ........ 38
አዳዲስ የሕክምና ቴክኖሎጂዎች ........ 38
**ሌላ አስፈላጊ መረጃ ........ 39**
አድራሻዬን ብቀይር ምን አደርጋለሁ........ 39
ልጅ ብወልድ ምን ማድረግ አለብኝ........ 39
ልጅ በጉዲፈቻ ባሳድግ ምን ማድረግ አለብኝ ........ 39
በእኔ ቤተሰብ ውስጥ ሰው ቢሞት ምን ማድረግ አለብኝ........ 39
እንዴት የእኔን MCO መቀየር እችላለሁ ........ 40
በመድን ሽፋን ላለው አገልግሎት ክፍያ ብጠየቅስ ምን አደርጋለሁ ........ 40
የመድን ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ክፍያን መክፈል ........ 40
የላቀ መመሪያ ........ 41
ሌላ ኢንሹራንስ ቢኖረኝ ምን አደርጋለሁ........ 41
ሁለቱም Medicaid እና Medicare ካሉኝ ምን አደርጋለሁ........ 41

ማጭበርበር ድርጊት ..... 41
የሐኪም (ዶክተር) ማበረታቻ ዕቅድ ይፋ ማድረጊያ ..... 41
**ቅሬታዎች፣ ይግባኝ ጥያቄዎች እና ፍትሐዊ ዳኝነት ..... 42**
ቅሬታዎች ..... 42
ይግባኝ ጥያቄዎች እና ፍትሐዊ ዳኝነት ..... 42
ይግባኞች ..... 43
የተፋጠነ (አጣዳፊ) የቅሬታዎች እና ይግባኝ ጥያቄዎች ማስተናገድ ሂደት ..... 43
በቅሬታዎች፣ ይግባኝ ጥያቄዎች እና ፍትሐዊ ዳኝነት ሂደት ወቅት የእርስዎ መብቶች ..... 43
**የ HIPAA የግላዊነት ጥበቃ አደራረግ ማስታወቂያ ..... 44**
**Office of Health Care Ombudsman እና Bill of Rights ..... 47**
**ትርጓሜዎች ..... 49**

# ወደ Amerigroup District of Columbia, Inc. እንኳን በደህና መጡ

እንደ የእርስዎ የጤና መድን ዕቅድ Amerigroup District of Columbia, Inc. ን ስለመረጡ እናመሰግናለን። የ District Medicaid እና CHIP ተመዝጋቢዎችን በ DC Healthy Families ጥዋት Immigrant Children's Programs በኩል ስናገለግል ኩራት ይሰማናል።

ይህ የተመዝጋቢ አነስተኛ መጽሐፍ ስለ Amerigroup እና እንዴት የእርስዎ ጤና መድን ዕቅድ እንደሚሠራ የሚያስረዳ አስፈላጊ መረጃ አለው። እባክዎ በጥንቃቄ ይገምግሙት። እንደ Amerigroup ተመዝጋቢነትዎ፣ እንደ በሐኪም መታየቶች፣ ላብራቶሪ እና ራጂዎች እንዲሁም ክትባቶች ከዚህ በተጨማሪ እርስዎ ጤናማ ሆነው እንዲኖሩ እና የተሻለ ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎት የሚያደርጉ ተጨማሪ ነገሮችን የመሳሰሉ መደበኛ የ Medicaid ጤና መድን ሽፋን ጥቅማ ጥቅሞችን በሙሉ ያገኛሉ።

በየወሩ፣ Amerigroup የአዲስ የተመዝጋቢ ማስተዋወቂያ ትምህርት ያዘጋጃል። ይህ እርስዎ ስለ የእርስዎ የ Amerigroup የመድን ሽፋን ጥቅማጥቅሞች የበለጠ የሚያውቁበት ሌላ መንገድ ነው። በማስተዋወቂያ ትምህርቱ ላይ፣ ለጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ከእኛ ሠራተኞች መካከል ከአንዱ ጋር መነጋገር ይችላሉ። አሁኑኑ ከእኛ ጋር መነጋገር ያስፈልግዎታል? በአንድ ጠቅታ ወይም በአንድ የስልክ ጥሪ ብቻ ልንገኝ እንችላለን። ወደ የእርስዎ መለያ (አካውንት) በመለያ ይግቡ ወይም መስመር ላይ (ኦንላይን) www.myamerigroup.com/DC ላይ ይመዝገቡ። ደኅንነት የተጠበቀ መልእክት ይላኩልን ወይም መልሰን እንድንደውልል የመልሶ ማስደወያ መርሐግብርን ያስይዙ። ወይም ወደ የእኛ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ክፍል በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 (TTY 711) ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ 8 ጥዋትእስከ ምሽቱ 6 ከሰዐትምሥራቃዊ የሰዓት አቆጣጠር ድረስ ይደውሉ። በእያንዳንዱ የእርምጃ መውሰጃ መንገድ ላይ ለማገዝ ከጎንዎ አለንልዎት!

## ይህ አነስተኛ መጽሐፍ እንዴት እንደሚያገለግል

Amerigroup District of Columbia, Inc. በኮሎምቢያ ዲስትሪክት እርስዎ የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማገዝ የሚከፈልልዎት የሚተዳደር የጤና መድን ሽፋን ዕቅድ ነው። በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት Amerigroup ሥራውን እንደሚሠራ፣ እንዴት ዶክተሮችን ማግኘት እንደሚቻል፣ እንዴት ለእኛ መደወል እንደሚችሉ እና እኛ ለምን ነገሮች ክፍያ እንደምንፈጽምባቸው እንነግርዎታለን። በጤና ክብካቤ ላይ እና በዶክተሮች ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላት አንዳንድ ጊዜ ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው። እነዚህን ቃላት በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ትርጓሜዎች በሚለው ክፍል ውስጥ ማብራሪያ ሰጥተንባቸዋል።

**በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሚያነቡዋቸው ነገሮች ላይ ጥያቄ ካልዎት ወይም ስለ Amerigroup ሌሎች ጥያቄዎች ካልዎት፣ ወደ Amerigroup የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 (TTY 711) መደወል ወይም www.myamerigroup.com/DC መጎብኘት ይችላሉ እኛም እርስዎንን ለማገዝ የሚቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።**

## ይህ የተመዝጋቢ አነስተኛ መጽሐፍ እንዴት ሊያግዝዎት እንደሚችል

ይህ የተመዝጋቢ አነስተኛ መጽሐፍ የሚከተሉትን ይነግርዎታል፡-

- የጤና እንክብካቤን እንዴት መድረስ እንደሚቻል
- የመድን ሽፋን ያላቸው የእርስዎ አገልግሎቶች
- የመድን ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች
- እንዴት የእርስዎን ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እና ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (የእርስዎ PCP ወይም PDP)ን መምረጥ እንደሚችሉ
- ካመምዎት ምን ማድረግ እንደሚችሉ
- ቅሬታ ካልዎት ወይም በ Amerigroup የተሰጠ ውሳኔን ለማስቀየር (ይግባኝ ለማለት) ከፈለጉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

ይህ አነስተኛ መጽሐፍ እንዴት Amerigroup ሥራውን እንደሚሠራ መሠረታዊ የሆነ መረጃን ይሰጥዎታል። ማናቸውም ጥያቄዎች ካልዎት እባክዎ ወደ Amerigroup የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በማናቸውም ጊዜ[ከሰኞ እስከ አርብ ከ ጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት] ይደውሉ።

## የእርስዎ መብቶች

**የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡-**

- ከአክብሮት እና ከክብር ጋር መስተናገድ
- ከእርስዎ ዶክተሮች እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ሲነጋገሩ ጉዳይዎት የግል ጉዳይ እንደሆነ ማወቅ
- እርስዎ በሚገባዎት ቋንቋ አንድን በሽታ ወይም ሕክምና እንዲብራራልዎት መደረግ
- በእርስዎ እንክብካቤ አሰጣጥ ላይ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ
- ዋጋው ከግምት ሳይገባ ወይም ሕክምናው በእርስዎ የመድን ሽፋን ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ ይኑር አይኑር ሳይቆጠር በመረጃ ላይ የተመረኮዘ ውሳኔ ላይ መድረስ እንዲችሉ ስላሉት የሕክምና አማራጮች እንዲሁም እያንዳንዱ አማራጭ ያሉበትን ስጋቶች በተሟላ፣ እና ሊገባዎት በሚችል መልኩ ማብራሪያን ማግኘት።
- ሕክምናን ወይም እንክብካቤን አልቀበልም ማለት
- በድንገተኛ አደጋ ሁኔታዎች ውስጥ ካልሆነ በቀር ከአካላዊ እና ኬሚካላዊ ማነቆዎች ነጻ መሆን
- ትክክል ካልሆነ ማስቀየር እንዲችሉ የእርስዎን የሕክምና ሪኮርዶች ማየት መቻል
- በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ያለ ብቁ የሆነ PCP/PDP መምረጥ እና የእርስዎን PCP/PDP መቀየር
- ለእርስዎ በተሰጠው አገልግሎት ላይ ቅሬታ ማቅረብ እና መልስ ማግኘት
- እርስዎ Amerigroup አንድን አገልግሎት ወይም ነገር በመከልከል፣ መጠኑን በመቀነስ ወይም በማስቆም ላይ የሰጠው ውሳኔ ልክ አይደለም ብለው የሚያምኑ ከሆነ ይግባኝ ማለት ወይም ፍትሐዊ ዳኝነት ችሎት እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ።
- የእርስዎ ምርጫ ከሆነ አገልግሎት ሰጪ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችን እና አቅርቦቶችን ይቀበሉ።
- ያለምንም መጉላላት የሕክምና እንክብካቤን ማግኘት
- በላቁ መመሪያዎች ላይ መረጃን መቀበል እና ማናቸውንም ዕድሜ ልቅ የሚዘልቅ ሕክምናን ለመቀበል መስማማት ወይም ለማቋረጥ መወሰን
- የአምሪግሩፕ Amerigroup የተመዝጋቢአነስተኛ መጽሐፍ እና/ወይም የአገልግሎት አቅራቢ ማውጫን ቅጂ መቀበል
- ስለ የእኛ ሐኪሞች እና ሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች መረጃን መቀበል
- አዲስ የሕክምና ዕቅድ እስከሚኖርዎት ድረስ አሁን እየተቀበሉ ያሉትን ሕክምና እየተቀበሉ መቀጠል
- የሰው እና የሰነድ ትርጉም አገልግሎቶችን **ያለምንም ክፍያ በነጻ** ማግኘት
- የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን አልፈልግም ማለት
- የትራንስፖርት አገልግሎቶችን **ያለምንም ክፍያ በነጻ** ማግኘት
- ቅድሚያ ፈቀዳ አሰጣጥ አካሄዶችን በተመለከተ ማብራሪያን ማግኘት
- ስለ Amerigroup ድርጅት፣ አገልግሎቶቹ፣ ፋይናንስ-ነክ አቋሙና ሁኔታው እንዲሁም የእኛን ዶክተሮች የምንከፍልባቸው ማናቸውም ልዩ መንገዶችን በተመለከተ መረጃ ማግኘት
- ስለ ደንበኛ እርካታ የሚደረጉ ዳሰሳ ጥናቶች ውጤታቸውን የያዙ አጭር ማጠቃለያዎችን ማግኘት
- በሐኪም ለሚታዘዙ መድኃኒቶች የአምሪግሩፕ Amerigroup "እንደተጻፈው ተጠቀም" መመሪያ መቀበል
- የመድን ሽፋን ያላቸውን ሁሉንም መድኃኒቶችን መቀበል
- ስለ የእርስዎ መብቶች እና ግዴታዎች ለ Amerigroup ጥቆማ ሐሳቦችን መስጠት
- የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ሊገኙ ከሚችሉ እና ተደራሽ ከሆኑ፣በሰዐቱ እና የተቀናጀ እንክብካቤ ከሚሰጡ፣ባህላዊ እምነቶችዎን የሚያከብሩ እና የተለየ ፍላጎቶችዎን ሊያሟላ የሚያስችል አስፈላጊውን እንክብካቤ ማግኘትዎን ከሚያረጋግጡ አቅራቢዎች ያግኙ።

## የእርስዎ ግዴታዎች

**ለሚከተሉት ነገሮች እርስዎ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፦**


- እርስዎን እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡትን ሰዎች በአክብሮት እና በክብር ማስተናገድ
- የ DC Medicaid Managed Care Program እና የ Amerigroup ደንቦችን ማክበር
- ከእርስዎ ዶክተሮች እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጥዎትን መመሪያዎች ማክበር
- ለእርስዎ ዶክተሮች እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ስለጤናዎ ሁኔታ መንገር
- ከአገልግሎት አቅራቢ ጋር ለእርስዎ የትኛው የጤና እንክብካቤ የተሻለ እንደሆነ መወሰን ላይ እንደ አንድ ቡድን አብሮ መሥራት
- በዕቅድ ወደ ተያዙ ቀጠሮዎች መሄድ
- ቀጠሮዎትን መሰረዝ ካለብዎት ለእርስዎ ዶክተር ቢያንስ 24 ሰዓታት ቀደም ብለው መንገር
- የእርስዎ ዶክተር የሚሰጥዎትን መመሪያዎች ካልተረዱዋቸው ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥዎት መጠየቅ
- ድንገተኛ የሕክምና ጉዳይ ሲያጋጥምዎት ብቻ ወደ ድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል መሄድ
- የእርስዎ ጤና ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ የሕክምና እና የግል ችግሮች ለእርስዎ PCP/PDP መንገር
- እርስዎ ወይም የእርስዎ ተመዝጋቢ የሆነ የቤተሰብ አባል ሌላ የጤና ኢንሹራንስ ካላችሁ ወይም የእርስዎን አድራሻ ወይም ስልክ ቁጥር ከቀየሩ ወደ Economic Security Administration (ESA) እና Amerigroup ሪፖርት ማድረግ
- በቤተሰብዎ ውስጥ ለውጥ ካለ (ለምሳሌ ሞት፣ ልደት ወዘተ) ለ Economic Security Administration (ESA) እና Amerigroup ሪፖርት ማድረግ
- የእርስዎን የጤና ችግሮች ለመረዳት መሞከር እና የሕክምና ግቦችን በማዘጋጀት ላይ መሳተፍ
- ከዚህ ቀደም እርስዎን ካከምዎት አገልግሎት አቅራቢዎች የሕክምና ሪኮርዶችን ማግኘት ላይ የእርስዎን ዶክተር ማገዝ
- በአደጋ ምክንያት ወይም በሥራ ላይ ጉዳት ከደረሰብዎት ለ Amerigroup ማሳወቅ

## የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ

አንድ ጊዜ እርስዎ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP) እንደ ተመደበልዎት የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ በፖስታ ቤት በኩል እንልክልዎታለን። ይህ ካርድ የእርስዎ ዶክተሮች፣ ሆስፒታሎች፣ የመድኃኒት መደብሮች እና ሌሎች እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ እንደሆኑ እንዲያውቁ ያደርጋል። የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ላይ ያለው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ እባክዎ ያረጋግጡ። ማናቸውም ችግሮች ካሉብዎት ወይም የእርስዎ ካርድ ከጠፋብዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። እያንዳንዱ Amerigroup ተመዝጋቢ የራሱ/የራሷ ካርድ አለው/ላት። የእርስዎ ልጆችም የራሳቸው የሆነ ካርድ ይኖራቸዋል። ካርዶቹ እንዳይጠፉ የእርስዎን ልጆች ካርድ እርስዎ መያዝ ይኖርብዎታል። ማንም ሌላ ሰው የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ እንዲጠቀምበት መፍትቀድ በሕግ ያስጠይቃል።

### የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይህን ይመስላል፦


**የካርዱ ፊት ገጽ**


Amerigroup
District of Columbia

Effective Date:
Date of Birth:
Amerigroup #:

www.myamerigroup.com/DC
Member Name:
DC Healthy Families Program Number:
Primary Care Provider (PCP):
PCP Telephone #:
PCP Address:
Primary Dental Provider (PDP):
PDP Telephone #:
PDP Address:
Vision: 1-833-554-1012 Dental: 1-844-876-7918
Member Services/24-hour Nurse HelpLine: 1-800-600-4441 (TTY 711)
Behavioral Health Crisis Line: 1-844-405-4300 (TTY 711)
Pharmacy Member Services: 1-833-214-3604

**የካርዱ ጀርባ**


MEMBERS: Please carry this card at all times. Show this card before you get medical care. You do not need to show this card before you get emergency care. If you have an emergency, call 911 or go to the nearest emergency room. Always call your Amerigroup PCP for nonemergency care. If you have questions, call Member Services at 1-800-600-4441. If you are deaf or hard of hearing, please call 711.

HOSPITALS: Preadmission certification is required for all nonemergency admissions, including outpatient surgery. For emergency admissions, notify Amerigroup within 24 hours after treatment at 1-800-454-3730.

ECONOMIC SECURITY ADMINISTRATION (ESA) CHANGE CENTER:1-202-727-5355
TRANSPORTATION SERVICES: 1-888-828-1081 (TTY 711)

PROVIDERS: Certain services must be preauthorized. Care that is not preauthorized may not be covered. For preauthorization/billing information, call 1-800-454-3730. For preauthorization of medications, call 1-800-454-3730.

PHARMACIES: Submit claims using RxBIN: 020107; RxPCN: FC; RxGRP: WK4A
To reach Help for Pharmacists, call 1-833-235-2029

SUBMIT MEDICAL CLAIMS TO:
AMERIGROUP • P.O. BOX 61010 • VIRGINIA BEACH, VA 23466-1010
USE OF THIS CARD BY ANY PERSON OTHER THAN THE MEMBER IS FRAUD.

DC01 09/19

እያንዳንዱ የ Amerigroup ተመዝጋቢ የራሱ ወይም የራሷ ካርድ አለው/ላት። ማንም ሌላ ሰው የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ እንዲጠቀምበት መፍትቀድ በሕግ ያስጠይቃል።

**ሁልጊዜ የእርስዎ የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ እና ፎቶ ያለበት መታወቂያ አብረው ይዘው መገኘት እንዳለብዎት እባክዎ ያስታውሱ። ማናቸውንም የሕክምና እንክብካቤ ከማግኘትዎት በፊት ወይም በመድኃኒት መደብር መድኃኒት ከማግኘትዎት በፊት የእርስዎ ካርድ ሁልጊዜ ያሳዩ።**

# የእርስዎ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP)

አሁን እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ እንደመሆንዎት የእርስዎ PCP (ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ) እርስዎን እና የእርስዎን ቤተሰብ የሚያስፈልጋችሁን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ያግዝዎታል።

እንክብካቤ ማግኘት ሲያስፈልግዎት ወደ እርስዎ PCP መጀመሪያ መደወል አስፈላጊ ነው። ወደ Amerigroup ከመመዝገብዎ በፊት ቀደም ሲል PCP ከነበርዎት እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች ወደ 1-800-600-4441 ይደውሉ። የሚፈልጉ ከሆነ ከዚያ PCP ጋር እንዲቆዩ ለማድረግ ማገዝ እንችላለን።

## የእርስዎን PCP መምረጥ

1. **ወደ Amerigroup በሚመዘገቡበት ጊዜ የእርስዎን PCP ይምረጡ።** ይህ ግለሰብ እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ የእርስዎ PCP ይሆናል።
   - አሁን ያለው የእርስዎ PCP የAmerigroup አውታረ-መረብ ያለ አገልግሎት ሰጪ ከሆነ ከዚያ ዶክተር ጋር አብረው መቆየት ይችላሉ።
   - PCP ከሌልዎት፣ ከእኛ የአገልግሎት አቅራቢ ማውጫ ዝርዝር ውስጥ ወይም ከ www.myamerigroup.com/DC ላይ መምረጥ ይችላሉ። የዶክተሮቹን አድራሻዎች፣ ስልክ ቁጥሮች እና ልዩ ሥልጠናን ይዘረዝራል።
   - ዶክተር መምረጥ ላይ እገዛ ካስፈልግዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ።
   - በእኛ የመድን ዕቅድ ውስጥ በገቡ ባሉት የመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ውስጥ PCP ካልመረጡ፣ እኛ ራሳችን ዶክተር ለእርስዎ እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PCP ካልፈለጉዋቸው የራስዎንPCP መለወጥ ይችላሉ። የእርስዎን PCP ለመቀየር ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ።
   - Amerigroup የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። የእርስዎ ካርድ የእርስዎን PCP ስም እና የስልክ ቁጥር በላዩ ላይ ይኖርበታል።
2. **በእኛ የመድን ዕቅድ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ ተመዝጋቢ የእርስዎን ልጆች ጨምሮ PCP ይምረጡላቸው።** የእርስዎ PCP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፦
   - የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሕክምና ዶክተር - አብዛኛውን ጊዜ ሙሉውን ቤተሰብ ማከም ይችላሉ።
   - የውስጥ ደዌ ሕክምና ዶክተር - አብዛኛውን ጊዜ ጎልማሶችን እና ዕድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆችን ያክማሉ።
   - የሕፃናት ሐኪም - ከተወለዱ ጨቅላ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ጎልማሳ ድረስ ያክማሉ
   - የፅንስ/የማህፀን ሐኪም (OB/GYN) - በሴቶች ጤና እና በወሊድ ክብካቤ ላይ ልዩ ሥልጠና የወሰዱ።
   - ልዩ የጤና ክብካቤ ፍላጎቶች እርስዎ ወይም የእርስዎ ልጅ ካላችሁ አንድን ስፔሺያሊስት እንደ የእናንተ PCP አድርገው መምረጥ ይችላሉ።
3. **የእርስዎን PCP ሲመርጡ፣ እባክዎ፦**
   - እርስዎ ወደ የሚፈልጉት ሆስፒታል ሊልክዎት የሚችል ዶክተርን ይምረጡ። ሁሉም ዶክተሮች ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። የእኛ የአገልግሎት አቅራቢ ማውጫ አንድ PCP ወደ የትኛዎቹ ሆስፒታሎች ሊልክዎት እንደሚችሉ ይዘረዝራል። እገዛ ለማግኘት ወደ የአባል አገልግሎቶች መደወል ይችላሉ።
   - አንዳንድ ጊዜ የመረጡት PCP አዳዲስ ታካሚዎችን ለመቀበል አይችል ይሆናል። ሌላ ዶክተር መምረጥ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እንዲያውቁት እናደርግዎታለን።
   - ወደ የእርስዎ መኖሪያ ቤት ወይም መሥሪያ ቤት አቅራቢያ የሚገኝ ዶክተርን ይምረጡ።

## እንዴት የእርስዎን PCP መቀየር እንደሚችሉ

የእርስዎን PCP በማናቸውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአገልግሎት አቅራቢ ማውጫው ላይ አዲስ PCP መምረጥ ብቻ በቂ ነው። አንድ ጊዜ የእርስዎን አዲሱን PCP መርጠው እንደጨረሱ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ። አዲስ PCP መምረጥ ላይ እገዛ ካስፈለግዎት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎት ይችላሉ።

# የእርስዎ ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም (PDP)

አሁን እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ እንደመሆንዎት የእርስዎ PDP (ተቀዳሚ የጥርስ ሐኪም) እርስዎን እና የእርስዎን ቤተሰብ የሚያስፈልጋችሁን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ያግዝዎታል።

እንክብካቤ ማግኘት ሲያስፈልግዎት ወደ እርስዎ PDP መጀመሪያ መደወል አስፈላጊ ነው። ወደ Amerigroup ከመመዝገብዎ በፊት ቀደም ሲል የጥርስ ሐኪም ከነበርዎት እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች ወደ 1-800-600-4441 ይደውሉ። የሚፈልጉ ከሆነ ከዚያ የጥርስ ሐኪም ጋር እንዲቆዩ ለማድረግ ማገዝ እንችላለን።

## የእርስዎን PDP መምረጥ

1. **ወደ Amerigroup በሚመዘገቡበት ጊዜ የእርስዎን PDP ይምረጡ።** ይህ ግለሰብ እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ የእርስዎ PDP ይሆናል።
   - አሁን ያለው የእርስዎ PDP የAmerigroup አውታረ-መረብ ያለ አገልግሎት ሰጪ ከሆነ ከዚያ ዶክተር ጋር አብረው መቆየት ይችላሉ።
   - PDP ከሌልዎት፣ ከእኛ የጥርስ ሕክምና አገልግሎት አቅራቢ ማውጫ ዝርዝር ውስጥ ወይም ከ www.myamerigroup.com/DC ላይ መምረጥ ይችላሉ።
   - የጥርስ ሐኪም መምረጥ ላይ እገዛ ካስፈልግዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ።
   - በእኛ የመድን ዕቅድ ውስጥ በገቡ ባሉት የመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ውስጥ PDP ካልመረጡ፣ እኛ ራሳችን የጥርስ ሐኪም ለእርስዎ እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትን PDP ካልፈለጉዋቸው የራስዎን PDP መለወጥ ይችላሉ። የእርስዎን PDP ለመቀየር ወደ DentaQuest 1-844-876-7918 ላይ ይደውሉ።
   - Amerigroup የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። የእርስዎ ካርድ የእርስዎን PDP ስም እና የስልክ ቁጥር በላዩ ላይ ይኖርበታል።
2. **በእኛ የመድን ዕቅድ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ ተመዝጋቢ የእርስዎን ልጆች ጨምሮ PDP ይምረጡላቸው።** የእርስዎ PDP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፦
   - የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሕክምና የጥርስ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ሙሉውን ቤተሰብ ማከም ይችላሉ።
3. **የእርስዎን PDP ሲመርጡ፣ እባክዎ፦**
   - እርስዎ ወደ የሚፈልጉት ሆስፒታል ሊልክዎት የሚችል የጥርስ ሐኪምን ይምረጡ። ሁሉም ዶክተሮች ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። የእኛ የአገልግሎት አቅራቢ ማውጫ አንድ PDP ወደ የትኛዎቹ ሆስፒታሎች ሊልክዎት እንደሚችሉ ይዘረዝራል። እገዛ ለማግኘት ወደ የአባል አገልግሎቶችመደወል ይችላሉ።
   - አንዳንድ ጊዜ የመረጡት PDP አዳዲስ ታካሚዎችን ለመቀበል አይችል ይሆናል። ሌላ የጥርስ ሐኪም መምረጥ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እንዲያውቁት እናደርግዎታለን።

## እንዴት የእርስዎን PDP መቀየር እንደሚችሉ

የእርስዎን PDP በማናቸውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአገልግሎት አቅራቢ ማውጫው ላይ አዲስ PDP መምረጥ ብቻ በቂ ነው። አንድ ጊዜ የእርስዎን አዲሱን PDP መርጠው እንደጨረሱ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ። አዲስ PDP መምረጥ ላይ እገዛ ካስፈለግዎት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎት ይችላሉ።

## መደበኛ ሕክምና፣ አስቸኳይ ሕክምና እና ድንገተኛ ሕክምና

### እርስዎ ሊያስፈልግዎት የሚችሉ ሦስት (3) ዓይነት የጤና እንክብካቤዎች አሉ፦ መደበኛ ሕክምና፣ አስቸኳይ ሕክምና ወይም ድንገተኛ ሕክምና።

**መደበኛ ሕክምና** ከእርስዎ PCP የሚያገኙት መደበኛ የጤና ክብካቤ ነው። መደበኛ ክብካቤ በተጨማሪ የእርስዎ PCP እርስዎን ከሚልክዎት ሌሎች ዶክተሮች የሚያገኙት ክብካቤም ነው። መደበኛ ሕክምና የጤና ምርመራዎች፣ አካላዊ እና የጤና በሐኪም መታየቶች እና እንደ የስኳር በሽታ፣ የደም ግፊት እና አስም ለመሳሰሉ የጤና ችግሮች እርስዎ የሚያገኙት ክብካቤ ሊሆን ይችላል። መደበኛ ሕክምና ማግኘት ካስፈለግዎት፣ ወደ የእርስዎ PCP ቢሮ ይደውሉ እና ቀጠሮ እንዲያዝልዎት ይጠይቁ።

**አስቸኳይ ሕክምና** ወዲያውኑ ባይሆንም በ 24 ሰዓት ውስጥ ማግኘት ያለብዎት የሕክምና ክብካቤ ነው። አንዳንድ የአስቸኳይ ሕክምና ችግሮች እነዚህ ናቸው፦

- ማስታወክኑ
- ቀላልወክኑ ባይሆንም በ 24 ሰዓት ውስጥ ማግኘት
- የጆሮወክኑ ባ
- ራስሮወክኑ
- የጉሮሮክኑ ባይ
- የጡንቻክኑ ባይሆንም በ
- ከጡንቻክኑ ባይሆንም በ 24 ሰዓት ውስጥ

**አስቸኳይ እንክብካቤ ካስፈለግዎት፣ ለእርስዎ PCP ቢሮ ይደውሉ።** የእርስዎ PCP ቢሮ ከተዘጋ፣ ቢሮው ሲዘጋ ለስልክ መልስ ለሚሰጠው ሰው መልእክት ይተውለት። በመቀጠል ወደ Nurse HelpLine በስልክ ቍጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ። ወዲያውኑ ወደ ዶክተሩ መሄድ ያሚያስፈልግዎት እንደሆነ ነርሷ ከውሳኔ ላይ ትደርሳለች። ነርሷ እንዴት የሕክምና ክብካቤ እንደሚያገኙ ትነግርዎታለች። ለመደበኛ ወይም ለአስቸኳይ ሕክምና ክብካቤ ወደ ድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም የለብዎትም።

**ድንገተኛ ሕክምና**ለከባድ፣ ድንገተኛ (አንዳንድ ጊዜ ሕይወትን ሊያሰጋ የሚችል) የአካል ጉዳት ወይም በሽታ ወዲያውኑ የሕክምና ክብካቤ የሚያስፈልግዎት የሕክምና ክብካቤ ዓይነት ነው።

- ለመተንፈስድንገተኛ
- ራስንንፈስድ
- በጣምንፈስድንገተኛ
- የደረትፈስድን
- የማይቆምስድንገተኛ (አንዳንድ ጊዜ ሕ
- ኮንቨልዥንድንገተኛ (አንዳንድ ጊዜ ሕይወትን ሊያሰጋ የሚችል) የአካል ጉዳት ወይ

**ድንገተኛ አደጋ ካጋጠምዎት ምን ማድረግ ይችላሉ፦**

1. **ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል (Emergency Room (ER)) ይሂዱ።**
2. **ለ ER የእርስዎን Amerigroup የተመዘጋቢ መታወቂያ ካርድ ያሳዩ።**
3. **በተቻልዎት ፍጥነት የእርስዎ PCP ይደውሉ።**

ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች አስቀድሞ ፍቃድ አያስፈልግም።

# ከከተማ ውጪ ሲሆኑ የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት

## ከከተማ ውጪ ሲሆኑ

ከከተማ ውጭ ሆነው ሳለ በዶክተር መታየት ወይም መድኃኒት ማግኘት ሲያስፈልግዎት የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፡-

**<u>ለመደበኛ ሕክምና፡-</u>** ለእኛ መደወል እና እርስዎ ከከተማ ውጭ ሲሆኑ በዶክተር ወይም በሌላ አገልግሎት አቅራቢ ለመታየት እኛ ለእርስዎ መክፈል እንደምንችል ይጠይቁን ምክንያቱም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያልሆኑ ዶክተሮች የ Amerigroup ተመዝጋቢ ላይሆኑ ይችላሉ። እርስዎ ሕክምናውን ከማግኘትዎ በፊት Amerigroup እሺ ካላለ፣ **ላገኙት የሕክምና እንክብካቤ እርስዎ ራስዎ መክፈል ይኖርብዎታል።** እርስዎ ከከተማ ውጭ እያሉ ከዶክተር መድኃኒት ማግኘት ካለብዎት፣ ለእርስዎ PCP ይደውሉ። እገዛ ካስፈለግዎት ወደ Nurse HelpLine በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

**<u>ለአስቸኳይ ሕክምና፡-</u>** ለእርስዎ PCP ይደውሉ። የእርስዎ PCP ቢሮ ከተዘጋ ወደ Nurse HelpLine (1-800-600-4441) ይደውሉ። ወዲያውኑ ወደ ዶክተሩ መሄድ ያሚያስፈልግዎት እንደሆነ ነርሷ ከውሳኔ ላይ ትደርሳለች። ነርሷ እንዴት የሕክምና ክብካቤ እንደሚያገኙ ልትነግርዎት ትችላለች። ለመደበኛ ወይም ለአስቸኳይ ሕክምና ክብካቤ ወደ ድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም የለብዎትም።

**<u>ለድንገተኛ ሕክምና፡-</u>** የሥነ አእምሮ ጤና፣ አልኮል ወይም ሌላ የአደገኛ መድኃኒት ድንገተኛ ሕክምና ፍላጎትን ጨምሮ ድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠምዎት ወዲያውኑ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል (Emergency Room (ER)) ይሂዱ። ወደ ድንገተኛ ክፍሉ ከሄዱ፣ የ ER ሠራተኞች ወደ የእርስዎ PCP እንዲደውሉልዎት መጠየቅ ይኖርብዎታል። ወደ ድንገተኛ ክፍል ከሄዱ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በተቻልዎት ፍጥነት መደወል ይኖርብዎታል።

## የእርስዎ ልጅ በቤት ውስጥ የማይኖር ከሆነ እና በዶክተር መታየት የሚያስፈልገው ከሆነ እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

## በአውታረ-መረብ ውስጥ ያሉ እና ከአውታረ-መረብ ውጭ ያሉ አገልግሎት አቅራቢዎች

Amerigroup ወደ የእኛ አንዱ ዶክተር ወይም ሌላ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ በሚሄዱበት ጊዜ እርስዎ ላገኙት ክብካቤ ክፍያውን ይከፍላል። እነዚህን ዶክተሮች እና ሌሎች የጤና ክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎችን የእኛ "አውታረ-መረብ" አገልግሎት ሰጪዎች በማለት እንጠራቸዋለን። እነዚህ ሁሉ "በአውታረ-መረብ ውስጥ" ያሉ ዶክተሮች በእርስዎ የአገልግሎት አቅራቢ ማውጫ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። የእኛ ያልሆነ ዶክተር ወይም አገልግሎት አቅራቢ "ከአውታረ-መረብ ውጭ" ያለ አገልግሎት አቅራቢ በመባል ይታወቃል።

ወደ ከ"አውታረ-መረብ ውጭ" ያለ ዶክተር፣ ሆስፒታል ወይም ላብራቶሪ ዘንድ ከሄዱ ለሚያገኙት ክብካቤ ክፍያ መክፈል ሊኖርብዎት ይችል ይሆናል። ለእኛ በመጀመሪያ ከጠየቁን እና ብዙውን ጊዜ በጽሑፍ እኛ ምንም ችግር እንደሌለው ከነገርንዎት መክፈል አይኖርብዎትም። ይህንን "ቅድሚያ ፈቃድ አሰጣጥ" እንለዋለን።

**ቅድሚያ ፈቃድ አሰጣጥ (Prior Authorization (PA)) ማለት ከመደበኛ ሕክምና በላይ የሆነ እንደ በሆስፒታል ተኝቶ መታከም ወይም ቀዶ ጥገና ለመሳሰለ ወይም በ Amerigroup በመደበኛነት ሽፋን የማይሰጠው አገልግሎት የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ፈቃድ ማለት ነው። አገልግሎቱን ከማግኘትዎ በፊት ይህን ፈቃድ መስጫ ማግኘት ይኖርብዎታል። PA ለማግኘት ጥያቄ ለማቅረብ ወደ አባል አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ።**

**የእርስዎ ምርጫ <u>ከአውታረ-መረብ ውጭ</u>. ያሉ እንኳ ቢሆኑም ወደ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ሰጪ መሄድ ይችላሉ። ምንም የቅድሚያ ፈቃድ አያስፈልግም። በቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ገጽ 24 ን ይመልከቱ።**

**ያስታውሱ፦ የAmerigroup አውታረ መረብ ውስጥ ወዳለ አገልግሎት አቅራቢ መሄድ ይኖርብዎታል።**

## ቀጠሮ ማስያዝ

### ከእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ

1. የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ እና እርሳስ እንዲሁም ወረቀት በአጠገብዎ ያዘጋጁ።
2. ወደ የእርስዎ PCP ቢሮ ይደውሉ። የእርስዎን PCP ስልክ ቁጥር ከእርስዎ ተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ላይ ከፊት ይፈልጉት። በተጨማሪ በእርስዎ የአገልግሎት አቅራቢ ስልክ ማውጫ ውስጥ ወይም በሚከተለው አድራሻ መስመር ላይ (ኦንላይን) ማግኘት ይችላሉ፦ www.myamerigroup.com/DC።
3. ለስልኩ መልስ ለሚሰጡት ግለሰብ እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ እንደሆኑ ይንገሩዋቸው። ከእርስዎ PCP ጋር ቀጠሮ ለማስያዝ እንደሚፈልጉ ይንገሩዋቸው።
4. ቀጠሮ ለማስያዝ ለምን እንደሚፈልጉ ለግለሰቡ ይንገሩዋቸው። ለምሳሌ፦
    a. እርስዎ ወይም የቤተሰብ ተመዝጋቢ ታሟል
    b. ራስዎ ላይ ጉዳት አድርሰዋል ወይም አደጋ አጋጥሞታል።
    c. ምርመራ ወይም የክትትል ክብካቤ ያስፈልግዎታል
5. የእርስዎን ቀጠሮ ሰዓት እና ቀን በወረቀት ላይ ይጻፉት።
6. ወደ ቀጠሮዎ ቦታ በሰዓቱ ይሂዱ እና የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ (እና ፎቶ ያለበት መታወቂያ) ከእርስዎ ጋር ይዘው ይሂዱ።
7. ቀጥሮ ለማስያዝ እገዛ ካስፈለግዎት፣ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

**እንደ Amerigroup አዲስ ተመዝጋቢነትዎ፣ ለመጀመሪያው የእርስዎ የጤና ምርመራ በተቻለ ፍጥነት ቀጠሮ ማስያዝ አለብዎት።**

### ቀጠሮን መቀየር ወይም መሰረዝ

ወደ ቀጠሮዎ መምጣት እና ሰዓትን ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው።

- የእርስዎን ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ ከፈለጉ፣ እባክዎ **ከቀጠሮው ሰዓት በፊት ለዶክተሩ ቢያንስ 24 ሰዓት በፊት ይደውሉላቸው።**
- ለአንዳንድ ቀጠሮዎች ለመሰረዝ ከ24 ሰዓትም በፊት ቀደም ብሎ መደወል ያስፈልግዎት ይሆናል።
- በቀጠሮዎ ላይ ሳይገኙ ቢቀሩ ወይም ከዘገዩ የእርስዎ ዶክተር እርስዎ የእሳቸው ታካሚ ሊሆኑ እንደማይችሉ ሊወስኑ ይችላሉ።

### የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ሲዘጋ እንክብካቤ ማግኘት

ቢሮው ሲዘጋ ከእርስዎ PCP ወይም PDP ጋር መነጋገር ካስፈለግዎት፣ ወደ የእርስዎ PCP ወይም PDP ቢሮ ይደውሉ እና ስልኩን መልስ ለሚሰጠው ሰው የእርስዎን ስልክ ቁጥር ጨምሮ መልእክት ይተዉላቸው። የሆነ ሰው በተቻለ ፍጥነት መልሶ ይደውልልዎታል። ወደ Nurse HelpLine 24 ሰዓት በቀን በሚከተለው ስልክ ቁጥር መደወል ይችላሉ፦ 1-800-600-4441። ድንገተኛ ሕክምና ያስፈልገኛል ብለው ካሙኑ ወደ 911 መደወል ወይም ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ ይችላሉ።

### የእርስዎን ዶክተር ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?

የእርስዎ ዶክተር ቢሮ እርስዎ ስልክ ከደወሉ በኋላ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ለእርስዎ ቀጠሮ ቀን መስጠት አለበት። ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ ቀጠሮ ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ እንደሚወስድብዎት ያሳይዎታል። በእነዚህ ጊዜያት ላይ ቀጠሮ ማግኘት ካልቻሉ እባክዎ ወደ 1-800-600-4441 ይደውሉ።

| የጉብኝት ዓይነት | የእርስዎ ሁኔታ | በእርስዎ ዶክተር ለመታየት ምን ያክል ጊዜ እንደሚወስድ |
|---|---|---|
| **አስቸኳይ ጉብኝት** | ጉዳት ደርሶቦታልወይም ታመዋል እና ነገሮች እንዳይባባሱ በ24 ሰዓታት ውስጥ የሕክምና እርዳታ ያስፈልግዎታል ነገር ግን ወዲያውኑ የግድ በዶክተር መታየት የለብዎትም። ቀላል የቃጠሎ አደጋ ወይም ቀላል መቆረጥ፣ ራስ ምታቶች፣ የጉሮሮ ሕመም፣ ወይም የጡንቻ መቆጣት/ወለምታ። | በ24 ሰዓት ውስጥ |
| **መደበኛ ጉብኝት** | ቀላል ሕመም ወይም ጉዳት አጋጥሞታል ወይም መደበኛ ምርመራ ማድረግ ያስፈልግዎታል ነገር ግን አስቸኳይ ቀጠሮ አያስፈልግዎትም። | በ30 ቀናት ውስጥ |
| **የክትትል ጉብኝት** | ከነበረዎት ሕክምና በኋላ እርስዎ በሚገባ እየዳኑ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን በዶክተር መታየት ያስፈልግዎታል። | እንደ ሕክምናው ዓይነት የሚወሰን ሆኖ ከ፤ እስከ 2 ባሉ ሳምንታት ውስጥ |
| **የኀልማሳ የጤናማነት ማረጋገጫ ጉብኝቶች** | • ከአዲስ ዶክተር ጋር የመጀመሪያ ቀጠሮዎ ነው<br>• መደበኛ የኀልማሳ ጤና ምርመራ ማድሪጊያዎ ጊዜ ደርሷል<br>• ለፕሮስቴት ዕጢ፣ ለፔልቪክ (ማህፀን ምርመራ)፣ PAP፣ የካንሰር ምርመራ ወይም የጡት ምርመራ ማድሪጊያ ጊዜዎት ደርሷል | በ30 ቀናት ውስጥ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከዚህም ቀደም ብሎ |
| **ከስፔሺያሊስቶች (በሪፌራል) የሚያዝ አስቸኳይ ያልሆኑ ቀጠሮዎች** | የእርስዎ PCP አስቸኳይ ላልሆነ ሁኔታ በስፔሻሊስት እንዲታዩ ሪፌር ልኮዎታል | በ30 ቀናት ውስጥ |
| **የልጅ EPSDT ምርመራዎች -አስቸኳይ ያልሆነ** | የእርስዎ ልጅ የ EPSDT ምርመራ ማድረጊያ ጊዜው ደርሷል | የመጀመሪያ ምርመራ፡- በ60 ቀናት ውስጥ<br>ተጨማሪ ምርመራዎች፤ ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት መታየት ካሉባቸው ቀናት በ30 ቀናት ውስጥ፤ ዕድሜያቸው ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሕፃናት መታየት ካሉባቸው ቀናት በ60 ቀናት ውስጥ |
| **ስደተኛ ልጆች የጤናማ ሕፃን ምርመራዎች - አስቸኳይ ያልሆነ** | የእርስዎ ልጅ የጤናማ ሕፃን ምርመራ ማድረጊያ ጊዜው ደርሷል | የመጀመሪያ ምርመራ፡- በ60 ቀናት ውስጥ<br>ተጨማሪ ምርመራዎች፤ ዕድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት መታየት ካሉባቸው ቀናት በ30 ቀናት ውስጥ፤ ዕድሜያቸው ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሕፃናት መታየት ካሉባቸው ቀናት በ60 ቀናት ውስጥ |
| **IDEA (በጊዜ ማረቂያ) ምርመራዎች** | የአእምሮ ዕድገት መዘግየት ወይም የአካል ጉዳት ላለባቸው ዕድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት ምርመራዎች (“ግምገማዎች”) | በ30 ቀናት ውስጥ |

## ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች

## የትራንስፖርት አገልግሎቶች

Amerigroup እርስዎ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ወደ ዶክተር ቀጠሮ ለመሄድ የትራንስፖርት አገልግሎትን ያቀርባል።

- በስንት ሰዓት እና በምን ቀን መጥተው እንዲወስዱዎት እንደሚፈልጉ ለመንገር ወደ Medical Transportation Management (MTM) በስልክ ቁጥር 1-888-828-1081 ይደውሉ።
- ትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ከቀጠሮዎ በፊት ቢያንስ 1 ቀን (ቅዳሜ እና እሁድን ሳይጨምር) ቀደም ብለው መደወል አለብዎት። ወደ EPSDT ምርመራዎች ወይም አስቸኳይ ምርመራዎች ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያስፈልግዎት ከሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥዎት ከቀጠሮው አንድ ቀን ቀደም ብለው መደወል ይችላሉ።
- የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶቹ አውቶቡስ፣ ሜትሮ፣ ለታክሲ ክፍያ የሚያገለግሉ የገንዘብ ሰነዶች፣ የተሽከርካሪ ወንበር ሚኒባሶች እና አንቡላንሶች ናቸው። የሚያገኙት የትራንስፖርት አገልግሎት እንደ የእርስዎ የሕክምና ፍላጎት የሚመረኮዝ ይሆናል።
- ለ MTM የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የት መጥተው እንደሚወስድዎት አድራሻ ይስጡዋቸው። በተጨማሪ የሚሄዱበትን የሕክምና/የጥርስ ሕክምና ተቋም ወይም የዶክተር ቢሮ ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር ይስጡዋቸው።

## የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች/መስማት እና ማየት ለተሳናቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች

**የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች እና መስማት እና ማየት ለተሳናቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች <u>ነጻ</u>**

### የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

Amerigroup በሆስፒታል ጨምሮ እርስዎ የሚያስፈልግዎት ከሆነ የአስተርጓሚ አገልግሎትን ያቀርባል።

የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ለማግኘት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር1-800-600-4441 ይደውሉ። የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ከእርስዎ ዶክተር ቀጠሮ በፊት ለእኛ እባክዎ ይደውሉልን።

የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ብዙውን ጊዜ በስልክ አማካይነት ይሰጣሉ። በእርስዎ የዶክተር ቀጠሮ ላይ አስተርጓሚ በአካል እንዲገኝልዎት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ከቀጠሮዎ በፊት ቢያንስ 5 ቀናት ቀደም ብሎ እኛ እንድናውቀው ማድረግ ይኖርብዎታል።

### የትርጉም አገልግሎቶች

መረጃ ከ Amerigroup ካገኙ እና ወደ ሌላ ቋንቋ እንዲተረጎምልዎት የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

### መስማት እና ማየት ለተሳናቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች

መስማት የሚቸገሩ ከሆነ እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 711 ይደውሉ።

ማየት የሚቸገሩ ከሆነ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ። በኦዲዮ ቴፕ፣ በብራይል ወይም በትላልቅ ፊደላት የታተመ ጽሑፍ መረጃውን ልንሰጥዎት እንችላለን።

## የአጠቃቀም አስተዳደር ማስታወቂያ

አንዳንድ ጊዜ እኛ እንዴት ለአንድ የተሰጠ የሕክምና እንክብካቤ እና አገልግሎቶች የመድን ሽፋን እንደምንሰጥ ውሳኔ ላይ መድረስ ያስፈልገናል። ይህ የአጠቃቀም አስተዳደር (UM) በመባል ይታወቃል። የእኛ የ UM ሂደት በብሔራዊ የጥራት ማረጋገጫ ኮሚቴ (National Committee for Quality Assurance (NCQA)) መስፈርቶች ላይ የተመረኮዘ ነው። ሁሉም የ UM ውሳኔዎች በተመዝጋቢው የሕክምና ፍላጎቶች ላይ እና በሚሰጡት ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ብቻ የተመረኮዙ ናቸው። ይህንን የምናደርገው የእኛ ተመዝጋቢዎች የሚቻለውን የተሻለ የጤና ውጤት እንዲያገኙ ለማስቻል ነው። የ Amerigroup ፖሊሲዎች በእኛ የ UM ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ

ከመጠቀም አቅም በታች መጠቀምን አይደግፉም። በ UM ውሳኔዎች ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሐኪሞች ወይም ሌሎች አካላት የጤና ክብካቤን ወይም የመድን ሽፋንን ስለከለከሉ ሽልማት አይሰጣቸውም።

## ወደ አጠቃቀም አስተዳደር ሠራተኞች መዳረሻ

በ UM ፕሮግራም በኩል ባስፈለግዎት ጊዜ ትክክለኛውን እንክብካቤ እንዲያገኙ እናግዝዎታለን። የአጠቃቀም አስተዳደር የሚከተሉትን የሚያካትት ቢሆንም ሆኖም ግን በነዚህ የተገደበ አይደለም፡-

- ቅድመ-አገልግሎት ግምገማ
- አስቸኳይ፣ አብሮ የሚታይ ግምገማ
- ድሕረ-አገልግሎት ግምገማ
- ይግባኝ ጥያቄን ማቅረብ

የእኛየአጠቃቀም ግምገማ ቡድን የአገልግሎት ፈቃድ መስጫ ጥያቄዎችን ይመለከታል። ቡድኑ የሚከተለው ላይ ይወስናል፡-

- አገልግሎቱ ያስፈልጋል
- አገልግሎቱ በእርስዎ የጤና ዕቅድ የመድን ሽፋን አለው

እኛ ለእንክብካቤው አንከፍልም ካልን፣ እርስዎ ወይም የእርስዎ ዶክተር ውሳኔው እንደገና እንዲታይ መጠየቅ ትችላላችሁ። ጥያቄው ከደረሰን በኋላ ለእርስዎ እና ለዶክተርዎ እንዲያውቁት እናደርጋለን። ጥያቄው ለሚከተሉት አገልግሎቶች ሊቀርብ ይችላል፡-

- ላልተፈቀዱ
- በመጠን፣ በአሰጣጥ ጊዜ ገደብ፣ በመጀመሪያ ከተጠየቀው ባነሰ መጠን መሰጠትን የሚያስከትሉ

በጥያቄ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ወይም በደረስዎት ውድቅ ማድረጊያ ላይ ጥያቄዎች ካልዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች ይደውሉ። ከፈለጉ ከእኛ የአጠቃቀም ግምገማ ቡድን ተመዝጋቢዎች አንዱ ከእርስዎ ጋር ሊነጋገር ይችላል።

በተጨማሪ ልዩ እንክብካቤ ማግኘት ላይ ወይም ስለ የእርስዎ ዶክተር ጥያቄዎች ካልዎት ስልክ መደወል ይችላሉ። ወደ 1-800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። እኛን ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ ከጥዋቱ 8 ሰዐት እስከ 6 ከሰዐት. ምሥራቃዊ ሰዓት አቆጣጠር ሊያገኙን ይችላሉ። እርስዎ ከደወሉ እና እኛ ቢሮዎችንን ከዘጋን፣ ደኅንነቱ በሚጠበቅ የድምፅ-ደብዳቤ መልእክት መተው ይችላሉ። በሚቀጥለው የሥራ ቀን ላይ የሆነ ሰው መልሶ ይደውልልዎታል። የሚደውልልዎት ሰው ከ Amerigroup እያደወለልዎት እንደሆነ እና ስም እና ማዕረጉን ለእርስዎ ይነግርዎታል። ከእኛ ጋር የሚጋሩት መረጃ በግል እንደተያዘ ይቆያል እና ማወቅ ከማይገባው ከማንም ሌላ ሰው ጋር አይጋራም።

እንግሊዝኛ ለማይናገሩ ተመዝጋቢዎች፣ በሁሉም ቋንቋዎች በነጻ የቃል የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን እንሰጣለን። እነዚህ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝ ይችላል። ሙሉ በሙሉ መስማት የማይችሉ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት ወደ 711 ይደውሉ።

## ልዩክብካቤእናሪፌራሎች

### ልዩክብካቤእንዴትማግኘትይቻላል

የእርስዎ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP) አብዛኛውን የእርስዎን የጤና ክብካቤ ፍላጎቶች ያስተናግዳሉ ሆኖም ግን ከሌላ ዓይነት አገልግሎት ሰጪዎች እንክብካቤ ሊያስፈልግዎት ይችል ይሆናል። ሌሎች በሕክምና የሚያስፈልጉ እንክብካቤዎችን ከሚሰጡ ከበርካታ የተለያዩ ዓይነት አገልግሎት አቅራቢዎች አገልግሎቶችን እንሰጣለን። እነዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች በሕክምና በአንዱ መስክ ልዩ ሥልጠና የወሰዱ በመሆናቸው ስፔሺያሊስት ይባላሉ።

የስፔሺያሊስቶች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- አለርጂስቶች (የአለርጂ ዶክተሮች)
- ዴርማቶሎጂስቶች (የቆዳ ሐኪሞች)
- ካርዲዮሎጂስቶች (የልብ ሐኪሞች)
- ፖዲያትሪስቶች (የእግር ሐኪሞች)

በእኛ አውታረ-መረብ ውስጥ በሌለ ስፔሺያሊስት መታየት ከፈለጉ ነገር ግን ፈቃድ ካላገኙ እና እኛ ለጉብኝቱ እንደማንከፍል ከተናገርን፣ የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፦

- በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ካለ ሌላ ዶክተር ጋር ቀጠሮ መያዝ እና ሁለተኛ ሐሳብ ማግኘት
- የእኛን ውሳኔ ይግባኝ ማለት (በይግባኝ አጠያየቆች ላይ ገጽ56 ን ይመልከቱ)
- ፍትሐዊ ዳኝነት እንዲሰጥዎት መጠየቅ (ስለ ፍትሐዊ ዳኝነት አሰጣጥ ገጽ 58 ን ይመልከቱ)

## ራስን በራስ ሪፈር ማድረጊያ አገልግሎቶች

ከእርስዎ PCP በቅድሚያ ፈቃድ ሳይገኙ ማግኘት የሚችሉዋቸው የተወሰኑ አገልግሎቶች አሉ። እነዚህም ራስን በራስ ሪፈር ማድረጊያ አገልግሎቶች የሚባሉ ሲሆኑ ከዚህ በታች ምንነታቸው ተዘርዝሯል።

**ለሚከተሉት ሪፌራል አያስፈልግዎትም፦**

- በእርስዎ PCP ለመታየት
- ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥምዎት የሕክምና እንክብካቤ ለማግኘት
- በእርስዎ አውታረ-መረብ ውስጥ ወይም በመከላከያ አገልግሎቶች ላይ ከእርስዎ OB/GYN ዶክተር አገልግሎቶችን ለመቀበል (ሴቶች ብቻ)
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችን ለማግኘት
- በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STIዎች) ለመታከም አገልግሎቶችን ለማግኘት
- ክትባቶችን (ሾትስ) ለማግኘት
- በአውታረ-መረቡ ውስጥ ባለ የዕይታ ሕክምና አገልግሎት አቅራቢ ለመታየት
- የእርስዎን ልጅ በአውታረ-መረቡ ውስጥ ወዳለ የጥርስ ሕክምና አገልግሎት አቅራቢ ይውሰዱት።
- ከአልኮል ወይም ከሌላ አደገኛ መድኃኒቶች ጋር ለተገናኙ ችግሮች የሥነ አእምሮ ጤና ሕክምና ወይም አገልግሎቶችን ያግኙ።

## የሥነ አእምሮ ጤና አገልግሎቶች

የሥነ አእምሮ ጤና አገልግሎቶች ለሁለቱም ለጎልማሶች እና ለሕፃናት ይሰጣሉ። ይህ የጤና ክብካቤ እርስዎ ከደበትዎት ወይም ጭንቀት ውስጥ ከገቡ ወይም ሌላ የሥነ ባሕሪ ጤና ችግሮች ካጋጠምዎት እገዛ ይሰጣል።

**እርስዎ እገዛ ከፈለጉ ወይም በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ ያለ የሆነ ሰው እገዛ ካስፈለገው፣ ወደዚህ አድራሻ ይደውሉ፦**

- የችግሮች ቀጥታ የስልክ መሥመር Amerigroup 1-844-405-4300 (TTY 711)
- የ DC Department of Behavioral Health Hotline በስልክ ቍጥር 1-888-793-4357፣ በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት

## ለአልኮል ወይም ሌላ የአደገኛ መድኃኒቶች ችግሮች አገልግሎቶች

ከአልኮል ወይም ከሌላ አደገኛ መድኃኒቶች ጋር የተገናኙ ችግሮች ለእርስዎ ጤና እንዲሁም በአጠገብዎ ላሉ ሌሎች ሰዎች ጤና አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ለእነዚህ ችግሮች እገዛ ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ወደ ዶክተሩ መሄድ አስፈላጊ ነው። Amerigroup ከአልኮልና ከመርዝ ነጻ የመሆን አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማመቻቸት እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የክብካቤ ማስተባበር ሥራን በመሥራት ሊያግዝዎት ይችላል። ለእነዚህ ችግሮች አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ፦

- ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቍጥር 1-800-600-4441፣ በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት መደወል
- ወደ DBH Assessment and Referral Center (ARC) በቀጥታ በስልክ ቍጥር 202-727-8473 መደወል

ሁሉም የአእምሮ ጤና፣ አልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት አላግባብ መጠቀም አገልግሎቶች ምሥጢራዊ ናቸው።

## የወሊድ ቁጥጥር እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች

**የወሊድ ቁጥጥር እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለመቀበል ሪፌራል አያስፈልግዎትም።**

የወሊድ ቁጥጥር እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ከማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ማግኘት ይችላሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ሪፌራል ማግኘት አያስፈልግዎትም። የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ዶክተር ከእርስዎ PCP ይልቅ ከመረጡ ለእርስዎ PCP ይንገሩዋቸው። የእርስዎ PCP ለእርስዎ የተሻለ እንክብካቤ እንዲያደርጉልዎት ያግዛቸዋል። በወሊድ ቁጥጥር እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከእርስዎ PCP ጋር ይነጋገሩ ወይም ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቍጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

**ሁሉም የወሊድ ቁጥጥር እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች በምሥጢር የሚስተናገዱ ናቸው።**

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**

- የእርግዝና ምርመራዎች
- ለሴቶች እና ለጥንዶች የምክር አገልግሎት
- መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ
- ክትባቶች
- ለሁሉም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ
- ለሁሉም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ሕክምና
- የማምከን ሕክምና (ዕድሜ 21 ወይም ከዚያ በላይ መሆን እና ሕክምናው ከመሰጠቱ በፊት 30 ቀናት ቀደም ብሎ ቅጽ እንዲፈርሙ ያስገድዳል)
- ኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን አያካትቱም፡-**

- የመሃንነት ጥናቶች ወይም ሕክምናዎች
- ለማምከን የሂስቴርክቶሚ ሕክምና
- በፍቃደኝነት ላይ የተመርኮዘ ማምከንን ማክሸፍ
- የኤችአይቪ/ኤድስ ሕክምና
- ፅንስ ማቋረጦች

**ኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት**

ኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡-

- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ካልዎት
- ከእርስዎ PCP
- ከኤችአይቪ ምርመራ እና ምክር አገልግሎት ማእከል

ኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና ምክር አገልግሎት የት መሄድ እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 መደወል ይችላሉ።

የኤችአይቪ ሕክምና ካስፈለግዎት የእርስዎ PCP እርስዎ ክብካቤውን እንዲያገኙ ሊያግዙ ይችላሉ። ወደ የአባል አገልግሎቶች 1-800-600-4441 መደወል ይችላሉ።

## የመድኃኒት መደብር አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች

መድኃኒት መደብሮች የእርስዎን መድኃኒት የሚቀበሉባቸው ቦታዎች ናቸው። የእርስዎ ዶክተር የመድኃኒት ማዘዣ ከሰጥዎት በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ወዳለ መድኃኒት መደብር መሄድ ይኖርብዎታል።

የሁሉንም መድኃኒት መደብር ዝርዝርን በ Amerigroup አውታረ መረብ በእርስዎ የአገልግሎት ሰጪ ስልክ ማውጫ ውስጥ ወይም መሥመር ላይ (ኦንላይን)www.myamerigroup.com/DC ላይ ሊያገኙት ይችላሉ።

ያሉት ከከተማ ውጭ ከሆነ እና ድንገተና ወይም አስቸኳይ ክብካቤ ማግኘት የሚያስፈልግዎት ከሆነ፡-

- ለድንገተኛ አገልግሎቶች፣ ወደ አቅራቢያዎ የሚገኝ የድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል ይሂዱ ወይም ወደ 911 ይደውሉ።
- ለአስቸኳይ ሕክምና፡-
  - ለእርስዎ PCP ይደውሉ። የPCPዎ ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ሊገኙበት የሚችሉትን ስልክ ቁጥር ይተዉ። የእርስዎ PCP ወይም ሌላ እሳቸውን የሚተካ ሐኪም መልሶ ይደውልልዎታል።
  - የእርስዎን PCP ምክር ይከተሉ። በምን ያክል ፍጥነት ክብካቤውን እንደሚያገኙ እና ክብካቤውን የት እንደሚያገኙ ሊነገርዎት ይችላሉ።
  - እገዛ ካስፈለግዎት ወደ Nurse HelpLine በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

**ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚሰጡ መድኃኒቶች**

ለተወሰኑ ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚሰጡ መድኃኒቶች በየሦስት ወሩ እስከ $15 ድረስ ልንሰጥዎት እንችላለን። እነዚህን ትርፍ ጥቅማ ጥቅሞች የሚያገኙት የእርስዎ ዶክተር መድኃኒት ሲጽፍልዎት ነው። የሦስት ወራት ክፍለ ጊዜያቱ በጃንዋሪ፣ ኤፕሪል፣ ጁላይ እና አክቶበር የመጀመሪያው ቀን ላይ ይጀምራሉ። የእርስዎ ፋርማሲስት ለሦስት ወር ክፍለ ጊዜው ወደ $15 ገደቡ እርስዎ ሲደርሱ ይህንኑ እንዲያውቁ ያደርግዎታል።

**በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን ለማግኘት**

- በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ያለን እና ከእርስዎ መሥሪያ ቤት ወይም መኖሪያ ቤት አቅራቢያ ያለን መድኃኒት መደብርን ይምረጡ።
- የሐኪም የመድኃኒት ማዘዣ ሲኖርዎት ወደ መድኃኒት መደብሩ ይሂዱ እና ለፋርማሲስቱ የእርስዎን የመድኃኒት ማዘዣ እና የእርስዎን Amerigroup ተመዝጋቢመታወቂያ ካርድ ይስጡ።
- እገዛ ካስፈለግዎት እባክዎ ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

በእርስዎ Amerigroup የጤና መድን ሽፋን ሥር አብሮ መክፈሎች የሉም።

**ማስታወስ የሚገባዎት ነገሮች፦**

- ለእርስዎ መድኃኒቶች እንዲከፍሉ መጠየቅ የለብዎትም። መድኃኒት መደብሩ ወይም ፋርማሲው ክፍያ እንዲከፍሉ ከጠየቅዎት ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች ይደውሉ።
- አንዳንድ ጊዜ የእርስዎ ዶክተር ከ Amerigroup ለመድኃኒት የቅድሚያ ፈቃድ (PA) ያስፈልጋቸው ይሆናል። የእርስዎ ዶክተር ቅድሚያ ፈቃድ እስከሚያገኙ ድረስ ሲጠብቁ መድኃኒቱን በሚከተሉት ሁኔታዎች የማግኘት መብት ሊኖርዎት ይችል ይሆናል፦
    - እስከ 72 ሰዓታት ወይም
    - በቀን ከአንድ ጊዜ በታች የሚወስዱት ከሆነ ለአንድ ዙር የሚያገለግል መድኃኒት

**የተቆለፈ ፕሮግራም**

የመድን ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶች ወይም ነገሮች ከልክ በላይ እንደተጠቀሙባቸው ተደርጎ የተቆጠሩ ተመዝጋቢዎች ከተመደቡላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዳይደርሱ አገልግሎቶቻቸው ሊቆለፉባቸው ይችላል። በተቆለፈ ፕሮግራም ውስጥ እንዲገቡ ከተደረጉ፣ ይህንኑ እንዲያውቁት ደብዳቤ እንልክልዎታለን። ከፍተኛ ባለሙያዎች ያሉበት ቡድን በትክክለኛው ጊዜ እና በትክክለኛው ቦታ ትክክለኛውን ክብካቤ እንዲያገኙ እርስዎን ያግዝዎታል። የእርስዎ ቡድን የሚከተሉትን ያካትታል፦

- የእርስዎን የሕክምና ክብካቤ ለማስተባበር ተቀዳሚ የክብካቤ አገልግሎት ሰጪ (PCP)
- የእርስዎን በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶችን የሚሰጥ አንድ መድኃኒት መደብር
- በእርስዎ PCP ሊታከም ለማይችል ድንገት የሚፈጠር የሕክምና ፍላጎት ሕክምና የሚሰጥ አንድ ሆስፒታል

በተቆለፈ ፕሮግራም ውስጥ እንዲገቡ ከተደረጉ እና ጥያቄዎች ካልዎት እባክዎ ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቍጥር 1-800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## የበሽታ ቁጥጥር አስተዳደር የተማከለ የእንክብካቤ አሃድ

ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የጤና ችግር ካለብዎት ብቻዎን መቸገር የለብዎትም። የእኛ የበሽታ ቁጥጥር አስተዳደር ፕሮግራም ከሕይወት የተሻለውን ሁሉ እንዲያገኙ ሊያግዝዎት ይችላል። ፕሮግራሙ በበጎ ፈቃድ ላይ የተመረኮዘ፣ በግል እና በእርስዎ ላይ ምንም ወጪ ሳያስከትል የሚሰጥ ነው። የበሽታ ቁጥጥር አስተዳደር የተማከለ የእንክብካቤ አሃድ (Disease Management Centralized Care Unit (DMCCU)) ፕሮግራም በመባል ይታወቃል። ፈቃድ ያላቸው ነርሶች DMCCU በመባል የሚታወቁ የጉዳይ ክትትል ሠራተኞች ስለ የእርስዎ የጤና ችግር ትምህርት ሊሰጥዎት እና የእርስዎን ጤና እንዴት ማስተዳደር እንደሚችሉ ሊያግዝዎት ይችላሉ። የእርስዎ ተቀዳሚ የጤና እንክካቤ ሰጪ (PCP) እና የእኛ DMCCU ቡድን በእነዚህ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ላይ እርስዎን ለማገዝ ዝግጁ ናቸው።

ከነዚህ ሁኔታዎች አንዱ ካልዎት ፕሮግራሙን መቀላቀል ይችላሉ፦

- አስም
- ባይፖላር ዲስኦርደር
- ስር የሰደደ ለመተንፈስ የሚያስቸግር የሳንባ በሽታ (COPD)
- አስጨናቂ የልብ ሥራ ማቆም (CHF)
- የደም ትቦ በሽታ (CAD)
- የስኳር በሽታ
- ኤችአይቪ/ኤድስ
- ደም ግፊት
- ከፍተኛ የድብት ጤና መቃወስ
- ሲዞፍሬኒያ
- የአደገኛ መድኃኒት አላግባብ መጠቀም ችግር

የእኛ የጉዳይ ክትትል ሠራተኞች በክብደት ቁጥጥር እና በሲጋራ ማቆም አገልግሎቶች ላይ ሊያግዝዎት ይችላሉ።

የ DMCCU ጉዳይ ክትትል ሠራተኞች የጤና ግቦችን ለመምታት እና ከግቦቹ ላይ እንዲደርሱ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ እርስዎን ማገዝ ይችላሉ። በፕሮግራሙ ውስጥ እንዳለ ተመዝጋቢ፣ የሚከተለውን የሚያደርግ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ ስለሚኖርዎት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፦

- እርስዎን የሚያዳምጥ እና የእርስዎን የተወሰኑ ፍላጎቶች ለመረዳት ጊዜ የሚሰጥ
- ከእርስዎ የጤና ክብካቤ ግቦች ላይ እንዲደርሱ የጤና ክብካቤ ዕቅድን እንዲያዘጋጁ የሚያግዝ
- የእርስዎን የሕይወት ጥራት ለማሻሻል ሊያግዝዎት የሚችሉ መሣሪያዎችን፣ ድጋፍ እና የማኅበረሰብ ሀብቶችን ለእርስዎ የሚሰጥ
- የተሻለ ምርጫዎችን ማድርግ እንዲችሉ የጤና መረጃ የሚሰጥ
- ከእርስዎ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር የጤና ክብካቤን በማስተባበር ላይ የሚያግዝዎት

በ DMCCU እንደተመዘገበ የ Amerigroup ተመዝጋቢነትዎ የተወሰኑ መብቶች እና ግዴታዎች አሉብዎት።

የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡-

- ስለ Amerigroup መረጃ ማግኘት፤ ይህ ሁሉንም የ Amerigroup ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች እንዲሁም የእኛን ሠራተኞች የትምህርት እና የሥራ ልምድ ያካትታል፤ በተጨማሪ ከሌሎች የንግድ ድርጅቶች ወይም ኤጀንሲዎች ጋር ያለንን የሥራ ውሎችንም ያካትታል
- እኛ የምናቀርበውን ፕሮግራም ወይም አገልግሎት አልቀበልም ማለት ወይም ትቶ መውጣት
- የእርስዎ የጉዳይ ክትትል ሠራተና ማን እንደሆነ ማወቅ እና ሌላ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛን እንዴት መጠየቅ እንደሚቻል ማወቅ
- ከዶክተሮችዎ ጋር ስለጤና እንክብካቤዎ ምርጫ ለመምረጥ Amerigroup እንዲረዳዎ ማድረግ
- ስለ ሁሉም ከ DMCCU-ጋር የተገናኙ ሕክምናዎች ማወቅ፤ እነዚህ ሕክምናዎች በ Amerigroup የመድን ሽፋን ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም በክሊኒክ መመሪያዎች የተጠቀሰውን ማናቸውም ነገር ያካትታሉ፤ ከእርስዎ ዶክተሮች ጋር በሁሉም አማራጮች ላይ ለመነጋገር መብት አልዎት
- በ HIPAA መሠረት የግል እና የጤና መረጃዎችዎ በምሥጢር እንዲጠበቁ ማድረግ፣ መረጃዎን ማግኘት የሚችለው ማን እንደሆነ ማወቅ፣ እና Amerigroup ግላዊነቱ እንዲጠበቅ ምን እንደሚያደርግ ማወቅ
- በ Amerigroup ሠራተኞች በትህትና እና በአክብሮት መስተናገድ
- በ Amerigroup ላይ ቅሬታ ማቅረብ እና ቅሬታ እንዴት እንደሚቀርብ ማወቅ፣ ይህም የAmerigroup ን ተገቢ የቅሬታ መመለሻ ጊዜ እና የጥራት ጉዳዮችን መፍታትን ማወቅን ይጨመራል።
- መረዳት የሚችሉትን መረጃ ማግኘት

የሚከተለውን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡-

- በ Amerigroup የጤና ክብካቤ የሚሰጠውን ምክር መከተል
- አገልግሎታችንን ለመወጣት የሚያስፈልገንን መረጃ ለ Amerigroup መስጠት
- ከ DMCCU ፕሮግራም ለመውጣት ሲፈልጉ ለ Amerigroup እና ለእርስዎ ዶክተር መንገር

ከእነዚህ የጤና ችግሮች ውስጥ አንዱ ካለብዎት ወይም ስለ DMCCU የበለጠ ለማወቅ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ በስልክ ቁጥር

1-888-830-4300 ላይ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጠዋቱ ከጥዋቱ 8:30 እስከ 5:30 ከሰዐትድረስ በአካባቢው ሰዓት አቆጣጠር ይደውሉ። ከ DMCCU የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ ጋር ለመናጋገር ይጠይቁ። ወይም ለእርስዎ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ በቀን ለ 24 ሰዓት የግል መልእክት መተው ይችላሉ። በተጨማሪ የእኛን የድር ጣቢያ www.myamerigroup.com/DC ላይ መጎብኘት ወይም መሥመር ላይ (ኦንላይን) የሚያገኙትን የ DMCCU መረጃ ቅጂ ማግኘት ከፈለጉ ወደ DMCCU ይደውሉ። ስልክ መደወል ለተሻለ ጤና የመጀመሪያ እርምጃዎ ሊሆን ይችላል።

## የሕክምና ማስተባበር እና የጉዳይ ክትትል ፕሮግራሞች

የእርስዎ ልጅ ሥር የሰደደ በሽታ ካለበት ወይም እንደ የስኳር በሽታ፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የአእምሮ በሽታ ወይም አስም፣ ካለበት፣ ለእርስዎ የጤና ክብካቤ ፍላጎቶች ተጨማሪ እገዛ ለመስጠት Amerigroup ልዩ አገልግሎቶችን እና ፕሮግራሞችን ያቀርብልዎታል። እርስዎ ወይም የእርስዎ ልጅ የእናንተን በሽታ ለማስተዳደር እና የእናንተን ጤና ለማሻሻል እንድትችሉ አገልግሎቶችን እና መረጃዎችን እንድታገኙ የሚያግዛችሁ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ ይኖራችኋል።

የ Amerigroup የጉዳይ ክትትክል ሠራተኛ እርስዎን ወይም የእርስዎን ልጅ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ያግዛችኋል፡-

- የመድን ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶችን ማግኘት
- የሕክምና ቀጠሮዎችን እና ምርመራዎችን ማመቻቸት
- የትራንስፖርት አገልግሎትን ማመቻቸት
- ትክክለኛውን አገልግሎት እርስዎ የሚያገኙባቸውን መንገዶች ማግኘት
- ልዩ የጤና ክብካቤ ፍላጎቶች ላይ እና/ወይም ከዕለት ወደ ዕለት ጭንቀትን ለመቅረብ የሚሠሩ ለእርስዎ ክብካቤ ሰጪዎች እገዛ እንዲያገኙ ግብዓቶችን ማግኘት
- ከማኅበረሰብ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት

ለተጨማሪ መረጃ የተመዝጋቢ አገልግሎቶችን ያነጋግሩ። ወደ የእኛ የጉዳይ ክትትል መምሪያ እንልክዎታለን። የእኛ ሠራተኞች ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላሉ። በተጨማሪ ለየትኛዎቹ ፕሮግራሞች እርስዎ አሁን ላይ ተመዝግበው እንዳሉ ያሳውቁዎታል። እንዲሁም ሪፌራል መጠየቅ ወይም ከፕሮግራም እንዲወጡ መጠየቅ ይችላሉ።

እርስዎ በተጨማሪ በዲስትሪክቱ በኩል My DC Health Home ወይም My Health GPS Health Home ለሚባሉ የእንክብካቤ ቅንጅት (የክብካቤ ማስተባበሪያ) ጥቅማ ጥቅም ብቁ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል። Health Home የእርስዎን ሁሉንም የጤና — አካላዊ፣ ሥነ አእምሯዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች መከታተል እንዲችሉ ለማገዝ የተፈጠረ ተጨማሪ የ Medicaid ጥቅም ነው።

My DC Health Home የሚከተሉትን ይሰጣል፡-

- ተቀዳሚ እና የሆስፒታል ጤና አገልግሎቶች
- የአእምሮ ጤና ሕክምና ክትትል
- የንጥረ ነገር አላግባብ መጠቀም ክብካቤ እና
- የረዥም ጊዜ አገልግሎቶች እና ድጋፎች

ከእርስዎ ጋር፣ ከእርስዎ ዶክተሮች፣ ቤተሰብ እና ሌሎች ማናቸውም የእርስዎን የጤና እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች በማስተዳደር ላይ እንዲያግዙ የሚመርጧቸው ሰዎች ጋር አብሮ የሚሠራ እንክብካቤ ሰጪ ቡድንን

በርካታ ሥር የሰደዱ ችግሮች ላሉባቸው ተመዝጋቢዎች በ My Health GPS በኩል እንክብካቤ እና አገልግሎቶችን በማቀናጀት ላይ ያግዛል።

ለ Health Home ጥቅማ ጥቅም ብቁ ከሆኑ ሁሉንም የእርስዎን ፍላጎቶች ለማስተባበር እንዲቻል ለማገዝ Amerigroup ከእርስዎ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ ጋር አብሮ ይሠራል። እነዚህን ነጻ አገልግሎቶች ለመቀበል የሚፈልጉ ከሆኑ ወደ DC Access HELPLINE በስልክ ቁጥር 1-888-7WE-HELP (1-888-793-4357) በቀን ለ 24 ሰዓት፣ በሳምንት ለ 7 ቀናት ከ My DC ወይም My Health GPS Health Home ጋር ለመገናኘት ይደውሉ።

## ጎልማሶች እንዳይታመሙ ለመከላከል የሚሰጡ አገልግሎቶች

Amerigroup ጤናዎትን እንዲጠብቁ ይፈልጋል። በተጨማሪ እኛ ለእርስዎ ለምናቀርባቸው የጤና እና የጤናማነት አገልግሎቶች እንዲመዘገቡ እንፈልጋለን። የጤና እና የጤናማነት አገልግሎቶች ምርመራዎችን፣ የምክር አገልግሎቶችን እና ክትባቶችን ያካትታሉ።

### በሐኪም ለመታየቶች ("ምርመራዎች") የሚሰጡ ምክሮች

ለአጠቃላይ ምርመራ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ እባክዎ ቀጠሮ ያስይዙ እና በእርስዎ PCP ሄደው ይታዩ። በእርስዎ ምርመራ ወቅት ከእርስዎ PCP ጋር መነጋገር ስለሚችሉዋቸው ነገሮች ለመዘጋጀት "በየእርስዎ የጤና ጥቅማ ጥቅማ ጥቅሞች" ክፍል ውስጥ "የጎልማሳ ጤናማነት አገልግሎቶች" ዝርዝርን ይመልከቱ።

**ለአጠቃላይ ምርመራ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ እባክዎ ቀጠሮ ያስይዙ እና በእርስዎ PCP ሄደው ይታዩ።**

### የመከላከያ የምክር አገልግሎት

የመከላከያ የምክር አገልግሎት እርስዎ ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ ማግኘት ይቻላል። በሚከተሉት ላይ የመከላከያ የምክርት አገልግሎትን ማግኘት ይችላሉ፡-

- የአመጋገብ ጥንቃቄ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ
- የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት አጠቃቀም
- ሲጋራ ማጨስን ማቆም
- የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያ
- ለጎልማሳ የሚሰጡ ክትባቶች

ጎልማሳ ከሆኑ አንዳንድ ክትባቶች (ሻቶች) ሊያስፈልግዎት ይችሉ ይሆናል። ከእርስዎ PCP ጋር የትኛዎቹ እንደሚያስፈልግዎት ይነጋገሩ።

## እርግዝና

ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም ነፍሰ ጡር ነኝ ብለው ካሰቡ ወደ የእርስዎ OB/GYN ዶክተር ወዲያውኑ መሄድዎት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህን ቀጠሮ ከማስያዝዎት በፊት በእርስዎ PCP *መታየት**አያስፈልግዎትም።***

ነፍሰጡር ከሆኑ፣ እባክዎ የእርስዎን ነፍሰ ጡርነት ሪፖርት ለማድረግ ወደ የሚከተሉት ይደውሉ፡-

- Economic Security Administration (ESA) በስልክ ቍጥር 202-727-5355
- የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቍጥር 1-800-600-4441
- የእርስዎ PCP

ነፍሰ ጡር ከሆኑ መመርመር ያሉብዎት የተወሰኑ ነገሮች አሉ። እነዚህ ምርመራዎች ጤናማ እርግዝና፣ ወሊድ እና ሕፃን እንዳልዎት እርግጠኛ ለመሆን ያግዛሉ። ይህ የቅድመ ወሊድ ክብካቤ በመባል ይታወቃል። የቅድመ ወሊድ ክብካቤ የእርስዎ ልጅ ከመወለዱ በፊት ያገኛሉ።

**ያስታውሱ፡- ነፍሰጡር ከሆኑ ወይም ነፍሰጡር ነኝ ብለው ካሰቡ አልኮል መጠጥ አይጠጡ፣ አደገኛ መድኃኒት አይጠቀሙ ወይም አያጭሱ።**

# ቅድመ ወሊድ እና ድኅረ ወሊድ ክብካቤ

**ለነፍሰጡር ሴቶች የሚሰጥ ልዩ እንክብካቤ**
Taking Care of Baby and Me® ለሁሉም ነፍሰጡር ተመዝጋቢዎች የሚሰጥ የ Amerigroup ፕሮግራም ነው። ነፍስ ጡር ሲሆኑ በእርስዎን ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ (PCP) ወይም የፅንስ ሐኪም ወይም የማህፀን ሐኪም (OB/GYN) መታየትዎት በጣም አስፈላጊ ነው። እንደዚህ አይነቱ እንክብካቤ **ቅድመ-ወሊድ እንክብካቤ** ይባላል። ጤናማ ልጅ እንዲኖርዎት ያግዛል። የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ ከዚህ በፊት ልጅ ወልደው የነበሩ ቢሆንም እንኳን ዘወትር ጠቃሚ ነው። ከእኛ ፕሮግራም ጋር ተመዝጋቢዎች የጤና መረጃን እና በቅድመ ወሊድ እና ድኅረ ወሊድ ክብካቤ ላይ ስለተሳተፉ ሽልማቶችን ይቀበላሉ።

የእኛ ፕሮግራም የተወሳሰቡ የጤና ክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸውን ነፍሰጡር ተመዝጋቢዎችን በተጨማሪ ያግዛል። ነርስ ጉዳይ ክትትል ሠራተኛ የሚከተሉትን ለመስጠት ከተመዝጋቢዎች ጋር በቅርበት ይሠራሉ፡-

- ትምህርት
- ስሜታዊ ድጋፍ
- የዶክተራቸውን የእንክብካቤ ዕቅድ እንዲከታተሉ እገዛ መስጠት
- እንደ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ WIC፣ የቤት-ጎብኚ ፕሮግራሞች፣ የጡት ማጥባት ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት በመሳሰሉ በእርስዎ ማኅበረሰብ ውስጥ በሉ አገልግሎቶች እና ግብዓቶች ላይ መረጃ

የእኛ ነርሶች በተጨምሪ ከዶክተሮች ጋር ይሠራሉ እና እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች የአገልግሎቶች ተመዝጋቢዎች ጋር ይተጋገዛሉ። ግቡ ለተመዝጋቢዎች የተሻለ ጤናን ለማጠናከር እና ጤናማ የሆኑ ሕፃናት እንዲወለዱ ለማገዝ ነው።

## My Advocate™ ን ማወቅ

በ Amerigroup ውስጥ በእርስዎ እርግዝና ጊዜ በጣም ምርጡን እንክብካቤ ልናደርግልዎት እንፈልጋለን። ለዚህም ነው የ Taking Care of Baby and Me® ፕሮግራም አካል በሆነው በ My Advocate™ ላይ እንዲመዘገቡ የምንጋብዝዎት። My Advocate™ በእርስዎ እርግዝና ወቅት ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ የሚያስፈልግዎትን መረጃ እና ድጋፍ ይሰጥዎታል።

My Advocate™ አስደሳች፣ አጋዥ የነፍሰጡር ነክ የጤና ትምህርትን በስልክ፣ በጽሑፍ መልእክት በስማርት ስልክ ላይ በሚጫን መተግበሪያ ያቀርባል። እርስዎ እንደ ሰው የምታገለግለውን የኮምፒዩተር ሰው Mary Beth፣ My Advocate™ ይተዋወቃሉ። Mary Beth

የእርስዎ ጨቅላ ሕፃን እያደገ እና እየጎለበተ በሄደ ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ከእርስዎ ፍላጎቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ ምላሾችን ትሰጣለች። በሚከተሉት መተማመን ይችላሉ፡-

- ሊጠቀሙበት በሚችሉት ትምህርት
- ጥያቄዎች ወይም ችግሮች ካሉ አድራሻቸው በ My Advocate™ ከሆኑት የእርስዎ ጉዳይ ክትትል ሠራተኛ በሚያገኙዋቸው መልእክቶች ላይ
- ቀላል የመልእክት ልውውጥ ማድረጊያ መርሐግብር
- በእርስዎ ላይ ምንም ወጪ አያስከትልም

ከ My Advocate™ ጋር የእርስዎ መረጃ ደኅንነቱ አስተማማኝ በሆነ እና ግላዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ይቀመጣል። Mary Beth በደወለች ቊጥር የተወለዱበትን ዓመት ምህረት ትጠይቅዎታለች። እባክዎ ለእሷ ከመንገር እንዳያመነቱ። ከትክክለኛው ግለሰብ ጋር መነጋገሯን እርግጠኛ ለመሆን መረጃው ያስፈልጋታል።

**እርስዎን እና የእርስዎን ልጅ ጤናማ እንደሆናችሁ እንድትቆዩ ማገዝ**

የ My Advocate™ የስልክ ጥሪዎች ለእርስዎ ጥያቄዎች መልሶችን እንዲሁም በተጨምሪ ካስፈለግዎት የሕክምና ድጋፍ ይሰጥዎታል። ከቀጣይ ትምህርታዊ የቤት ለቤት ግንኙነት በኋላ አንድ በጣም አስፈላጊ የጤና ምርመራ በስልክ ይደረግልዎታል። ማድረግ የሚኖርብዎት ነገር ቢኖር ማዳመጥ፣ መማር እና ለአንድ ወይም ሁለት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው። የጤና ምርመራውን አንዴ ካጠናቀቁ በኋላ የእርስዎን ትምህርት በስልክ፣ በጽሑፍ ወይም በስማርት ስልክ መተግበሪያ እንዲሆንልዎት መምረጥ ይችላሉ። ችግር እንዳለብዎት ከነገሩን ከጉዳይ ክትትል ሠራተኛ ስልክ ይደወልልዎታል። የ My Advocate™ ትምህርት ርዕሰ ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ቅድመ ወሊድ እና ድኅረ ወሊድ እንክብካቤ
- የጤናማ ሕፃና ክብካቤ
- የጥርስ ጤንነት
- ክትባቶች
- የጤናማ አኗኗር ጠቃሚ ምክሮች

## ነፍሰጡር ሲሆኑ

ነፍሰጡር ነኝ ብለው ካሰቡ፡-

- ወዲያውኑ ወደ የእርስዎ PCP ወይም OB/GYN ዶክተር ይደውሉ። OB/GYN (የማሕጸን ሐኪም) ዶክተር ጋር ለመቅረብ ከእርስዎ PCP ሪፌራል ማግኘት አያስፈልግዎትም።
- OB/GYN በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ማግኘት ላይ እገዛ ካስፈለግዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች ስልክ ይደውሉ።
- ነፍሰጡር እንደሆኑ ሲያውቁ በተጨማሪ ወደ Amerigroup ተመዝጋቢዎች አገልግሎቶች መደወል ይኖርብዎታል።

የነፍሰጡርነት ትምህርት እሽግ እንልክልዎታለን። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፥

- ወደ Taking Care of Baby and Me® ፕሮግራም እንኳን ደህና መጡ የሚል የእንኳን ደስ ያልዎት መግለጫ በራሪ ወረቀት
- ስለ የእርስዎ እርግዝና ለራስ እንክብካቤ ማድረጊያ መረጃን የያዘ መጽሐፍ፤ ይህን መጽሐፍ በተጨማሪ በእርስዎ እርግዝና ወቅት ያጋጠምዎትን ነገሮች ለመጻፍ እንደ ማስታወሻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ
- *Labor, Delivery and Beyond* የሚባል አነስተኛ መጽሐፍ፤ በሦስተኛው ሩብ የእርግዝና ክፍለ ጊዜ ምን ይሆናል ብለው መጠበቅ እንዳለብዎት የሚገልጽ መረጃን የያዘ
- ለቅድመ ወሊድ ክብካቤ የሚሰጥዎትን ሽልማት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያስረዳ መረጃ
- ስለ ፕሮግራሙ እና እንዴት መመዝገብ እንደሚችሉ እንዲሁም በኮምፒዩተር በተደገፈ ድምፅ፣ የጽሑፍ መልእክት ወይም የስማርት ስልክ መተግበሪያ አማካይነት የጤና መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያስረዳ የ My AdvocateTM በራሪ ወረቀት
- *Having a Healthy Baby* ብሮሹር ከጠቃሚ መረጃዎች ጋር

እርጉዝ በሆኑበት ጊዜ ለጤናዎ ጥሩ እንክብካቤ ማድረግ አለብዎ። ለ Medicaid ብቁ ከሆኑ ከWomen, Infants, and Children መርሀግብር (WIC) ጤናማ ምግብ ለማግኘት ይችሉ ይሆናል። የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ለእርስዎ ቅርብ የሆነውን የ WIC ፕሮግራም ስልክ ቊጥር ሊሰጥዎት ይችላል። ለእኛ 1-800-600-4441 (TTY 711) ላይ ይደውሉልን።

ነፍሰጡር ሲሆኑ፣ ወደ የእርስዎ PCP ወይም OB/GYN ቢያንስ በሚከተሉት ጊዜያት መሄድ አለብዎት፥

- ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት በየዐራት ሳምንቱ
- ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ወራት በየሁለት ሳምንቱ
- በመጨረሻው ወር ላይ በየሳምንቱ

የእርስዎ PCP ወይም የማህፀን ሐኪምዎ (OB/GYN) ለእርስዎ ጤና እንደሚያስፈልገው መጠን ከዚህ በላይ እንዲጎበኙዋቸው ሊፈልግብዎት ይችሉ ይሆናል።

## አዲስ ልጅ ሲወልዱ

ልጅዎን ሲወልዱ፣ እርስዎ እና ጨቅላ ሕጻን ልጅዎ ቢያንስ ለሚከተሉት ጊዜያት በሆስፒታል መቆየት አለባችሁ፥

- በብልት በቀጥታ ከተወለደ በኋላ ለ48 ሰዓታት
- በቀላል ቀዶ ጥገና /Cesarean section (C-section)/ ከተወለደ ለ72 ሰዓታት

የእርስዎ PCP ወይም OB/GYN እርስዎና እና የልጅዎ እንክብካቤ ሰጪ ደህና ናችሁ ብለው ካሰቡ፣ ከዚህ ያነሰ ሰዓት ሊቆዩ ይችላሉ። እርስዎ ወይም ልጅዎ ቀደም ብለው ሆስፒሉን ከለቀቁ፣ የርስዎ PCP ወይም OB/GYN በ48 ሰዓታት ውስጥ የቢሮ ወይም የቤት ውስጥ የነርስ ጉብኝት እንዲያደርጉ ሊጠይቅዎ ይችላል።

ልጅ ከወለዱ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርብዎታል፡-

- የእርስዎ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ እንዲያውቁት በተቻልዎት ፍጥነት ለ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች ይደውሉ። ስለ የእርስዎ ልጅ መረጃ ማግኘት እንፈልጋለን።
- ለእርስዎ ልጅ ለ Medicaid ማመልከቻ ለማስገባት ወደ የእርስዎ ESA የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ በስልክ ቁጥር 202-727-5355 ይደውሉ።

## ልጅ ከወለዱ በኋላ

Amerigroup ለእርስዎ የ Taking Care of Baby and Me® የድኅረ ወሊድ ትምህርት እሽግን ልጅ ከወለዱ በኋላ ይልክልዎታል። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፥

- ወደ Taking Care of Baby and Me® ፕሮግራም የድኅረ ወሊድ ክፍል እንኳን ደህና መጡ የሚል የእንኳን ደስ ያልዎት መግለጫ በራሪ ወረቀት
- ስለ የእርስዎ ጨቅላ ሕፃን እንክብካቤ ማድረጊያ መረጃን የያዘ መጽሐፍ፤ ይህን መጽሐፍ በተጨማሪ በእርስዎ ልጅ የመጀመሪያ ዓመት ያጋጠምዎትን ነገሮች ለመጻፍ እንደ ማስታወሻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ
- ለድኅረ ወሊድ ክብካቤ የሚሰጥዎትን ሽልማት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያስረዳ መረጃ
- ስለ ድኅረ ወሊድ የመደበት ስሜት መረጃ የያዘ ብሮሹር
- የቤተሰብ ዕቅድ ማውጣትን የተመለከተ መረጃ የያዘ ብሮሹር

በ My Advocate™ ውስጥ ከተመዘገቡ እና በእርስዎ እርግዝና ወቅት የስልክ ጥሪዎችን ከተቀበሉ፣ ከወለዱ በኋላም እነዚህን ጥሪዎች እስከ 12 ሳምንታት ድረስ እስከ ተመዘገቡ ድረስ ማግኘትዎን ይቀጥላሉ።

ለድኅረ ወሊድ ምርመራ ልጅ ከወለዱ በኋላ በእርስዎ PCP ወይም OB/GYN ለመታየት ቀጠሮ ማስያዝ አስፈላጊ ነው። ደህና የሆኑ እና እየተሻልዎት ያለ ሆኖ ሊሰማዎት ይችላል ነገር ግን ከወሊድ በኋላ ሰውነት ሙሉ በሙሉ እስኪጠገን ድረስ ቢያንስ ስድስት ሳምንታት ያስፈልጉታል።

- ይህ የሕክምና ምርመራ ወይም ጉብኝት ከወለዱ በኋላ ከ 21 እስከ 56 ቀናት ባለው ጊዜያት መካከል መደረግ አለበት።
- የወለዱት በቀላል ቀዶ ጥገና /C-section/ ከሆነ የእርስዎ PCP ወይም OB/GYN ለሁለት ሳምንቱ የድኅረ ቀዶ ጥገና ምርመራ ተመልሰው እንዲመጡ ሊጠይቅዎት ይችላሉ። ይህ እንደ ድኅረ ወሊድ ምርመራ አይቆጠርም። አሁንም ድረስ ከወለዱ በኋላ ለእርስዎ የድኅረ ወሊድ ምርመራ ከ21 እስከ 56 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መሄድ እና በእርስዎ አገልግሎት ሰጪ መታየት አለብዎት።

እርስዎ እንዴት ጤና እየተሰማዎት እንደሆነ ለማወቅ ከእኛ የድኅረ ወሊድ የቤት ለቤት ቡድን የስልክ ጥሪ ሊደርስዎትም ይችላል። ቡድኑ የእርስዎን የ21 እስከ 56 ቀናቱን ድኅረ ወሊድ ምርመራ ከወለዱ በኋላ እንዲያደርጉ ሊያግዝዎት ይችላል። ቡድኑ ለማስታወስም ሊደውል ይችላል።

የእርስዎን ጨቅላ ሕፃን ወደ የእሱ/የእሷ PCP ከተወለደ/ች ከ 2 እስከ 5 ቀናት ውስጥ መልሰው መውሰድዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

# የእርስዎ ልጅ ጤና

## Health Check Program for Children (EPSDT)

Amerigroup የእርስዎ ልጆች ጤናማ ሆኖ እንዲያድግ ለማገዝ ይፈልጋል። የእርስዎ ልጅ በ DC Healthy Families (Medicaid) ፕሮግራም ውስጥ ካለ፣ የእርስዎ ልጅ በ Health Check ወይም በተጨማሪ Early and Periodic Screening, Diagnosis and Treatment (EPSDT) በሚባለው ፕሮግራም ውስጥ ይሆናል። ይህ ፕሮግራም ልክ የእርስዎ ልጅ እንደተወለደ ይጀምር እና የእርስዎ ልጅ ዕድሜው 21 እስከሚሆነው ድረስ ይቆያል። የ Health Check Program ለእርስዎ ልጅ በርካታ አስፈላጊ ምርመራዎችን ያደርጋል።

በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ የ Health Check (EPSDT) መረጃ አለ። የ Health Check (EPSDT) Periodicity Schedule ቅጂ ለማግኘት ተጨማሪ የእርስዎን ዶክተር መጠየቅ፣ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች መደወል ወይም የእኛን የድር ጣቢያ www.myamerigroup.com/DC ን መጎብኘት ይችላሉ። መርሐ ግብሩ የእርስዎ ልጅ መቼ ወደ ዶክተር መሄድ እንዳለበት ይነግርዎታል።

ከ Health Check/EPSDT አገልግሎቶች በተጨማሪ የእርስዎ ልጅ በ "ተመዝጋቢ የጤና ጥቅማጥቅሞች" የሚለው ከዚህ በታች ያለው ክፍል የተዘረዘሩትን ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት ይችላል።

## ስደተኛ ልጆች

የእርስዎ ልጅ በ Immigrant Children's Program ውስጥ ያለ ከሆነ የእርስዎ ልጅ የጤናማ ሕፃን ክብካቤን ያገኛል። ይህ ፕሮግራም የእርስዎ ልጅ ዕድሜው 21 እስኪሆን ይቆያል።

ከጤናማ ሕፃን ክብካቤ በተጨማሪ የእርስዎ ልጅ በ "ተመዝጋቢ የጤና ጥቅማጥቅሞች" የሚለው ከዚህ በታች ያለው ክፍል የተዘረዘሩትን ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት ይችላል። ስደተኛ ልጆች በ Amerigroup ውስጥ ተመዝግበው በሚቆዩበት ጊዜ ለሕክምና አገልግሎቶች ብቻ ብቁ ናቸው።

**ለእነዚህ አገልግሎቶች ምንም ክፍያ መክፈል አይኖርብዎትም – ነጻ ናቸው። ማናቸውም ጥያቄዎች ካልዎት ወይም ትራንስፖርት ለማግኘት ወይም ቀጠሮ ለማስያዝ እገዛ ካስፈለግዎ፣ ወደ አባል አገልግሎቶች በስልክ ቊጥር**

## ለእርስዎ ልጅ ጥርስ ክብካቤ

ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ የ Amerigroup ተመዝጋቢዎች ሁሉም የጥርስ ጤና ምርመራዎች እና ሕክምናዎች ነጻ ናቸው።

የጥርስ ሐኪሞች የጥርስ መበስበስን ሊከላከሉ እና እርስዎን እና የእርስዎን ልጅ እንዴት ለጥርሱ ክብካቤ ማድረግ እንደሚችል ሊያስተምሩ ይችላሉ።

- ከልደት እስከ 3 ዓመት ዕድሜ የእርስዎ ልጅ PCP በመደበኛ ምርመራዎች ወቅት የጥርስ ሕክምና ክብካቤን ሊሰጥ ይችላል። PCPው ወደ የጥርስ ሐኪም ልጁን ለመላክ ሊወስን ይችላል።
- ከ3 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ሁሉም ሕፃናት በየዓመቱ በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ባለ የጥርስ ሐኪም መታየት አለባቸው። በ Amerigroup አገልግሎት አቅራቢ ማውጫ ላይ ወይም መሥመር ላይ (ኦንላይን) www.myamerigroup.com/DC ላይ በአቅራቢያዎ ያለ የጥርስ ሐኪምን ይፈልጉ። ቀጠሮ ለማስያዝ እባክዎ ወደ ጥርስ ሐኪሙ ቢሮ ይደውሉ።

## ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያሉዋቸው ልጆች

ሕፃናት ቋሚ የሆኑ ወይም ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ አካላዊ፣ ሥነ አእምሮዋዊ ዕድገት፣ ሥነ ባሕሪያዊ ወይም የስሜት ችግሮች ካሉባቸው ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች አገልግሎትን ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ ሕፃናት ተጨማሪ የጤና ክብካቤ እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ያስፈልጋቸው ይሆናል።

Amerigroup የእርስዎ ልጅ ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ካሉት የጤና ምርመራ እንዲያደርግ እርስዎን ያነጋግርዎታል። Amerigroup እርስዎን አግኝቶ ካላነጋገርዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቊጥር 1-800-600-4441 እባክዎ ይደውሉ።

- የእርስዎ ልጅ ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ካሉት የእርስዎ ልጅ ስፔሺያሊስት የሆነ PCP እንዲኖረው መብት አለው።
- የእርስዎን ልጅ ልዩ ፍላጎቶች እንዲያግዝ የእርስዎ ልጅ ወደ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ ሊመደብ ይችላል።

- የእርስዎ ልጅ የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ የሕክምና ዕቅድን ለመፍጠር ከእርስዎ እና ከእርስዎ ልጅ ዶክተር ጋር አብሮ ይሠራል።
- የእርስዎ ልጅ የሕክምና ዕቅድ በእርስዎ እና በእርስዎ ልጅ ዶክተር መፈረሙን ያረጋግጡ።
- የሕክምና ዕቅድ ከሌልዎት፣ ለእርስዎ ልጅ የሕክምና ዕቅድን ለመጠየቅ ወደ Amerigroupተመዝጋቢ አገልግሎቶች ይደውሉ።

**ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የአባል አገልግሎቶችን በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441**

## የ IDEA Program

IDEA ማለት Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ) ማለት ነው። IDEA የፌደራል ሕግ ነው። የ IDEA ፕሮግራም የአእምሮ ዕድገት መዘግየት፣ የአካል ጉዳቶች ወይም ልዩ ፍላጎቶች ላሉት የእርስዎ ልጅ ልዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ዕድሜያቸው ከ 3 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በጊዜ ማረቂያ አገልግሎቶችን ከ Amerigroup ያገኛሉ። ዕድሜያቸው 4 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሕፃናት ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ከ D.C. Public School እና Public Charter School ሥርዓቶች ያገኛሉ።

የዲሲ የዕድገት ቻርት (እባክዎ በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ይመልከቱ) የእርስዎ ልጅ በአእምሮ ዕድገት እና አካላዊ ዕድገት ላይ መዘግየት እንዳለበት እርስዎ እንዲያውቁ ሊያግዝዎት ይችላል።

የእርስዎ ልጅ ማደግ እንዳለበት ወይም እንዳለባት እያደገ አይደለም/አይደለችም ብለው የሚያስቡ ከሆነ የእርስዎ ልጅ እንዲመረመር ያድርጉ ("IDEA ምርመራ")። የ IDEA ምርመራ ለማግኘት ወደ የእርስዎ PCP ይደውሉ። የእርስዎ ልጅ የ IDEA አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት ከሆነ የእርስዎ PCP የእርስዎን ልጅ ወደ D.C. Strong Start Early Intervention Program ሪፈር ይልከዋል።

Amerigroup ስለ IDEA እና ሌሎች የእርስዎ ልጅ ሊያገኛቸው ስለሚችላቸው አገልግሎቶች ተጨማሪ ሊነግርዎት የሚችሉ የጉዳይ ክትትል ሠራተኞች አሉት።

Amerigroup የእርስዎ ልጅ በ IDEA ፕሮግራም ውስጥ ከሆነ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ወጪ ይሸፍናል፦

- ዕድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት Amerigroup ምንም እንኳ አገልግሎቱ በእርስዎ ልጅ ትምህርት ቤት የሕክምና ዕቅድ ውስጥ ያለ እንኳ ቢሆን ሁሉንም የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች ወጪን ይሸፍናል።
- ዕድሜያቸው 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሕፃናት Amerigroup፦
  - የእርስዎ ልጅ በትምህርት ቤት በማይሆንበት ጊዜ—በሌሊት፣ በሳምንት መጨረሻ እና በበዓላት እንኳ ሳይቀር የእርስዎ ልጅ ለሚያስፈልጉት በእርስዎ ልጅ የሕክምና ዕቅድ ውስጥ ያሉ የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች እና አገልግሎቶች በሙሉ ወጪያቸውን ይከፍላል።
  - በትምህርት ቤት የሕክምና ዕቅድ ውስጥ የማይሰጡ አገልግሎቶችን ያስተባብራል።

የእርስዎ ልጅ በ IDEA ፕሮግራም በኩል ሊያገኛቸው የሚችላቸውን አገልግሎቶች በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የእርስዎን ልጅ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## ለሕፃናት እና ታዳጊ ወጣቶች ክትባቶች (ሾትስ)

**ክትባቶች (ሾትስ) የእርስዎን ልጅ ጤናማ እንደሆነ ለማቆየት አስፈላጊ ናቸው!**የእርስዎ ልጅ በጣም ትንሽ እያለ በየጥቂት ሳምንታቱ ክትባቶች ያስፈልጉታል። ክትባቶቹ ልደት ላይ ይጀምራሉ። እነዚህ ክትባቶች ከበሽታዎች ጥበቃ ያደርጉላቸዋል። የእርስዎ PCP እና Amerigroup ለእርስዎ ልጅ ክትባቶች ቀጠሮዎችን መርሐ ግብር ያዘጋጃሉ።

የእርስዎን ልጅ ክትባቶች መርሐ ግብር ለማግኘት በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለውን የክፍለ ጊዜ ቻርት ይመልከቱ።

# የእርስዎ ጤና የመድን ሽፋኖች

## በ Amerigroup የመድን ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች

ከዚህ በታች የተሰጠው ዝርዝር ለሁሉም የ Amerigroup ተመዝጋቢዎች የሚሰጡትን የጤና ክብካቤ አገልግሎቶችን እና ጥቅማ ጥቅሞችን ያሳያል። ለአንዳንድ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ዕድሜዎ የተወሰነ ዓመት ላይ ያለ መሆን ወይም ለአገልግሎቱ የተወሰነ ልዩ ፍላጎት ያልዎት መሆን ይኖርብዎታል። Amerigroup በዚህ ዝርዝር ውስጥ ላሉ ለማናቸውም የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች ወደ አውታረ-መረብ አገልግሎት ሰጪ ወይም ሆስፒታል እርስዎ እስከሄዱ ድረስ እርስዎን ክፍያ አያስከፍልዎትም። በእርስዎ Amerigroup የጤና መድን ሽፋን ሥር አብሮ መክፈሎች የሉም። ለአንዳንድ አገልግሎቶች ቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ሊያስፈልግ ይችል ይሆናል።

የተወሰኑ የጤና ክብካቤዎችን Amerigroup የመድን ሽፋን ይሰጥባቸው እንደሆነ በተመለከተ ጥያቄ ካልዎት ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

| ጥቅም | እርስዎ ምን እንደሚያገኙ | ማን ይህን ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| **የጎልማሳ የጤናማነት አገልግሎቶች** | • ክትባቶች<br>• በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለሚተለለፉ በሽታዎች መደበኛ ምርመራ<br>• ኤችአይቪ/ኤድስ በሐኪም መታየት፣ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት<br>• የጡት ካንሰር ምርመራ<br>• የማህፀን ካንሰር ምርመራ (ሴቶች ብቻ)<br>• ኦስቲዮፖሮሲስ ምርመራ (ያረጡ ሴቶች)<br>• ኤችፒቪ ምርመራ<br>• የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ (ወንዶች ብቻ)<br>• የሆድ አኦርቲክ አንዩሪዝም ምርመራ<br>• የቅጥ ያጣ ውፍረት ምርመራ<br>• የስኳር በሽታ ምርመራ<br>• የከፍተኛ ደም ግፊት እና ኮሌስትሮል ምርመራ (የሊፒድ ችግሮች) ምርመራ<br>• የድብት ምርመራ<br>• የትልቁ አንጀትና ፊንጢጣ ካንሰር ምርመራ (ዕድሜያቸው 50 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች)<br>• የሲጋር ማጨስን ማቆም የምክር አገልግሎት<br>• የአመጋገብ ጥንቃቄ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የምክር አገልግሎት<br>• የሥነ አእምሮ ጤና የምክር አገልግሎት<br>• የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት ምርመራ | ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች እንደ ተገቢነቱ |
| **የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት አላግባብ መጠቀም ሕክምና** | ብቁ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች እኛ ክፍያ የምንከፍልባቸው የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት አላግባብ መጠቀም ሕክምና አገልግሎቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ለእነዚህ ሁሉ አገልግሎቶች ለሁሉም ተመዝጋቢዎች አንከፍልም። የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ለማጣራት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ።<br>• ተኝቶ ታካሚ የአልኮል እና የመርዛማ ንጥረ ነገሮች ማስወገድ ሕክምና<br>• ሌሎች የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት አላግባብ መጠቀም ሕክምናዎች በ Addiction, Prevention and Recovery Administration (DBH) ይሰጣሉ<br>• ከ DBH ክብካቤ ማግኘት ላይ እገዛ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| | • ተኝቶ ታካሚ እና ተመላላሽ ታካሚ የንጥረ ነገር አላግባብ መጠቀም ሕክምና<br>• ሌሎች የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት አላግባብ መጠቀም ሕክምናዎች በ Addiction, Prevention and Recovery Administration (DBH) ይሰጣሉ<br>• ከ DBH ክብካቤ ማግኘት ላይ እገዛ | ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅም | እርስዎ ምን እንደሚያገኙ | ማን ይህን ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| **የሕፃን የጤናማነት አገልግሎቶች** | የታመሙ ልጆችን መንከባከብ ባስፈለገ ጊዜ እና ጤናማ የሆኑ ሕፃናትን ጤናማ እንደሆኑ ለማቆየት እንደ የሚከተለው ያለ ምርመራ እና ግምገማን ጨምሮ፡- <br>• የጤና እና የዕድገት ታሪክ እና ምርመራዎች <br>• የአካላዊ እና የአእምሮ ጤና ዕድገት እና ምርመራዎች <br>• አጠቃላይ የጤና ምርመራ <br>• ክትባቶች <br>• በደም ውስጥ ያለ ሊድ ደረጃ ምርመራን ጨምሮ የላብራቶሪ ምርመራዎች <br>• የጤና ትምህርት <br>• የጥርስ ሕክምና ምርመራ አገልግሎቶች <br>• የዕይታ ምርመራ አገልግሎቶች <br>• የመስማት ችሎታ ምርመራ አገልግሎቶች <br>• የአልኮል እና የአደገኛ መድኃኒት ምርመራ እና የምክር አገልግሎት <br>• የሥነ አእምሮ ጤና አገልግሎቶች <br><br>በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጅ የሚሰጡ ማናቸውም የጤና አገልግሎቶችን አያካትትም | ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎች |
| **የጥርስ ሕክምና ጥቅማ ጥቅሞች** | • አጠቃላይ ጥርስ ሕክምና (መደበኛ እና ድንገተኛ ሕክምናን ጨምሮ) እና ኦርቶዶንቲክ እንክብካቤ ለልዩ ችግሮች <br>• ዕድሜያቸው ከ 3 እስከ 20 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት በጥርስ ሐኪም በዓመት ሁለቴ ለሚደረጉ ምርመራዎች <br>• የልጅ PCP ዕድሜያቸው እስከ 3 ዓመት ለሆኑ ልጆች የጥርስ ምርመራን ማድረግ ይችላል <br>• መደበኛ የኦርቶዶንቲክ እንክብካቤን አያካትትም <br>• የፍሎራይድ ቫርኒሽ ሕክምና በዓመት እስከ ዐራት (4) ጊዜ | ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎች (ዕድሜያቸው 21 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች ከ Medicaid የጥርስ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። ለ MCO Dental Help Line በስልክ ቁጥር 1-866-758-6807 ይደውሉ። ) |
| **የጥርስ ሕክምና ጥቅማ ጥቅሞች (ካለፈው የቀጠለ)** | • አጠቃላይ የጥርስ ሕክምና ምርመራዎች እና መደበኛ የማጽዳት አገልግሎቶች በየስድስት (6) ወራቱ <br>• የቀዶ ጥገና አገልግሎቶች እና ጥርስ መንቀል <br>• ድንገተኛ የጥርስ እንክብካቤ <br>• የጥርስ ሙሌት <br>• ራጂዎች (ሙሉ አገልግሎቱ በየሦስት (3) ዓመቱ ለአንድ (1) ጊዜ የተገደበ ነው) <br>• ሙሉ የአፍ ዲብራድመንት <br>• በዓመት ለሁለት (2) ጊዜ የተገደበ ፕሮፓይላክሲስ <br>• የጥርስ የኤክስሬይ ምስል ሲሪስ <br>• የላንቃ ሕክምና <br>• ሴላንት አፕሊኬሽን <br>• ሊወጣ የሚችል ከፊል እና ሙሉ ዴንቸር (አርቴፊሻል ጥርስ) <br>• የጥርስ ካናል ሕክምና ሥር ሕክምና በዓመት እስከ ሁለት (2) መንጋጋዎች <br>• ፔሪዮዶንታል ማስተካከያ እና የሥር ፕላኒግ | ዕድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅም | እርስዎ ምን እንደሚያገኙ | ማን ይህን ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| | • የጥርስ ክራውንስ<br>• የተበላሸ ጥርስን ማስወገድ<br>• ወጪ ገቢ ፕሮቴሲስን ለመጀመሪያ ጊዜ ማስገባት (ማናቸውም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የጎደለ ጥርስን የሚተካ የጥርስ መሣሪያ ወይም ዕቃ፣ ተዛማጅነት ያላቸው ቅርጾች፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ወጪ ገቢ እንዲሆን እና መልሶ እንዲገባ ተደርጎ የተዘጋጀ)፣ በየአምስት (5) ዓመቱ አንድ ጊዜ። አንዳንድ ገደቦች ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ።<br>• ወጪ ገቢ ፓርሺያልስ ፕሮቴሲስ<br>• ማናቸውም ተኝቶ በሆስፒታል መታከም የሚያስፈልገው የጥርስ ሕክምና አገልግሎት በቅድሚያ ፈቃድ (ቅድመ ፈቃድ መስጫ) ማግኘት አለበት<br>• አጠቃላይ አኔዝቴዥየ (ማደንዘዣ) የሚያስፈልጋቸው ኢሌክቲቭ የቀዶ ጥገና ሕክምናዎች | ዕድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች |
| **የኩላሊት እጠባ አገልግሎቶች** | • በሳምንት እስከ 3 ጊዜ ሕክምና (በቀን ለአንድ ጊዜ የተገደበ) | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **Durable Medical Equipment (DME) (ዘለቄታ ያለው የሕክምና መሣሪያ) & Disposable Medical Supplies (DMS) (ጥቅም ላይ ውለው የሚጣሉ መሣሪያዎች)** | • ዘለቄታ ያለው የሕክምና መሣሪያ (Durable medical equipment (DME))<br>• ጥቅም ላይ ውለው የሚጣሉ መሣሪያዎች (Disposable medical supplies (DMS)) | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የድንገተኛ አገልግሎቶች** | • የእርስዎ የጤና ሁነታ በሐኪም በመታየት የሚደረግ ምርመራ፣ ድኅረ- መረጋጋት አገልግሎቶች፣ እና የማረጋጋት አገልግሎቶች  እርስዎ የድንገተኛ አደጋ የሕክምና ችግር ካለበዎት፣ አገልግሎት ሰጪው በ Amerigroup አውታረ-መረብ ውስጥ ሆነም አልሆነም።<br>• ለድንገተኛ ሁኔታዎች ሕክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት** | • የእርግዝና ምርመራ፣ ለሴቶች የምክር አገልግሎት<br>• መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ<br>• ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች የሚሰጥ በፈቃደኝነት ላይ የተመረኮዘ ማምከን ሕክምናዎች (የተፈረመበት የመምከን ፈቃድ መስጫ ቅጽ በተመዝጋቢው ከሕክምናው በፊት 30 ቀናት በፊት ማቅረብ ያስፈልጋል)<br>• ምርመራ፣ ምክር አገልግሎት እና ክትባቶች ለ Human Papilloma Virus- HPV)<br>• ለሁሉም በግብረሥጋ የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ እና የመከላከያ ሕክምና<br><br>ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች የማምከን ሕክምናን አያካትትም | ሁሉም ተመዝጋቢዎች እንደ ተገቢነቱ |
| **የመስማት ችግር ጥቅማጥቅሞች** | • ከመስማት ችግር ጋር ለተያያዙ ሁኔታዎች የመስሚያ መረጃ መሣሪያዎችን እና የመስሚያ መረጃ መሣሪያ ባትሪዎችን ጨምሮ ምርመራ እና ሕክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የቤትውስጥ የጤና አገልግሎቶች** | በቤት ውስጥ የሚሰጡ የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦<br>• ነርሲንግ እና የቤት የጤና ረዳት<br>• የቤት የጤና ረዳት አገልግሎቶች በቤት ጤና ኤጀንሲ የሚቀርቡ ናቸው<br>• የአካል ቴራፒ፣ ኦክፔሽናል ቴራፒ እና የንግግር ፓቶሎጂ እና የኦዲዮሎጂ አገልግሎቶች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ሆስፒስ እንክብካቤ** | • ወደ ሕይወት ዘመናቸው ፍጻሜ እየተቃረቡ ላሉ ሰዎች የድጋፍ አገልግሎቶች | |

| ጥቅም | እርስዎ ምን እንደሚያገኙ | ማን ይህን ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| | | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የሆስፒታል አገልግሎቶች** | • ተመላላሽ ታካሚዎች (መከላከያ፣ ምርመራ፣ ቴራፖቲክ፣ ማገገሚያ ወይም ጽኑ ሕሙማን አገልግሎቶች)<br>• ተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች (በሆስፒታል መቆየት) | ቅድሚያ ፈቃድ ያለው ማናቸውም ተመዝጋቢ ወይም ሕይወትን የሚያሰጋ ድንገተኛ ችግር ያለበት |
| **የላብራቶሪ እና የራጅ አገልግሎቶች** | • የላብራቶሪ ውጤቶች እና ራጂዎች | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **በቤት ውስጥ በነርስ የሚሰጥ ክብካቤ** | • እስከ 30 ተከታታይ ቀናት ድረስ የሙያ ሥልጠናው ባላቸው ነርስ በቤት ውስጥ የሙሉ ጊዜ የሕክምና ክብካቤ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የሥነ አእምሮ ጤና አገልግሎቶች** | ብቁ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች እኛ ክፍያ የምንከፍልባቸው የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ለሁሉም አገልግሎቶች ለሁሉም ተመዝጋቢዎች አንከፍልም። የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ለማጣራት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች 1-800-600-4441 ላይ ይደውሉ<br>• የሚከተሉትን ጨምሮ በአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪ የሚሰጡ አገልግሎቶች፦<br>  ○ የምርመራ እና የግምገማ አገልግሎቶች<br>  ○ የሐኪም እና የአማካይ-ደረጃ ምርመራዎች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦<br>    ▪ የግለሰብ ምክር አገልግሎት<br>    ▪ የቡድን ምክር አገልግሎት<br>    ▪ የቤተሰብ ምክር አገልግሎት<br>    ▪ የ FQHC አገልግሎቶች<br>• መድኃኒት/ሶማቲክ ሕክምና<br>• የችግሮች አገልግሎቶች<br>• ተኝቶ ታካሚ በሆስፒታል የሚሰጥ ሕክምና እና የድንገተኛ መምሪያ አገልግሎቶች<br>• የቀን አገልግሎቶች<br>• የተጠናከረ የቀን ሕክምና<br>• የጉዳይ ክትትል አገልግሎቶች<br>• ዕድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች በአእምሮ ሕመም ተቋም ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች<br>• እርግዝናን ሊያወሳስብ ለሚችል ማናቸውም የአእምሮ ችግር የሚሰጥ ሕክምና<br>• ዕድሜያቸው ከ 22 ዓመት በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች ለሠላሳ (30) ተከታታይ ቀናት የታካሚ Patient psychiatric residential treatment facility services (PTRF) /የታካሚ ሳይካትሪክ ተኝቶ ታካሚ አገልግሎት/<br>• በዓመት በዓላት፣ በትምህርት ቤት ዕረፍት ጊዜዎች ወይም ሕፃኑ በመታመም ምክንያት በትምህርት ቤት በማይሆንባቸው ጊዜያት በ IEP ወይም IFSP ለተካተቱ ሕፃናት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች<br>• ከ DBH የሚከተሉትን አገልግሎቶች ለሚያገኙ ተመዝጋቢዎች የእንክብካቤ ማስተባበር ሥራ፦<br>  ○ በማኅበረሰብ ላይ የተመረኮዙ ማረቂያዎች<br>  ○ ባለብዙ ዘዴ ህክምና(MST)<br>  ○ ተማጓች ማህበረሰብ ህክምና(ACT)<br>  ○ የማኅበረሰብድጋፍ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅም | እርስዎ ምን እንደሚያገኙ | ማን ይህን ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| **የግል እንክብካቤ አገልግሎቶች** | • ለአንድ ተመዝጋቢ አገልግሎቶችን ለመስጠት ብቃት ማረጋገጫ ካለው የግለሰቡ ቤተሰብ ያልሆነ ተመዝጋቢ ብዙውን ጊዜ በቤት ውስጥ የሚሰጡ እና እንደ ተመዝጋቢው የሕክምና ዕቅድ አካል ሆነው በሐኪም የተፈቀዱ አገልግሎቶች<br>• ለዚህ አገልግሎት በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለብዎት | ሁሉም ተመዝጋቢዎች በሆስፒታል ወይም በነርሲንግ ቤት ውስጥ ላሉ ተመዝጋቢዎች አገልግሎቱ አይገኝም |
| **የመድኃኒት መደብር አገልግሎቶች (በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች)** | • በ Amerigroup የመድኃኒት መዘርዝር ላይ የተካተቱ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች። የመድኃኒት መዘርዝሩን www.myamerigroup.com/DC ላይ ወይም ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በመደወል ማግኘት ይችላሉ።<br>• ከአውታረ-መረብ መድኃኒት መደብሮች ብቻ የሚገኙ መድኃኒቶችን ያካትታል። የሚከተሉትንበሐኪምትዕዛዝየማይሰጡ (በቀጥታከመድኃኒትመደብርሊወሰዱየሚችሉ) መድኃኒቶችየሚከተሉትንጨምሮነገርግንበነዚህሳይገደብ፡- በአፍ የሚወሰዱ analgesics ከነጣላ ንቁ ንጥረ ነገሮች ጋር (እንደ አስፕሪን፣ acetaminophen እና ibuprofen)፤ ferrous salts፤ጸረ አሲዶች እስከ ሦስት ከሚደርሱ ንጥረ ነገሮች ጋር (እንደ አልሙኒየም፣ማግኒዝየም እና bismuth)፤የስኳር መድኃኒቶች (እንደ ኢንሱሊን እና መርፌ)፤ የሕፃናት ሕክምና፣ ቅደመ ወሊድ፣ geriatric ቪታሚን ፎርሙሌሽኖች፣ የቤተሰብ ምጣኔ መድኃኒቶች እና አቅርቦቶች (ድንገተኛ ወሊድ መከላከያ፣ ኮንደም/ዲያፍራም) እና Senna ኤክስትራክትበቀጥታከመድኃኒትመደብርየሚወሰዱመድኃኒቶችንለማግኘትከእርስዎዶክተርየሐኪም መድኃኒትማዘዣመያዝይኖርብዎታል። ሙሉውዝርዝርበድርጣቢያውላይወይምወደተመዝጋቢአገልግሎቶችበመደወልማግኘትይቻላል። | ሁሉም ከሁለቱ ብቁ (Medicaid/Medicare) የሆኑ ተመዝጋቢዎች በቀር የሐኪም መድኃኒት ማዘዣቸው በ Medicare ክፍል መ ወጪው የሚሸፈን |
| **ፖዲያትሪ** | • ለእግር ችግሮች ልዩ እንክብካቤ<br>• በሕክምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መደበኛ የእግር እንክብካቤ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ተቀዳሚ እንክብካቤ አገልግሎቶች** | • መከላከያ፣ ከባድ እና ሥር የሰደዱ የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች በአጠቃላይ በእርስዎ PCP የሚሰጡ ናቸው | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ፕሮስቴቲክ መሣሪያዎች** | • ፈቃድ ባለው አገልግሎት ሰጪ በሚታዘዘው መሠረት ምትክ ማግኘት፣ ማስተካከያ ማስደረግ ወይም ደጋፊ መሣሪያ ማግኘት | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **ማገገሚያ አገልግሎቶች** | • አካላዊ፣ የንግግር እና ኦክፔሽናል ቴራፒን ጨምሮ | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የስፔሺያሊስት አገልግሎቶች** | • በልዩ ሁኔታ የሠለጠኑ ዶክተሮች ወይም የላቁ አካሚ ነርሶች አማካይነት የሚሰጡ የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች<br>• በቀዶ ጥገና ወይም በበሽታ ምክንያት፣ በአደጋ ጉዳት ወይም በተላላፊ በሽታ የመጣ የሰውነት ቅርጽ መበላሻት ወይም የእርስዎን ሰውነት መደበኛ ተግባር የሚያውክ ችግር ካልሆነ በቀር የውበት ማስተካከያ የሕክምና አገልግሎቶችን እና ቀዶ ጥገናዎችን አይሸፍንም | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | • ከሕክምና ቀጠሮዎች ወይም ወደ ቀጠሮዎቹ የትራንስፖርት አገልግሎት | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የእይታ እንክብካቤ** | • የዓይን ምርመራዎች ቢያንስ አንድ ጊዜ በየዓመቱ እና እንደ አስፈላጊነቱ፤ እና የዓይን መነጽር (ማስተካከያ ሌንሶች) እንደ አስፈላጊነቱ | ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

| ጥቅም | እርስዎ ምን እንደሚያገኙ | ማን ይህን ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ይችላል |
|---|---|---|
| | • ተመዝጋቢ መነጽሩ ወይም መነጽሯ ካልጠፋባት በቀር በየሁለት (2) ዓመቱ አንድ የዓይን መነጽር ወይም የሐኪም ማዘዣው ከ0.5 ዲዮፕተር በላይ ከተለወጠ | ዕድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመዝጋቢዎች |

## እኛ የማንከፍልባቸው አገልግሎቶች

- በአብዛኛው ሁኔታ ለውበት የሚደረጉ ቀዶ ጥገናዎች
- የሙከራ ወይም የምርምር አገልግሎቶች፣ ቀዶ ጥገናዎች፣ ሕክምናዎች እና መድኃኒቶች በአብዛኛው ሁኔታ
- በክሊኒክ ደረጃ የሙከራ ፕሮቶኮል አካል ለሆኑ አገልግሎቶች በአብዛኛው ሁኔታ
- ፅንስ ማቋረጥ፣ ወይም በፈቃደኝነት የሚደረግ የፅንስ ማቋረጥ፣ በፌደራል ሕግ ያልተጠየቀ
- የመካንነት ሕክምና
- ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች የሚደረግ የማምከን ሕክምናዎች
- በሕክምና አስፈላጊ ላልሆኑ አገልግሎቶች

## አዳዲስ የሕክምና ቴክኖሎጂዎች

አዳዲስ ዘመናዊ ሕክምናዎችን እንገመግማለን። የ PCPዎች፣ ስፔሻሊስቶች፣ እና ሜዲካል ዳይሬክተሮች ቡድን ሕክምናውን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላቱን ያረጋግጣል፦

- በመንግሥት የተፈቀደ መሆኑን
- በታካሚዎች ላይ የሚያሳድረ ተጽዕኖ አዎንታዊ መሆኑን የሚያሳይ አስተማማኝ ጥናት እንዳለ ማሳየቱን
- አሁን ከምንጠቀምባቸው ሕክምናዎች ባላነሰ ወይም በበለጠ ታካሚዎችን ማገዝ ይችላል
- የታካሚን ጤና ያሻሽላል

የእርስዎ ዶክተር እኛን የግምገማ ቡድኑ እስካሁን ያልተመለከተውን ሕክምና በተመለከተ ጥያቄ ካቀረበልን ቡዱኑ ስለህክምናው ምርመራ በማድረግ ውሳኔን ይሰጣል።በእርስዎ ጤና ላይ ስጋትን የማያስከትል ሆኖም ግን ከባድ ወይም አፋጣኝ የሆነ ሕክምና እንዲሰጥዎት ጥያቄ ካቀረቡ ቡድኑ የእርስዎ ጥያቄ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ይሰጣል።ውሳኔው በእርስዎ የጤና ሁኔታ ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል።ከባድ ሕመምን፣ የሕይወት መጥፋትን፣ የአካል መጉደልን ወይም ዋንኛ የሰውነት ክፍለ አካልን ከጥቅም ውጭ መሆንን ሊያስከትል ከሚችል ከባድ ወይም አፋጣኝ ስጋት ጋር ግንኙነት ያለው ጥያቄ ከሆነ ቡድኑ የእርስዎ  ጥያቄ በደረሰው በ72 ሰዓታት ውስጥ ለጥያቄዎ ምላሽ ያገኛሉ። ውሳኔው በእርስዎ የጤና ሁኔታ ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል።ቡድኑ ምን እንደወሰነ የሚነግርዎት ደብዳቤ እንልክልዎታን።ለእርስዎ ዶክተር በደብዳቤ ወይም በፋክስ እንነግራቸዋለን። ማስታወቂያው ቡድኑ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በአንድ ቀን ውስጥ ይላካል።በተሰጠው ውሳኔ ላይ ከቡድኑ ጋር የማይስማሙ ከሆነ፣ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።

## ሌላ አስፈላጊ መረጃ

### አድራሻዬን ብቀይር ምን አደርጋለሁ

- ወደ District of Columbia (DC) Economic Security Administration (ESA) Change Center በስልክ ቁጥር 202-727-5355 ይደውሉ።
- ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በዚህ ቁጥር ይደውሉ 1-800-600-4441

### ልጅ ብወልድ ምን ማድረግ አለብኝ

- ወደ DC Economic Security Administration (ESA) Change Center በስልክ ቁጥር 202-727-5355 ይደውሉ።
- ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በዚህ ቁጥር ይደውሉ 1-800-600-4441

### ልጅ በጉዲፈቻ ባሳድግ ምን ማድረግ አለብኝ

- ወደ DC Economic Security Administration (ESA) Change Center በስልክ ቁጥር 202-727-5355 ይደውሉ።

### በእኔ ቤተሰብ ውስጥ ሰው ቢሞት ምን ማድረግ አለብኝ

- ወደ DC Economic Security Administration (ESA) Change Center በስልክ ቁጥር 202-727-5355 ይደውሉ።
- ወደ Amerigroup ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በዚህ ቁጥር ይደውሉ 1-800-600-4441

## እንዴት የእኔን MCO መቀየር እችላለሁ

**የእርስዎን MCO በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ጥሩ ምክንያት ሲኖርዎት በማናቸውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ።**

- የእርስዎ ምዝገባ ዓመት ከሚሞላበት ቀን —እርስዎ መጀመሪያ Amerigroup የተቀላቀሉበት ወር እና ቀን 90 ቀናት ቀደም ብለው የእርስዎን MCO አንድ ጊዜ በዓመት መቀየር ይችላሉ።
- DC Healthy Families የእርስዎ ምዝገባ ዓመታዊ ቀን ከመድረሱ ሁለት ወራት ቀደም ብሎ ደብዳቤ ይልክልዎታል። ደብዳቤው እንዴት MCOዎችን መቀየር እንደሚችሉ ይነግርዎታል።

**የእርስዎን MCO በበቂ ምክንያት መቀየር**
**በቂ ምክንያት ካልዎት የእርስዎን MCO በመጀመሪያዎቹ 90 ቀናት ለመቀየር መብት አልዎት። የበቂ ምክንያት ምሳሌዎች ደካማ ጥራት ያለው እንክብካቤ እና እርስዎ በሚፈልጉዋቸው አገልግሎት አቅራቢዎች አለመታየት ናቸው። የእርስዎን MCOዎች መቀየር የሚፈልጉ ከሆነ ወደ DC Healthy Families በስልክ ቊጥር**

የሚከተሉትን ካደረጉ ከዚያ ጊዜ በኋላ ከ Amerigroup የጤና ክብካቤ እንዲያገኙ አይፈቀድልዎትም።

- የእርስዎን የ Medicaid ብቁነት መብት ማጣት
- የማኅበራዊ ዋስትና ገቢ (Social Security Income (SSI)) ብቁነት መኖር

ሕፃኑ በሚከተሉት ሁኔታ ከ Amerigroup ይወገዳል፦

- በዲስትሪክቱ ጥበቃ ሥራ ከሆነ

**የዲሲ መንግሥት በሚከተሉት ሁኔታዎች ከ Amerigroup እርስዎን ሊያስወግዶት ይችላል፦**

- የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት መፍቀድ፤
- ዲስትሪክቱ እርስዎ የ Medicaid ማጭበርበር ድርጊት እንደፈጸሙ ሲያውቅ፤ ወይም
- የእርስዎን የተመዝጋቢ ኃላፊነቶች ሳይወጡ ከቀሩ።

## በመድን ሽፋን ላለው አገልግሎት ክፍያ ብጠየቅስ ምን አደርጋለሁ

ከላይ በተሰጠው ዝርዝር ውስጥ የመድን ሽፋን ላለው አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቢል ከደረስዎት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቊጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

## የመድን ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ክፍያን መክፈል

- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት እንደሚያስፈልግዎት ከወሰኑ እና አገልግሎቱን ለማግኘት ከ Amerigroup በጽሑፍ የተሰጠ ፈቃድ ከሌልዎት ለአገልግሎቱ እርስዎ ራስዎ መክፈል አለብዎት።
- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት እንደሚያስፈልግዎት ከወሰኑ እና አገልግሎቱን ለማግኘት ለአገልግሎቱ እርስዎ ራስዎ እንደሚከፍሉ የሚያረጋግጥ የእምነት ቃል መግለጫ ሰነድ መፈረም አለብዎት።
- አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ ***በፊት*** ሁልጊዜ የእርስዎን የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ማሳየት እና ለዶክተሮች እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ መሆንዎትን መንገር እንዳለብዎት ያስታውሱ።

*የላቀ መመሪያ*

**የላቀ መመሪያ**የእርስዎን የጤና ክብካቤ ምርጫዎች ሌሎች እንዲያውቁ የሚፈርሙት ሕጋዊ ሰነድ ነው። እርስዎ ስለ ራስዎ መናገር በማይችሉበት ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል። አንዳንድ ጊዜ ይህ "**የቁም ኑዛዜ**" ወይም "**ጸንቶ የሚቆይ የውክልና ሥልጣን**" በመባል ይታወቃል።

የላቀ መመሪያ ስለ የእርስዎ የሕክምና እንክብካቤ እንደ እርስዎ ሆኖ አንድ ሰው ምርጫዎችን እንዲያደርግ እንዲመርጡ ያስችልዎታል።

የላቀ መመሪያ በተጨማሪ እርስዎ የሚፈልጉትን ለመናገር አቅም እስከሚያጡ ደረጃ ከታመሙ ምን ዓይነት ሕክምና እንደሚፈልጉ እንዲናገሩ ያስችልዎታል።

- ስለ የላቀ መመሪያ ከእርስዎ ቤተሰብ፣ የእርስዎ PCP እና ሌሎች እንዲህ በመሰሉ ነገሮች ሊያግዝዎት ከሚችሉ ሰዎች ጋር መነጋገር አስፈላጊ ነው።

የላቀ መመሪያን መሙላት እና መፈረም ከፈለጉ፣ በሚቀጥለው የእርስዎ ቀጠሮ ላይ የእርስዎን PCP እንዲያግዝዎት ይጠይቁት ወይም ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ እና ያግዝዎታል።

## ሌላ ኢንሹራንስ ቢኖረኝ ምን አደርጋለሁ

የ Amerigroup ተመዝጋቢ ከሆኑ እና ለ Medicaid ብቁ ከሆኑ ሌላ የጤና ኢንሹራንስ ካልዎት ለእኛ ወዲያውኑ መንገር አለብዎት። እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

## ሁለቱም Medicaid እና Medicare ካሉኝ ምን አደርጋለሁ

እርስዎ Medicare እና Medicaid ካልዎት የ Medicare አገልግሎት ሰጪዎችን መምረጥ እንዲችሉ እባክዎ ለ Amerigroup ይንገሩ። እርስዎ Medicare ካልዎት ለእርስዎ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች ለ Medicare ክፍል መ መመዝገብ አለብዎት። Medicaid የእርስዎን የአብሮ ከፋይ ወጪን ይከፍላል። ለተጨማሪ መረጃ የዚህን አነስተኛ መጽሐፍ ገጽ 54 ይመልከቱ።

## ማጭበርበር ድርጊት

ማጭበርበር ከባድ ጉዳይ ነው። ማጭበርበር ምንድን ነው? ማጭበርበር ማለት የሐሰት ቃል ወይም ተጨባጭ የሰነድ እውነታዎችን አንዳንድ ጥቅሞችን ወይም ክፍያዎችን ያለአግባብ ለማግኘት ሲባል የመስጠት እና የማቅረብ ድርጊት ነው። የተመዝጋቢዎች የማጭበርበር ድርጊት ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ድንበር ውጭ እየኖሩ ሳሉ በዲስትሪክቱ ውስጥ እንደሚኖሩ አድርጎ በውሸት መናገር ነው። የአገልግሎት ሰጪዎች የማጭበርበር ድርጊት ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ላልተሰጡ አገልግሎቶች እና/ወይም ዕቃዎች የአገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቢል መስጠት ነው።

የማጭበርበር ድርጊት እንዳለ ከተጠራጠሩ፣ እባክዎ እኛ እንድናውቀው ያድርጉ። የራስዎን ማንነት መግለጽ ወይም የእርስዎን ስም መስጠት አያስፈልግም። ምን ተግባራት እንደ ማጭበርበር ድርጊት ሊቆጠሩ እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ፣ የ Amerigroup ድርጣቢያን www.myamerigroup.com/DC ላይ ይጎብኙ። የማጭበርበር ድርጊትን ሪፖርት ለማድረግ ወደ Amerigroup Compliance Hotline **1-877-660-7890** ወይም ወደ DC Department of Health Care Finance's Fraud Hotline በስልክ ቁጥር **1-877-632-2873** ይደውሉ።

## የሐኪም (ዶክተር) ማበረታቻ ዕቅድ ይፋ ማድረጊያ

**እርስዎ Amerigroup ልዩ የሆነ ገንዘብ ነክ ስምምነት ከ Amerigroup ዶክተሮች ጋር እንዳለው የማወቅ መብት አልዎት።**

ይህን መረጃ ለማግኘት ወደAmerigroup የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቁጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ።

# ቅሬታዎች፣ ይግባኝ ጥያቄዎች እና ፍትሐዊ ዳኝነት

Amerigroup እና የዲስትሪክቱ መንግሥት ሁለቱም እርስዎ ስለሚያገኙት እንክብካቤ ወይም Amerigroup ለእርስዎ ስለሚቀርብልዎት አገልግሎቶች ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉባቸው መንገዶች አሉዋቸው። ከዚህ በታች እንደተብራራው እንዴት ቅሬታን እንደሚያቀርቡ መምረጥ ይችላሉ።

## ቅሬታዎች

- በእርስዎ ላይ ባጋጠመ ነገር ደስተኛ ካልሆኑ ቅሬታን ማቅረብ ይችላሉ። ቅሬታ ሊያቀርቡ የሚችሉባቸው ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-
    - በአክብሮት እንዳልተስተናገዱ ሆኖ ከተሰማዎት
    - እርስዎ ባገኙት የጤና እንክብካቤ አልረኩም
    - ቀጠሮ ለማግኘት ከልክ በላይ ጊዜ ወስዷል
- ቅሬታን ለማቅረብ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቍጥር **1-800-600-4441** መደወል ይኖርብዎታል።
- የእርስዎ ዶክተር በተጨማሪ ለእርስዎ ቅሬታ ሊያስገባልዎት ይችላል።

**ደስተኛ ካልሆኑበት ክስተት በኋላ በማናቸውም ጊዜ ቅሬታዎን ማስገባት ይችላሉ።** Amerigroup የእርስዎ ቅሬታ ከደረሰው በኋላ በጉዳዩ ላይ ሙሉ ጥናት ያደርጋል። አብዛኛውን ጊዜ በ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔያችንን እናሳውቅዎታለን፣ ሆኖም ግን ውሳኔ ለእርስዎ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜ ልንጠይቅዎት እንችላለን። የእኛን ውሳኔ ከ 90 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እናሳውቅዎታለን።

## ይግባኝ ጥያቄዎች እና ፍትሐዊ ዳኝነት

የእርስዎ ጥቅማ ጥቅሞች ፍትሐዊ ባልሆነ መልኩ እንደተከለከሉ፣ እንደተቀነሱ፣ እንደዘገዩ ወይም እንደተቋረጡ ካመኑ **ይግባኝ** ወደ Amerigroup ማስገባት እና የዲሲ አስተዳደራዊ ፍትሐዊ ዳኝነት "ፍትሐዊ ችሎት" እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

- ወደ Amerigroup ይግባኝ ለማስገባት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በዚህ ስልክ ቍጥር ይደውሉ፡- 1-800-600-4441
- ፍትሐዊ ችሎት እንዲቆምልዎት ለመጠየቅ ወደ ዲስትሪክት መንግሥት በሚከተለው አድራሻ ላይ ይደውሉ ወይም ይጻፉ፡-
- ፍትሀዊ ዳኝነት ከመጠየቅዎ በፊት በ[Amerigroup] የይግባኝ ሂደት ማለፍ ይኖርብዎታል።

District of Columbia Office of Administrative Hearings
Clerk of the Court
441 4th Street, NW
N450
Washington, DC 20001
የስልክ ቁጥር፡- 202-442-9094

- ቀነ ገደቦች
    - የ Amerigroup የከባድ ውሳኔ እርምጃ ማስታወቂያ በደረሰዎት በ60 የቀን መቍጠሪያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ጥያቄ ማስገባት አለብዎት።
    - ወደ Amerigroup ያስገቡት ይግባኝ ጥያቄ በይደር እንዲቆይ ከተደረገ፣ የእርስዎ ይግባኝ ጥያቄ በይደር ስለመታለፉ የሚገልጽ ደብዳቤ በደረሰዎት በ120 ቀናት ውስጥ የፍታሐዊ ዳኝነት ችሎት እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ።
    - የእርስዎ የፍትሐዊ ዳኝነት ችሎት ጥያቄ ወይም ይግባኝ በሂደት ላይ እያለ ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበልዎትን መቀጠል ከፈለጉ የፍትሐዊ ዳኝነት ችሎቱን ወይም ይግባኙን ከሚከተሉት በኋላ መጠየቅ ይኖርብዎታል፡-
        - ከ Amerigroup የእርምጃ ማስታወቂያ የፖስታ ቤት ማኅተም ላይ ካለው ቀን በ 10 ቀናት ውስጥ ወይም
        - በ Amerigroup የቀረበው መፍትሔ ሐሳብ ወይም እርምጃ ተፈጻሚ መሆን የሚጀምርበት ቀን (ወይም በሌላ አነጋገር ጥቅማ ጥቅሙ ከሚቆምበት ጊዜ ጀምሮ)።

## ይግባኞች

የእርስዎን ይግባኝ በስልክ ደውለው መጀመር ይችላሉ፣ ሆኖም ግን ይህንኑ በጽሑፍ ቀጥለው ማስገባት ይኖርብዎታል። ይግባኝ ጥያቄውን እና ማናቸውም የእርስዎን ይግባኝ ጥያቄ የሚደግፉ ሰነዶችን ወደ የሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ፡-

Amerigroup District of Columbia Medical Appeals Department
7550 Teague Road
Ste. 500
Hanover, MD 21076

የእርምጃ ማስታወቂያ በደረስዎት 60 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ይኖርብዎታል።

የእርስዎ ይግባኝ ጥያቄ በደረሰን በ 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ በእርስዎ ይግባኝ ላይ ውሳኔ እንሰጣለን።
በእርስዎ ይግባኝ ላይ መረጃ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገዎት እና ዲስትሪክቱ ይህ ለእርስዎ የተሻለ እንደሆነ ከወሰነ ወይም እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ ተጨማሪ ጊዜ ከጠየቃችሁ Amerigroup ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገውን ጊዜ በ 14 ቀን መቁጠሪያ ቀናት ሊጨምረው ይችላል። ተጨማሪ ጊዜ የምንጠይቅ ከሆንን የጽሑፍ ማስታወቂያ እንልክልዎታለን።

በእርስዎ ይግባኝ ጥያቄ ላይ የእኛን ውሳኔ ምን እንደሆነ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ እንልክልዎታለን።

በእርስዎ ይግባኝ ላይ Amerigroup በሰጠው ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ ፍትሐዊ ዳኝነት ችሎት እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ። የእርስዎ አገልግሎቶች ከተጀመሩ እና በፍትሐዊ ዳኝነት ችሎት ክርክሩ ሂደት ላይ የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘትዎን መቀጠል ከፈለጉ ከ Amerigroup የእርምጃ ማስታወቂያ የፖስታ ቤት ማኅተም ላይ ካለው ቀን በ 10 ቀናት ውስጥ ፍትሐዊ ዳኝነት ችሎት እንዲቆም መጠየቅ ይኖርብዎታል።

## የተፋጠነ (አጣዳፊ) የቅሬታዎች እና ይግባኝ ጥያቄዎች ማስተናገድ ሂደት

የእርስዎ ይግባኝ እንደ አጣዳፊ እንዲታይ ከተወሰነ Amerigroup በ 72 ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል። አንድ ይግባኝ አጣዳፊ ተብሎ የሚቆጠረው አንድን ይግባኝ ለማስተናገድ የሚወስደው መደበኛው የመጠበቂያ የ 30 ቀናት ጊዜ ለእርስዎ ጎጂ ከሆነ ነው። [አጣዳፊ ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉ ይግባኞች ምሳሌ የሚያካትተው፣]

- አስቸኳይ እንክብካቤ
- ለህይወት አስኪ የሆኑ ሁኔታዎች ላይ እንክብካቤ
- ከተቋም እንዲወጡ ያልታዘዙ በሆስፒታል መቆየት ለቀጠሉ

## በቅሬታዎች፣ ይግባኝ ጥያቄዎች እና ፍትሐዊ ዳኝነት ሂደት ወቅት የእርስዎ መብቶች

- **ፍትሐዊ ዳኝነት የማግኘት መብት አልዎት።**ፍትሐዊ ዳኝነት ችሎትን ከ Office of Administrative Hearings እርስዎ ወደAmerigroup ይግባኝ ካስገቡ በኋላ እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ እና ይግባኙ በይደር ከታለፈ፣ ወይም የእርስዎን ይግባኝ ጥያቄ ከተቀበልን በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ ይህን ውሳኔ ለእርስዎ እንዲያውቁት ካላደረግን ሆኖም የእርምጃ ማስታወቂያ ለእርስዎ የይግባኝ በይደር መታለፍን በማሳወቅ በፖስታ ቤት እንዲልክልዎት ከተደረገ ከመቶ ሃያ (120) ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ መልስ ካልተሰጥዎት የፍትሐዊ ዳኝነት ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።
- የእርስዎ ይግባኝ ወይም ፍትሐዊ ዳኝነት በሚታይበት ጊዜ እኛ የከለከልነውን ጥቅማ ጥቅም ማግኘትዎን ለመቀጠል መብት አልዎት። በፍትሐዊ ዳኝነት ሂደት ላይ የእርስዎን ጥቅም እንደነበረ ለማስቀጠል፣ የፍትሐዊ ዳኝነቱን በተወሰኑ ቀናት ውስጥ መጠየቅ አለብዎት - ይህ የ10 ቀናት ያህል አጭር ጊዜ ሊሆን ይችላል።
- በቅሬታ መስማቱ እና በይግባኙ ሂደት ላይ ከ Amerigroup የሆነ ግለሰብ እንዲያግዝዎት ለማድረግ መብት አልዎት።
- ራስዎን ወክለው መቅረብ ወይም በእርስዎ ቤተሰብ፣ እንክብካቤ ሰጪ፣ ጠበቃ ወይም ሌላ ተወካይ የመወከል መብት አልዎት።
- ለማናቸውም እርስዎ ለሚያስፈልግዎት ልዩ የጤና ክብካቤ አቅርቦቶችን የማግኘት መብት አልዎት።

- በቂ የሆኑ የ TTY/TTD ችሎታዎች እና አገልግሎቶች ለማየት የተሳናቸው የማግኘት መብት አልዎት።
- በቂ የትርጉም አገልግሎቶችን እና አስተርጓሚን የማግኘት መብት አልዎት።
- ከቅሬታ፣ ይግባኝ ወይም ከፍትሐዊ ዳኝነቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሁሉንም ሰነዶች የመመልከት መብት አልዎት።

በቅሬታ፣ በይግባኝ ወይም በፍትሐዊ ዳኝነቱ ሂደት ላይ ማናቸውም ጥያቄዎች ካልዎት እባክዎ ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች በስልክ ቊጥር1-800-600-4441 ይደውሉ።

## የ HIPAA የግላዊነት ጥበቃ አደራረግ ማስታወቂያ

ይህ ማስታወቂያ በሥራ ላይ የሚውለው ከኤፕሪል 14፣ 2003 ጀምሮ ይሆናል። ሰነዱ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለበት ቀን በማስታወቂያው መጨረሻ ላይ ተገልጿል።

**እባክዎ ይህንን ማስታወቂያ በጥንቃቄ ያንብቡት።የእርስዎን ጥበቃ የሚደረግለት መረጃ /protected health information (PHI)/ ማን ሊመለከት እንደሚችል ይነግርዎታል። እኛ ከማጋራታችን በፊት መቼ የእርስዎን ይሁንታፈቃድ ማግኘት እንዳለብን ይነግርዎታል። መቼ የእርስዎን ይሁንታፈቃድ ሳናገኝ ማጋራት እንደምንችል ይነግርዎታል። የእርስዎን መረጃ ለመመልከት እና ለመለወጥ ምን መብቶች እንዳልዎት ይነግርዎታል።**

ስለ እርስዎ ጤና እና ገንዘብ የተመለከተ መረጃ የግል ነው። ሕጉ እንዲህ የመሰለውን መረጃ፣ ማለትም PHI የሚባለውን ለእኛ ተመዝጋቢዎች ደኅንነቱን ጠብቀን ማስቀመጥ እንዳለብን ይደነግጋል። ይህ ማለት አሁን ላይ ተመዝጋቢ ከሆኑ ወይም ተመዝጋቢ ከነበሩ የእርስዎ መረጃ ደኅንነቱ የተጠበቀ ነው ማለት ነው።

እርስዎ ብቁ ከሆኑ እና ለእኛ የጤና መድን ሽፋን ዕቅድ ከተመዘገቡ በኋላ ከስቴት ኤጀንሲዎች ስለ እርስዎ መረጃን ለ Medicaid እና Children's Health Insurance Program እናገኛለን። እኛ እሺ እንድንል እና የእርስዎን የጤና ክብካቤ ወጪ መክፈል እንድንችል ከእርስዎ ዶክተሮች፣ ክሊኒኮች፣ ላብራቶሪዎች እና ሆስፒታሎች ጭምር መረጃውን እናገኛለን።

ለእኛ የተነገረንን፣ በጽሑፍ የተሰጠንን ወይም በኮምፒዩተር ላይ የተቀመጠን PHI ለመጠበቅ እኛ ምን ማድረግ እንዳለብን ሕጉ የሚነግረንን ለእርስዎ እንድንነግር ፌደራል ሕጉ ያስገድደናል። በተጨማሪ ምን ያክል ደኅንነቱን ጠብቀን እንደምናስቀምጠው ለእርስዎ መንገር አለብን። ለ PHI ጥበቃ ለማድረግ፦

- በወረቀት ላይ (ቁሳዊ ይባላል)፣ እኛ
  - የእኛን ቢሮዎች እና ፋይሎች መቆለፍ አለብን
  - የጤና መረጃ ያለባቸውን ወረቀቶች ሌሎች እንዳያገኙዋቸው ማውደም አለብን
- በኮምፒዩተር ላይ የተቀመጠ (ቴክኒካዊ ይባላል)፣ እኛ
  - ትክክለኛዎቹ ሰዎች ብቻ መግባት እንዲችሉ የይለፍ ቃላትን መጠቀም አለብን
  - የእኛን ሥርዓቶች ለመቆጣጠር ልዩ ፕሮግራሞችን መጠቀም
- ለእኛ በሚሠሩ ሰዎች፣ ዶክተሮች ወይም ከስቴቱ ከእኛ ጋር የተጋራ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ መረጃ፣ እኛ
  - መረጃ ደኅንነቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲቀመጥ ደንቦችን ማውጣት አለብን (ይህ ፖሊሲዎች እና አሠራሮች ይባላል)
  - ለእኛ የሚሠሩ ሰዎች ደንቦቹን እንዲያከብሩ ማስተማር አለብን

**የእርስዎን PHI ለመጠቀም እና ለማጋራት ለእኛ መቼ ችግር የለውም?**
የእርስዎን PHI ከእርስዎ ቤተሰብ ወይም እርስዎ እንዲያግዝዎት ለመረጡት ግለሰብ ወይም እርስዎ ምንም ችግር የለውም ካሉን የእርስዎን የጤና ክብካቤ ወጪ ለሚከፍለው ግለሰብ ልናጋራ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ በሚከተሉት ሁኔታዎች የእርስዎን ይሁንታፈቃድ**ሳናገኝ** ልንጠቀምበት እና ልናጋራው እንችላለን፦

- **ለእርስዎ የሕክምና እንክብካቤ**
  - እርስዎ የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማገዝ ለዶክተሮች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች
- **ለክፍያ፣ ለጤና ክብካቤ ኦፕሬሽኖች፣ እና ሕክምና**
  - ለእርስዎ የጤና ክብካቤ እኛን ክፍያን ከሚጠይቁን ዶክተሮች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጋር መረጃን ለመጋራት
  - እርስዎ የጤና ክብካቤ ወይም አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት እኛ እንከፍልልዎታለን ስንል
  - የእኛን ፕሮግራሞች የተሻሉ ለማድረግ መንገዶችን ለማግኘት፣ እንዲሁም የእርስዎን PHI ለክፍያ፣ ለጤና ክብካቤ ኦፕሬሽኖች፣ እና ሕክምና መልእክት ልውውጦች የጤና መረጃን ለመለዋወጥ። ይህ እንዲደረግ የማይፈልጉ ከሆነ ለተጨማሪ መረጃ **www.myamerigroup.com/DC** ን ይጎብኙ።

- **ለጤና ክብካቤ የንግድ ሥራ ዓላማዎች**
  - ኦዲቶችን፣ የማጭበርበር እና የበደል መከላከያ ፕሮግራሞችን፣ ዕቅድ አወጣጦችን እና የዕለት ተዕለት ሥራን ለማገዝ
  - የእኛን ፕሮግራሞችን የተሻሉ ለማድረግ መንገዶችን ለማግኘት
- **ለሕዝብ ጤና ዓላማዎች**
  - የሕዝብ ጤና ጥበቃ ባለሥልጣናት ሕዝብ እንዳይታመም ወይም እንዳይጎዳ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለማገዝ
- **በእርስዎ እንክብካቤ ከሚያግዙ ወይም ከሚከፍሉ ጋር**
  - ከእርስዎ ቤተሰብ ወይም እርስዎ እንዲያግዝዎት ለመረጡት ግለሰብ ወይም እርስዎ ምንም ችግር የለውም ካሉን የእርስዎን የጤና ክብካቤ ወጪ ከሚከፍለው ግለሰብ ጋር።
  - እርስዎ ለራስዎ መናገር የማይችሉ ከሆነ እና ለእርስዎ የተሻለ ከሆነ በእርስዎ የጤና እንክብካቤ ከሚያግዝ ወይም ክፍያን ከሚፈጽም ግለሰብ ጋር

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የእርስዎ እንክብካቤ፣ ክፍያ፣ የዕለት ተዕለት የንግድ ሥራ ተግባራት፣ ምርምር ወይም ሌሎች ነገሮች በቀር ለሁሉም የእርስዎን PHI ከመጠቀማችን ወይም ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ይሁንታፈቃድ በጽሑፍ ማግኘት አለብን። ከእርስዎ ዶክተር ስለእርስዎ የሥነልቦና ቴራፒ የተሰጡ ማስታወሻ ጽሑፎችን ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ይሁንታፈቃድ በጽሑፍ ማግኘት አለብን።

ከዚህ ቀደም የሰጡትን የጽሑፍ ይሁንታፈቃድ መልሰው መውሰድ እንደሚፈልጉ ለኛ በጽሑፍ ሊያሳውቁን ይችላሉ። የእርስዎ ይሁንታፈቃድ እያለን የተጠቀምንበትን ወይም ያጋራነውን መልሰን ልናመጣው አንችልም። ሆኖም ግን የእርስዎን PHI ለወደፊቱ ከመጠቀም ወይም ከማጋራት እንቆጠባለን።

**ሌሎች የምንችልባቸው መንገዶች — ወይም ሕጉ — የእርስዎን PHI መጠቀም እንዳለብን የሚደነግጋቸው:-**

- ፖሊስን እና ሌሎች ግለሰቦች ሕግን ማክበራቸውን የሚያረጋግጡ ሌሎች ግለሰቦች ለማገዝ
- በደል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ
- ስንጠየቅ ፍርድ ቤትን ለማገዝ
- ለሕጋዊ ሰነዶች መልስ ለመስጠት
- እንደ ኦዲቶች ወይም ምርመራዎች ለመሳሰሉ የጤና ምልከታ ኤጀንሲዎች መረጃ ለመስጠት
- የእርስዎን ስም እና የአሟሟት ሁኔታ እንዲያውቁ ለማገዝ ለአስከሬን መርማሪዎች፣ የሕክምና መርማሪዎች ወይም የቀብር አስፈጻሚዎች
- ለሳይንስ ምርምር የእርስዎን የሰውነት ክፍሎች እንዲሰጡ እርስዎ ሲጠይቁ ለማገዝ
- ለጥናትና ምርምር
- እርስዎን ወይም ሌሎችን እንዳትታመሙ ወይም ክፉኛ እንዳትጎዱ ለመከላከል
- በተወሰኑ ሥራዎች ላይ ለመንግሥት የሚሠሩ ግለሰቦችን ለማገዝ
- በሥራ ገበታ ላይ ከታመሙ ወይም ከተጎዱ ለሠራተኞች ካሣ ቦርድ መረጃ ለመስጠት

**የእርስዎ መብቶች ምንድን ናቸው?**

- የእርስዎን PHI ለመመልከት እና ቅጂውን ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ሆኖም ግን ሁሉም የእርስዎ የሕክምና ሪኮርድ በእጃችን ላይ አይገኝም። ሙሉውን የእርስዎን የሕክምና ሪኮርድ ቅጂ ከፈለጉ የእርስዎን ዶክተር ወይም ክሊኒክ ይጠይቁ።
- የሆነ ነገር ተሳስቷል ወይም ይጎድላል ብለው ካመኑ እኛ ያለንን የሕክምና ሪኮርድ እንዲለወጥ እኛን መጠየቅ ይችላሉ።
- አንዳንድ ጊዜ የእርስዎን PHI እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ። ሆኖም ግን በእርስዎ ጥያቄ የግድ መስማማት አይጠበቅብንም።
- እኛ ለእርስዎ ካለን አድራሻ ወደ ተለየ አድራሻ ወይም በሌላ መንገድ የእርስዎ PHI እንዲላክልዎት መጠየቅ ይችላሉ። ይህን ልናደርግ የምንችለው እኛ ለእርስዎ የያዝነው አድራሻ እርስዎን አደጋ ውስጥ ሊከትዎት የሚችል ከሆነ ነው።
- የእርስዎን PHI ባለፉት ስድስት ዓመታት በሙሉ ከሌላ ከማን ጋር በመቼ ጊዜያት እንደተጋራን ለእርስዎ እንድንነግርዎት ሊጠይቁን ይችላሉ። እዚህ ላይ ባልዘረዘርናቸው የጤና ክብካቤ፣ የክፍያ፣ የዕለት ተዕለት የጤና ክብካቤ ሥራ ወይም ሌላ አንዳንድ ምክንያቶች ያጋራንባቸውን ጊዜያት ዝርዝር አይሰጥም።
- የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በኢሜይል ለመቀበል ተስማምተው የነበሩ እንኳ ቢሆን የወረቀት ቅጂ በማንኛውም ጊዜ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ለአንድ አገልግሎት ሙሉውን ክፍያ መጠየቂያ ቢል ራስዎ ከከፈሉ ስለ አገልግሎቱ መረጃ የእርስዎ ዶክተር ከእኛ ጋር እንዳያጋሩ መጠየቅ ይችላሉ።

**እኛ ምን ማድረግ አለብን?**

- በዚህ ማስታወቂያ ከተናገርነው በስተቀር የእርስዎን PHI በምሥጢር መያዝ እንዳለብን ሕጉ ይደነግጋል።

- ስለ ግላዊነት እኛ ምን ማድረግ እንዳለብን ሕጉ የሚለውን ለእርስዎ መንገር አለብን።
- በዚህ ማስታወቂያ ላይ ማድረግ አለብን ያልነውን ማድረግ አለብን።
- እንደ እርስዎ በአደጋ ውስጥ ካሉ በመሳሰሉ ትርጉም የሚሰጡ ምክንያቶች ከመደበኛው የፖስታ አድራሻ ውጭ በሌላ መንገድ ወይም በሌላ አድራሻ የእርስዎን PHI መላክ አለብን።
- እኛ እንዳናጋራው እርስዎ ከጠየቁን በኋላ የእርስዎን PHI ማጋራት ከተገደድን ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።
- እዚህ ላይ እኛ ከተናገርነው በላይ የስቴት ሕግ እንድናደርግ የሚያስገድደን ከሆነ እነዚህን ሕግጋት እናከብራለን።
- የእርስዎ PHI መብት ጥሰት ተፈጽሞበታል ብለን የምናስብ ከሆነ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።

**ልናነጋግርዎት እንችል ይሆናል**
የእኛን ተባባሪዎች እና/ወይም አገልግሎት አቅራቢዎች ጨምሮ እኛ የሽቦ አልባ የስልክ ቍጥርን ጨምሮ እርስዎ በሰጡን ማናቸውም ስልክ ቍጥሮች አውቶማቲክ የቴሌፎን መደወያ ሥርዓትን እና/ወይም አስቀድሞ የተቀዳ መልእክትን በመጠቀም ልንደውልልዎት ወይም የጽሑፍ መልእክት ልንልክልዎት እንደምንችል መስማማትዎን ያረጋግጣሉ። ያለምንም ገደብ እነዚህ የስልክ ጥሪዎች ወይም የጽሑፍ መልእክቶች ስለ የሕክምና አማራጮች፣ ሌላ ከጤና ጋር የተገናኙ ጥቅማ ጥቅሞች እና አገልግሎቶች፣ ምዝገባ፣ ክፍያ ወይም የክፍያ መጠየቂያ ጉዳይ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ጥያቄዎች ቢኖርዎትስ?**
ስለ የእኛ የግላዊነት ደንቦች ጥያቄዎች ካልዎት ወይም የእርስዎን መብቶች ማስከበር የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ወደ የአባል አገልግሎቶች በስልክ ቍጥር 1-800-600-4441 ይደውሉ። ሙሉ በሙሉ መስማት የማይችሉ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት ወደ **TTY 711** ይደውሉ።

**ቅሬታ ካልዎትስ?**
ልናግዝዎት ዝግጁ ነን። የእርስዎ PHI ደኅንነቱ እንዳልተጠበቀ ሆኖ ከተሰማዎት፣ ወደ የአባል አገልግሎቶች መደወል ወይም Department of Health and Human Services ን ማነጋገር ይችላሉ። ቅሬታ ስላቀረቡ ምንም መጥፎ ነገር በእርስዎ ላይ አይፈጠርም።

**ወደ Department of Health and Human Services ደብዳቤ ይጻፉ ወይም ይደውሉ:-**
Office for Civil Rights
U.S. Department of Health and Human Services
150 S. Independence Mall West
Suite 372, Public Ledger Building
Philadelphia, PA 19106-9111
የስልክ ቍጥር:- 1-800-368-1019
TDD: 1-800-537-7697
ፋክስ:- 1-215-861-4431

ይህን የጤና ኢንሹራንስ ተገዢነት እና ተጠያቂነት ሕግ /Health Insurance Portability and Accountability Act (HIPAA)/ ማስታወቂያ እና የእርስዎን PHI ደኅንነቱ እንዲጠበቅ የምናደርግባቸውን መንገዶች መለወጥ መብታችን የተጠበቀ ነው። ያ ሲያጋጥም፣ በውስጥ ጋዜጣ ስለተደረጉት ለውጦች እርስዎ እንዲያውቁዋቸው እናደርጋለን። በተጨማሪ በድር ላይ **www.myamerigroup.com/pages/privacy.aspx**ላይ እንለጥፋቸዋለን።

**ዘር፣ ጎሣ እና ቋንቋ**
ስለ የእርስዎ የዘር፣ የጎሣ፣ የቋንቋ መረጃ ከስቴት የ Medicaid ኤጀንሲ እና ከ Children's Health Insurance Program እንቀበላለን። ይህን መረጃ በዚህ ማስታወቂያ ላይ በተገለጸው መሠረት ጥበቃ እናደርግለታለን።

ይህን መረጃ ለሚከተሉት ዓላማዎች እንጠቀምበታለን:-
- የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ እንደሚያገኙ ለማረጋገጥ
- የጤና ከብካቤ ውጤቶችን ለማሻሻል ፕሮግራሞችን ለመፍጠር
- የጤና ትምህርት መረጃን ለማዘጋጀት እና ለመላክ
- ዶክተሮች የእርስዎን የቋንቋ ፍላጎቶች እንዲያውቁ ለማድረግ
- የትርጉም አገልግሎቶችን ለመስጠት

ይህን መረጃ ለሚከተሉት ዓላማዎች **አንጠቀምበትም**:-
- የጤና ኢንሹራንስ ለመስጠት
- ለአገልግሎት ምን ያክል ክፍያ መጠየቅ እንዳለብን ለመወሰን

- ጥቅማ ጥቅሞችን ለመወሰን
- ላልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች አሳልፎ ለመስጠት

**የእርስዎ የግል መረጃ**
በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተናገርነው የግል መረጃን /personal information (PI)/ ልንጠይቅ፣ ልንጠቀም እና ልናጋራ እንችል ይሆናል። የእርስዎ PI ይፋዊ ጉዳይ አይደለም እና እርስዎ ማን እንደሆኑ ለእኛ ይነግረናል። ብዙውን ጊዜ ለኢንሹራንስ ምክንያቶች ይወሰዳል።

- ስለሚከተሉት የእርስዎ ነገሮች ውሳኔ ላይ ለመድረስ የእርስዎን PI ልንጠቀም እንችል ይሆናል፡-
  - ጤና
  - ልማዶች
  - የትርፍ ጊዜ ሥራዎች
- እንደሚከተሉት ከመሳሰሉ ሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ስለ እርስዎ PI ልናገኝ እንችላለን፡-
  - ዶክተሮች
  - ሆስፒታሎች
  - ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች
- በአንዳንድ ሁኔታዎች ከእርስዎ ይሁንታፈቃድን ሳናገኝ ከእኛ ኩባንያ ውጭ ካሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች ጋር PI ን ልናጋራ እንችላለን።
- ለእርስዎ አይሆንም እንዲሉ ዕድል ለመስጠት ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት ይህንኑ እንዲያውቁት እናደርጋለን።
- የእርስዎን PI እንዳንጠቀም ወይም እንዳናጋራ ከፈለጉ ለእኛ እንዴት ማሳወቅ እንደሚችሉ እንነግርዎታለን።
- የእርስዎን PI መመልከት እና መለወጥ መብት አልዎት።
- የእርስዎ PI ደኅንነቱ ተጠብቆ መቀመጡን እናረጋግጣለን።

በጃንዋሪ 20፣ 2016 እንደገና የተሻሻለ

## Office of Health Care Ombudsman እና Bill of Rights

የ Health Care Ombudsman Program ከእርስዎ MCO የጤና ክብካቤ ሲያገኙ ለእርስዎ እገዛ እና ምክር የሚሰጥ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመንግሥት ፕሮግራም ነው። Health Care Ombudsman የሚከተሉትን አገልግሎቶች ሊሰጥ ይችላል፡-

- እርስዎ ለማግኘት መብቱ ያልዎትን የጤና ክብካቤ ማብራራት፤
- ስለ የእርስዎ የጤና ክብካቤ የእርስዎን ጥያቄዎች እና የሚያሳስብዎትን ነገሮች ምላሽ መስጠት፤
- በ MCO ውስጥ እንዳለ ተመዝጋቢነትዎ መጠን እርስዎ ያልዎትን መብቶች እና ግዴታዎች እንዲረዱ ማገዝ፤
- እርስዎ የሚያስፈልግዎትን አስፈላጊ የጤና አገልግሎቶች ማግኘት ላይ እገዛን መስጠት፤
- ስለ የእርስዎ የጤና ክብካቤ ጥራት ለሚኖርዎት የእርስዎ ጥያቄዎች እና የሚያሳስብዎት ነገሮች ምላሽ መስጠት፤
- ከእርስዎ ዶክተር ወይም ሌላ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ያሉብዎትን ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙባቸው ማገዝ፤
- ከእርስዎ MCO ጋር ያሉ ቅሬታዎችን እና ችግሮችን መፍትሔ እንዲያገኙ እገዛ መስጠት፤
- በይግባኝ ሂደቶች ላይ ማገዝ፤ እና
- የፍትሐዊ ዳኝነት ጥያቄን ሰነድ በማዘጋጀት ላይ ለእርስዎ እገዛ መስጠት።

Health Care Ombudsman ን ለማግኘት እባክዎ በስልክ ቁጥር 202-724-7491 ወይም 1-877-685-6391 (ነጻ የስልክ መሥመር) ይደውሉ። Health Care Ombudsman በቅሬታዎች፣ ይግባኞች ወይም የፍትሐዊ ዳኝነት ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ **አይሰጥም**። የ Office of Health Care Ombudsman & Bill of Rights በሚከተለው አድራሻ ላይ ይገኛል፡-

One Judiciary Square
441 4th Street, NW
Suite 900 South
Washington, DC 20001
ስልክ ቁጥር፦ (202) 724-7491
ፋክስ፦ (202) 442-6724
ነጻ የስልክ መሥመር፦ 1(877) 685-6391
ኢሜይል፦ healthcareombudsman@dc.gov

## ትርጓሜዎች

| | |
|---|---|
| **የላቀ መመሪያ** | እርስዎ የሚፈልጉትን ለመናገር አቅም እስከሚያጡ ደረጃ ከታመሙ ወይም ጉዳት ከደረሰብዎት ሌሎች እርስዎ ምን ዓይነት ሕክምና እንደሚፈልጉ ወይም እንደማይፈልጉ የሚያሳውቅ እርስዎ የሚፈርሙበት በጽሑፍ የተዘጋጀ ሕጋዊ ሰነድ ነው። |
| **ጠበቃ** | እርስዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና ክብካቤ እና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲያገኙ የሚያግዝዎት ግለሰብ። |
| **ይግባኝ** | ይግባኝ Amerigroup እርስዎ ቀደም ብለው ላገኙዋቸው ለጤና ክብካቤ አገልግሎቶች ወይም ለአገልግሎቶች ክፍያ ሲከለክል በዚህ ውሳኔው እርስዎ ካልተስማሙ እርስዎ የሚያቀርቡት የቅሬታ ዓይነት ነው። እርስዎ እየተቀበሉ ያሉት አገልግሎት እንዲቋረጥ የተሰጠ ውሳኔን በመቃወም እንዲህ ዓይነቱን ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። |
| **ቀጠሮ** | እርስዎ እና የእርስዎ ዶክተር ስለ የእርስዎ የጤና ክብካቤ ፍላጎቶች ለማየት የምትስማሙበት የተወሰነ ጊዜ እና ቀን። |
| **የጉዳይ ክትትል ሠራተኛ** | ለ Amerigroup የሚሠራ ግለሰብ ሆኖ አንድ ተመዝጋቢ ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ የሚያስችል እንክብካቤ እና መረጃ እንዲያገኙ ያግዛል። |
| **ምርመራ** | *በሐኪም መታየት የሚለውን ይመልከቱ* |
| **የወሊድ መከላከያ** | እርግዝናን መቆጣጠሪያ |
| **የሚሸፈኑ አገልግሎቶች** | በአንድ አገልግሎት አቅራቢ ተሰጥቶ ሲጠናቀቅ Amerigroup የሚከፍልባቸው የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች። |
| **ዲቶክሲፊኬሽን** | እንደ አደገኛ መድኃኒቶች እና አልኮል ያሉ ጎጂ ንጥረ ነገሮችን ከሰውነት ውስጥ ማስወገድ |
| **ዕድገት** | የእርስዎ ልጅ የሚያድግበት መንገድ። |
| **የበሽታ ቊጥጥርና አስተዳደር ፕሮግራም** | እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት ወይም የአእምሮ ሕመም የመሳሰሉ ሥር የሰደዱ በሽታዎች ወይም ልዩ የጤና ክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ክብካቤ ፍላጎት ያለባቸው ሰዎችን የሚያግዝ ፕሮግራም። |
| **ዘለቄታ ያለው የሕክምና መሣሪያ (Durable Medical Equipment)** | የእርስዎ ዶክተር በእርስዎ ቤት ውስጥ እንዲጠቀሙ የሚጠይቅዎት ወይም የሚነግርዎት ልዩ የሕክምና መሣሪያ። |
| **የድንገተኛ እንክብካቤ** | ለከባድ፣ ድንገተኛ፣ አንዳንድ ጊዜ ሕይወትን ሊያሰጋ የሚችል ሁኔታ ወዲያውኑ የሚሰጥ የሕክምና ክብካቤ። |
| **EPSDT** | **E**arly, **P**eriodic **S**creening, **D**iagnosis and **T**reatment Program (በተጨማሪ Health Check Program የሚባል) ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ተመዝጋቢዎች የሚሰጥ የጤና ክብካቤ። |
| **ፍትሐዊ ዳኝነት** | ቅሬታ ካስገቡ በዲሲ የአስተዳደራዊ ፍትሐዊ ዳኝነት በኩል ችሎት እንዲቆምልዎት መጠየቅ ይችላሉ። |
| **የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት** | እንደ የእርግዝና ምርመራዎች፣ የወሊድ መከላከያ፣ በግብረሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ የኤችአይቪ/ኤድስ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት የመሳሰሉ አገልግሎቶች። |
| **የቤተሰብ እና የአጠቃላይ ሕክምና ዶክተር** | ቤተሰቡን በሙሉ ማከም የሚችል ዶክተር። |
| **ቅሬታ** | በሚያገኙት ክብካቤ ወይም Amerigroup በሚሰጥዎት የጤና ክብካቤ አገልግሎቶች ደስተኛ ካልሆኑ ቅሬታ ለማስገባት ወደ ተመዝጋቢ አገልግሎቶች መደወል ይችላሉ። |
| **አነስተኛ መጽሐፍ** | ስለ Amerigroup እና የእኛ አገልግሎቶች መረጃ ለእርስዎ የሚሰጥዎት ይህ መጽሐፍ። |
| **Health Check Program** | *EPSDT ን ይመልከቱ* |
| **መስማት የተሳናቸው** | በደንብ መስማት የማይችሉ ከሆነ ወይም ሙሉ በሙሉ መስማት የተሳንዎት ከሆኑ። |
| **IDEA** | Individuals with Disabilities Education Act፤ የአእምሮ ዕድገት መዘግየት ችግር ላለባቸው እና ልዩ የጤና ክብካቤ ፍላጎት ላላቸው ልጆች አገልግሎቶችን የሚያሰጥ የፌደራል ሕግ። |
| **ክትባት** | ሾት ወይም ክትባት። |
| **የውስጥ ደዌ ሐኪም** | ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በላይ ለሆኑ ጎልማሶች እና ልጆች የሚያክም ዶክተር። |
| **የአስተርጓሚ/የትርጉም አገልግሎቶች** | የእርስዎን ቋንቋ መናገር ከሚችል ሰው ጋር እርስዎ መነጋገር ሲፈልጉ ወይም ከእርስዎ ዶክተር ወይም ሆስፒታል ጋር ለመነጋገር እገዛ ሲፈልጉ በ Amerigroup የሚሰጥ እገዛ። |
| **Managed Care Organization (MCO)** | ለእርስዎ የጢአና ክብካቤ እና የጤና አገልግሎቶችን እንዲሰጥዎት በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሚከፈለው ኩባንያ። |
| **የሚተዳደር የእንክብካቤ የመድን ዕቅድ** | *Managed Care Organization ን የሚለውን ይመልከቱ* |

| | |
|---|---|
| **እናትነት** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆኖ የምትቆይበት እና ከወሊድ በኋላ ያለው አጭር ጊዜ። |
| **ተመዝጋቢ** | በ Amerigroup የአገልግሎት ሰጪ አውታረ-መረብ በኩል የጤና ክብካቤ የሚያገኝ ግለሰብ። |
| **የተመዝጋቢ መለያ መታወቂያ ካርድ** | የእርስዎ ዶክተሮች፣ ሆስፒታሎች፣ የመድኃኒት መደብሮች እና ሌሎች እርስዎ የ Amerigroup ተመዝጋቢ እንደሆኑ እንዲያውቁ የሚያደርግ ካርድ። |
| **የአእምሮ ጤና** | አንድ ግለሰብ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እንደሚያስብ፣ ምን ስሜት እንደሚሰማው እና ምን ድርጊት እንደሚፈጽም። |
| **የአውታረ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች** | የ Amerigroup አካል የሆኑ የእርስዎን ጤና የሚንከባከቡ ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **የመድን ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች** | በአንድ አገልግሎት አቅራቢ ተሰጥቶ ሲጠናቀቅ Amerigroup የማይከፍልበት የጤና ክብካቤ አገልግሎት። |
| **OB/GYN** | የፅንስ ሐኪም/የማህፀን ሐኪም፤ የአንዲት ሴት ጤናን ነፍሰጡር ስትሆን ጨምሮ ለመንከባከብ የሠለጠነ ዶክተር። |
| **ከአውታረ-መረብ ውጭ የሆነ አገልግሎት ሰጪዎች** | የ Amerigroup አካል **ያልሆኑ** ነገር ግን የእርስዎን ጤና የሚንከባከቡ ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **የሕፃናት ሐኪም** | የልጆች ዶክተር። |
| **መድኃኒት መደብር** | የእርስዎን መድኃኒት የሚያገኙበት ቦታ። |
| **የሐኪም ማበረታቻ ዕቅድ** | የእርስዎ ዶክተር ከ Amerigroup ጋር ልዩ ስምምነት እንዳለው ለእርስዎ ይነግርዎታል። |
| **ድኅረ ወሊድ ክብካቤ** | አንዲት ሴት ልጇን ከተገላገለች በኋላ የሚሰጥ የጤና ክብካቤ። |
| **የቅድመ ወሊድ ክብካቤ** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና በምትቆይበት ጊዜ በሙሉ የሚሰጥ ክብካቤ። |
| **የሐኪም የመድኃኒት ማዘዣ ሰነድ** | የእርስዎ ዶክተር ለእርስዎ የሚያዝልዎት መድኃኒት፤ መድኃኒት ለማግኘት ወደ መድኃኒት መደብር ይዘውት መሄድ አለብዎት። |
| **የመከላከያ የምክር አገልግሎት** | ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ ወይም እንዳይታመሙ ወይም ጉዳት እንዳይደርስብዎት ለመጠንቀቅ የሚችሉባቸውን መንገዶች በተመለከተ እርስዎ ከሆነ ግለሰብ ጋር ሲነጋገሩ። |
| **ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ /Primary Care Provider (PCP)/** | አብዛኛውን ጊዜ እርስዎን የሚከታተልዎት ዶክተር። |
| **በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት** | የጤና ክብካቤ ወይም ሕክምና ለማግኘት ከ Amerigroup የሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ |
| **የአገልግሎት አቅራቢ ማውጫ** | የ Amerigroup አካል የሆኑ ሁሉንም አገልግሎት ሰጪዎችን የያዘ ዝርዝር። |
| **አገልግሎት ሰጪዎች** | የእርስዎን ጤና የሚንከባከቡ ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሪፌራል** | የእርስዎ ዋናው ዶክተር ሌላ የተለየ ዶክተር ጋር ሄደው እንዲታዩ የጽሑፍ ማስታወሻ ሲሰጥዎት። |
| **መደበኛ እንክብካቤ** | ከእርስዎ ተቀዳሚ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ወይም የእርስዎ ተቀዳሚ ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ የሚልክዎት ዶክተር ዘንድ በመሄድ የሚያገኙት መደበኛ እንክብካቤ። መደበኛ ሕክምና የጤና ምርመራ፣ አካላዊ እና የጤና በሐኪም መታየት እና እንደ የስኳር በሽታ፣ የደም ግፊት እና አስም ለመሳሰሉ የጤና ችግሮች የሚሰጥ መደበኛ ክብካቤ |
| **በሐኪም መታየት** | የእርስዎ ዶክተር ወይም ሌላ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ እርስዎ ጤናማ መሆንዎትን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ምርመራ። ይህ የመስማት ችሎታ ምርመራ፣ የዕይታ ምርመራ፣ ወይም የእርስዎ ልጅ በጤናማ ሁኔታ እያደገ መሆኑን ለማወቅ የሚደረግ ምርመራ ሊሆን ይችላል። |
| **ራስን በራስ ሪፌር ማድረጊያ አገልግሎቶች** | ከእርስዎ ዋናው ዶክተር የጽሑፍ ማስታወሻ ወይም ሪፌራል ሳይኖርዎት ሊያገኙ የሚችሉዋቸው የተወሰኑ ዓይነት አገልግሎቶች |
| **አገልግሎቶች** | ከእርስዎ ዶክተር ወይም ሌላ የጤና ክብካቤ አገልግሎት ሰጪ የሚያገኙት እንክብካቤ። |
| **ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች** | ከሌሎች ሕፃናት እና ጎልማሶች ፍላጎት በላይ ወይም የተለዩ የሆኑ የጤና ክብካቤ እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት የሚፈልጉ ሕፃናት እና ጎልማሶች። |
| **ስፔሺያሊስት** | እንደ ጆሮ፣ አፍንጫ እና ጉሮሮ ዶክተር ወይም የእግር ዶክተር ያሉ ልዩ ዓይነት የሕክምና ክብካቤ እንዲሰጥ የሠለጠነ ዶክተር። |
| **የስፔሺያሊቲ ክብካቤ** | አንድን የተወሰነ የጤና ክብካቤ እንዲሰጡ በሠለጠኑ ዶክተሮች ወይም ነርሶች የሚሰጥ የጤና ክብካቤ። |
| **የማምከን ሕክምና** | ለወደፊቱ ልጆች እንዲኖርዎት የማይፈልጉ ከሆነ ሊደረግልዎት የሚችል የቀዶ ጥገና ሕክምና። |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | ወደ የእርስዎ ቀጠሮ እንዲሄዱ ከ Amerigroup የሚሰጥ እገዛ። የሚያገኙት የትራንስፖርት አገልግሎት እንደ የእርስዎ የሕክምና ፍላጎት የሚመረኮዝ ይሆናል። |
| **ሕክምና** | ከእርስዎ ዶክተር የሚያገኙት ክብካቤ። |

| | |
|---|---|
| **አስቸኳይ እንክብካቤ** | ወዲያውኑ ባይሆንም በ 24 ሰዓት ውስጥ ማግኘት ያለብዎት የሕክምና ክብካቤ። |
| **ማየት የተሳናቸው** | በደንብ ማየት የማይችሉ ከሆነ ወይም ዐይነ ስውር ከሆኑ። |

## Health Check ለሕጻናት ፕሮግራም

የእርስዎ ልጆች ጤናማ ሆነው እንዲያድጉ ለማገዝ እንፈልጋለን። የእርስዎ ልጅ በ DC Healthy Families (Medicaid) ፕሮግራም ውስጥ ካለ፣ የእርስዎ ልጅ በ Health Check ወይም በተጨማሪ Early and Periodic Screening, Diagnosis and Treatment (EPSDT) በሚባለው ፕሮግራም ውስጥ ይሆናል። መደበኛ ምርመራዎችን ማድረግ የጤና ችግሮችን በጊዜ ለማወቅ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች የጤና ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመከላከል ያስችላል።

ከ Health Check ጋር የእርስዎ ልጅ ከልደት እስከ 21 ዓመት ዕድሜ ድረስ የሚከተሉትን ጨምሮ ነጻ ምርመራዎችን ያገኛል፡-

- ሙሉ አካላዊ ምርመራ
- የአካላዊ እና አእምሮዋዊ ዕድገት ምርመራ
- ክትባቶች
- የጥርስ ሕክምና ምርመራ
- የዕይታ ምርመራ
- የጆሮ ምርመራ
- በደም ውስጥ ያለ ሊድ ደረጃ ምርመራን ጨምሮ የላብራቶሪ ምርመራዎች
- የሥነ ባህሪ ጤና ምርመራ
- ሕክምና ወይም አገልግሎት ሪፌራል
- የጤና ትምህርት

በሕክምና አስፈላጊ ከሆነ፡-

- የአካል፣ አክፔሽናል እና የንግግር ቴራፒ
- የዕይታ እና የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች
- የሥነ ባሕሪያዊ ጤና አገልግሎቶች፡-
- መድሃኒቶች
- የሕክምና መሣሪያዎች እና አቅርቦቶች

ከእርስዎ ልጅ PCP ጋር መደበኛ ምርመራዎችን ማድረግ፡-

- የእርስዎ ልጅ ጤናማ ሆኖ እንዲያድግ ሊያግዝ ይችላል
- የጤና ችግሮችን በጊዜ ማወቅ እና
- በአንዳንድ ሁኔታዎች የጤና ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመከላከል ያስችላል

ችግር አለ ብለው የሚያስቡ ከሆነ ወዲያውኑ ወደ የእርስዎ ልጅ PCP ይደውሉ።

በእነዚህ ዕድሜዎች ላይ ምርመራዎች ይመከራሉ፡-

| ጨቅላ ሕፃን | ዳዴ የሚል ሕፃን | ልጅ/ታዳጊ ጎረምሳ/ወጣት |
|---|---|---|
| 1 ወር | 12 ወራት | ከ3 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ እስከ 20 በዓመት አንድ ጊዜ |
| 2 ወራት | 15 ወራት | |
| 4 ወራት | 18 ወራት | |
| 6 ወራት | 24 ወራት | |
| 9 ወራት | 30 ወራት | |

## ለልጆች የሚመከር የክትባት (ሾት) መርሐ ግብር

ልጅዎ ክትባቶችን በጊዜ መከተቡ በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህን የቅደም ተከተል እርምጃዎች ይከተሉ፡-

1) የልጅዎ PCP ክትባት ያስፈልጋል ሲል ልጅዎን ወደ ዶክተር ይውሰዱት።
2) ልጅዎ የሚያስፈልገውን ክትባት ዱካ ለመከታተል ከዚህ በመቀጠል የተሰጠውን ቻርት ይጠቀሙበት።

ከዚህ በተጨማሪ ለሁሉም ዕድሜዎች ለማንበብ ቀላል የሆኑ የክትባት ቻርቶችን ከ Centers for Disease Control and Prevention (CDC) የድር ጣቢያ www.cdc.gov/vacccines/schedules ላይ ማግኘት ይችላሉ።

| **ከልደት እስከ 3 ዓመት** | |
|---|---|
| **ዕድሜ** | **ክትባት** |
| ልደት | HepB #1 |
| 2 ወራት | HepB#2፣ DTaP#1፣ RV#1፣<br>Hib#1፣ PCV#1፣ IPV#1 |
| 4 ወራት | DTaP#2፣ RV#2፣ Hib#2፣<br>PCV#2፣ IPV#2 |
| 6 ወራት | HepB#3፣ Hib#3፣ DTaP#3፣<br>RV#3፣ PCV#3፣ IPV#3 |
| 12 ወራት | HiB#4፣ MMR#1፣ Varicella #1፣<br>PCV#4<br>HepA#1 |
| 15 ወራት | Varicella #2 ወይም 2nd ዶዝ ዕድሜ 4 ላይ ሊሰጥ ይችላል |
| 18 ወራት | Hep A#2 |
| **ዕድሜ 4-12** | |
| ዕድሜ 4-6 | DTaP፣ MMR፣ IPV |
| ዕድሜ 11-12 | HPV (ለሴት ልጆች ብቻ)፣ MCV4 |
| ዕድሜ 13 ወይም በላይ | Varicella |
| **ዕድሜ 13-18** | |
| ዕድሜ 13-18 | Tdap፣ HPV |
| ዕድሜ 18 ወይም ያነሰ | MCV4 |
| **ከ 6 ወር ጀምሮ** | |
| በየዓመቱ | ወቅትን ጠብቆ የሚከሰት እንፍሉዌንዛ (“ፍሉ”) ክትባት በየዓመቱ ይመከራል |

Amerigroup
District of Columbia

# የዕድገት ቻርት

Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) ፕሮግራም የአእምሮ ዕድገት መዘግየት፣ የአካል ጉዳቶች ወይም ልዩ ፍላጎቶች ላሉት የእርስዎ ልጅ ልዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ዕድሜያቸው ከ 3 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በጊዜ ማረቂያ አገልግሎቶችን ከ Amerigroup ያገኛሉ። ዕድሜያቸው 4 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሕፃናት ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ከ D.C. Public School እና Public Charter School ሥርዓቶች ያገኛሉ።

ይህ የዕድገት ቻርት የእርስዎ ልጅ በአካላዊ እና አእምሮዊ ዕድገት ላይ መዘግየት እንዳለበት ወይም እንደሌለበት እንዲያውቁ እርስዎን ሊያግዝዎት ይችላል። እንደ መመሪያ ይጠቀሙበት። የእርስዎ ልጅ እነዚህን ካሳማዎች ከሌሎች በተመሳሳይ ዕድሜ ካሉ ሕፃናት ቀድሞ ወይም ዘግይቶ ሊደርስባቸው ይችላል። ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም የሚያሳስብዎት ነገሮች ካሉ፣ የእርስዎን ልጅ ዶክተር ያነጋግሩ።

የእኛ የጉዳይ ክትትል ሠራተኞች ስለ IDEA እና ሌሎች የእርስዎ ልጅ ሊያገኛቸው ስለሚችላቸው አገልግሎቶች ተጨማሪ ሊነግርዎት ይችላሉ።

የእርስዎ ልጅ እያደገ ሲሄድ መመልከት ያለብዎት አንዳንድ ነገሮች እዚህ ላይ ቀርበዋል።

| | |
|---|---|
| **በ 7 ወራት መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**<br>• ስማቸው ሲጠራ ራሳቸውን ዞር ማድረግ<br>• ሌላ ሰው ፈገግ ሲል መልሰው ፈገግ ማለት<br>• ድምፅን በድምፅ መልስ መስጠት<br>• እንደ ፒክ-አ-ቡ ያሉ ጨዋታዎችን መውደድ | **በ 2 ዓመታት (24 ወራት) መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**<br>• ከ2-እስከ-4-ቃል ያላቸውን ሐረጎች መጠቀም<br>• ቀላል ትዕዛዞችን መከተል<br>• ከሌሎች ሕፃናት ጋር የመሆን ፍላጎት<br>• ስሙ ሲጠራ ዕቃን ወይም ስዕልን በጣት መጠቆም |
| **በ 1 ዓመት (12 ወራት) መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**<br>• ቀላል የእጅ ውዝዋዜዎችን መጠቀም፣ እጅን "ባይ፣ባይ" በማለት ማወዛወዝ)<br>• እንደ "ማ" እና "ዳ" የመሳሰሉ ድምፆችን መፍጠር<br>• በጨዋታቸው ላይ ድርጊቶችን ማስመሰል (እርስዎ ሲያጨበጭቡ ማጨብጨብ)<br>• "ተው" ሲባል ምላሽ መስጠት | **በ 3 ዓመታት (36 ወራት) መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**<br>• አብረዋቸው ለሚጫወቱ ፍቅርን ማሳየት<br>• ከ4-እስከ-5-ቃል ያላቸውን ዓርፍተ ነገሮችን መጠቀም<br>• ዐዋቂ ሰዎችን እና አብረው የሚጫወቱ ሕፃናትን ማስመሰል (ሌሎች ልጆች ሲሮጡ አብሮ መሮጥ)<br>• ከአሻንጉሊቶች፣ እንስሳት እና ሰዎች ጋር ድራማ መጫወት (ቴዲ ቤር አሻንጉሊትን "መመገብ") |
| **በ 1 1/2 ዓመት (18 ወራት) መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**<br>• ቀላል የማስመሰል ጨዋታን መጫወት (በመጫወቻ ስልክ "ማውራት")<br>• ወደ አስደሳች ዕቃዎች መጠቆም<br>• እርስዎ በእጅዎ ሲጠቁሙ እና እንዲመለከቱ ሲነግሯቸው ዕቃውን መመልከት<br>• ሳይጠይቁ በርካታ ነጠላ ቃላትን መጠቀም | **በ 4 ዓመታት (48 ወራት) መጨረሻ ላይ አብዛኛዎቹ ልጆች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**<br>• ከ4-እስከ-6-ቃል ያላቸውን ዓርፍተ ነገሮችን መጠቀም<br>• ባለ 3-ደረጃ ትዕዛዞችን መከተል ("ልብስ መልበስ፣ ጸጉርህን አበጥር እና ፊትህን ታጠብ")<br>• ከሌሎች ልጆች ጋር መተባበር |

**Amerigroup District of Columbia, Inc.**

የአባል አገልግሎቶች፡-
609 H Street NE, Ste. 600
Washington, DC 20002

This program is funded in part by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.